# ላንቺና ላንተ

የኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሐኪሞች ማህበር
Ethiopian Society of Obstetricians and Gynecologists

ቅፅ አንድ

# ላንቺና ላንተ

## ቅጽ 01

## ማውጫ


- የወንዶች የወሲባዊ ግንኙነት አቢይ ችግር
- ግማሽ ቀን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሙሉ ቀን ራስ ምታት
- ሙያቸው የገባቸው ባለሙያ
- «ለህይወት መዳን ምክንያት እሆናለሁ ብዬ ነው የማስበው»
- የሴት ልጅ ሶስት የስቃይ ምዕራፎች
- በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም-ለምን?
- ልጅ መውለድ ለምን እምቢ ይላል?
- «ባለቤቴ ታምነኛለች ብዬ አልዋሽም ከእሷ ውጪ ከሄድኩ ከንዶም
- የእናቶቻችን ጠላት ማነው?
- ወሲብ በስተእርጅና
- ምግብ፣ ጤንነት እና ወሲብ
- ለደረሳችሁ … እንኳን አደረሳችሁ!
- ከኔጌቲቭና ፖዘቲቭ የደም ዓይነቶች የሚፈጠር ፅንስ
- «ማስተርቤሽን»ን ማቆም ይቻላል? ማቆም የሚገባውስ ለምንድነው?
- ቡና፣ ሻይ፣ ቸኮሌትና ወሲብ
- «ፅንስ ማቋረጥ የማይቻለው መቼ ነው?»
- «ኮንዶም የማይወዱ ወንዶች ብዙ ጊዜ አጋጥመውኛል»
- «አብዛኛው ወንድ መሽታ ቤት ሲገባ የወሲብ እሳት ይፈላበታል!»
- «ባሎቻቸውን የሚያምኑ ሴቶች ያሳዝኑኛል»
- በወግና በልማድ የታሰሩ መብቶች
- የሴቶች ቀለማት - ነጭ ሐምራዊ እና አረንጓዴ
- «ሴቶችን የሚያማልሏቸው ስድስት ነገሮች»
- ጫት፣ ሙድ እና ወሲብ ምን አገናኛቸው?
- ኮረዳዋን ማን ገደላት?
- ፍቅረኛዎ የወሲብ ፍላጎት ባይኖራትስ?
- የሴቶች የወሲብ ፍላጎት ማጣት መንስኤዎች
- ታማኝ መሆን ይከብዳል?
- «… ድንግልናዬንማ በኮንዶም አላስረክብም!»
- ከወሲብ ጋር ለተያያዘ ችግርዎ መፍትሔው ምንድነው?
- ሕፃናቱን ከኤች.አይ.ቪ ለመታደግ

- ስለ ኤች.አይ.ቪ ዕውቀታችን የት ጋ ቆሟል?
- የሚስቱን ችግር ለመካፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ባል ማነው?
- በለጋ ወጣትነት ወሲብ መጀመርና ውጤቶቹ
- የ‹‹ፖርኖግራፊ›› እና የወሲብ ፊልም ውጤቶች
- እርግዝና ወሲብና ተያያዥ ጉዳዮች
- ማይክሮቢሳይድስ /Microbicides/
- ማይክሮቢሳይድ /Microbidcides/
- ‹‹የመኝታ ቤት ምስጢሮች››
- ‹‹መውለድ እፈልጋለሁ››
- ‹‹አለሁ አለሁ ብለሽ ብትለቃለቂ ባሌ ባል ላይሆንሽ ቁርጥሽን እወቂ!››
- ትዳርና ወሲባዊ ሕይወት
- መድረሻችን የት ይሆን?
- ‹‹የብልት ማደስ ሕክምና››
- የጡት ካንሰር የዘነጋነው ችግር
- ‹‹ባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው ብቻ የአእምሮ ጤንነታቸው ይጨምራል››
- ባልና ሚስት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንም ሊጋሩ ይችላሉ

# ላንቺና ላንተ

## ቅፅ 01

### አዘጋጆች

**ዋና አዘጋጅ**
ጻሃይ ተፈረደኝ

**ምክትል ዋና አዘጋጅ**
አዲሱ ደረሰ

**ኮፒ አርታኢ**
ሰላማዊትክፍሌ

**ከፍተኛ አርታኢዎች**
ፕሮፌሰር ሉከማን ዩሱፍ
ዶ/ር ሰለሞን ቁምቢ
ደ/ር እያሱ መስፍን
ዶ/ር እስክንድር ከበደ
ደ/ር አሸብር ጌታቸው
ደ/ር ገላኔ ሌሊሴ
ዶ/ር ገነት ገ/መድህን
ደ/ር ማቲያስ አስራት
ዶ/ር መሰረት አንሳ

# መግቢያ

የኢትዮጲያ ጽንስና ማህጸን ሃኪሞች ማህበር በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ የነበረውን የእናቶች ሞትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ እና ባጠቃላይ የሴቶች፤ የእናቶች እና ህጻናት እንዲሁም የስነተዋልዶ ጤናን በሃገሪቱ ለማሻሻል የተመሰረተ ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ ከተመሰረተበት ከ1984 አ/ም ጀምሮ ከሃገር በቀል እዲሁም ከሃገር ውጪ ካሉ ተቋማት ጋር በመተባበር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

ማህበሩ በቋሚነት ለረጅም ጊዜ ሲተገብራቸው ከነበሩት ፕግራሞቹ አንዱ በማህበሩ የኮሙኒኬሽን ክፍል እየተዘጋጅ ሲተላለፍ እና ሲነበብ የነበረው የላንቺና ላንተ የሬዲዮ ፕሮግራም እና የጋዜጣ አምድ ነው፡፡ የላንቺና ላንተ ፕሮግራም በሳምንት አንድ ጊዜ በመጀመሪያ በኤፍኤም አዲስ 97.1 ከዚያም በኢትዮጲያ ሬዲዮ ብሔራዊ አገልግሎት፤ በየሳምንቱ ለሰላሳ ደቂቃ ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡ ይህንኑ የሬዲዮ ፕግራም የሚደግፈው የጋዜጣ አምድ በተመሳሳይ ለባለፉት ከአስር አመታት በላይ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ሲነበብ ቆይቷል፡፡

የላንቺና ላንተ የሬዲዮ ፕሮግራም እና የጋዜጣ አምድ በስነተዋልዶ ጤና ላይ የማህበረሰቡን ችግር መሰረት በማድረግ እና የጤና ባሞያዎችን በማሳተፍ የተለያዩ ርዕሶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕግራሞችን እና ጽሁፎችን ሲያደርስ ቆይቷል፡፡

በዚህ የላንቺና ላንተ የአርካይቭ እትም ላይ በማህበሩ የኮምኒኬሽን ባለሞያ አበበ ተሻገር፤ ቤቴሌሄም ነጋሽ ተዘጋጅተው እና በአዲስ አድማስ አማካይነት ለማህበረሰቡ ሲደርሱ የነበሩ ጽሁፎችን ታነባላችሁ፡፡ እነዚህ የጽሁፍ ስብስቦች በጊዜ ውስጥ ውበታቸውም ሆነ ሳይንሳዊ ጥቅማቸው ያልሟሸሸ እንደመሆኑ ለአንባቢዎች ከፍተኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ምንጭ እንደሚሆኑ የማህበሩ አምነት ነው፡፡

# ሙያቸው የገባቸው ባለሙያ

አንዳንድ ባለሙያዎች ሙያቸውም ስነምግባሩም የገባቸው አሉ። በአንድ ትልቅ ሆስፒታል የሚገኙ የጽንስና ማህጸን ሕክምና ብቸኛ ስፔሻሊስት ሐኪም ናቸው። አካባቢው በርከት ላሉ እናቶች ሕክምና ስለሚሰጥ ውሎአቸውም አዳራቸውም እዛው ሆኖአል። በቀን ቢያንስ አምስት እናቶች ይወልዳሉ።ይህ ስራ የሳቸውና የሁለት ረዳት ነርሶች ስራ ነው።የቀዶ ጥገና ስራ በየቀኑ ይሰራል። ዶ/ር ወንድወሰን በለጠ በአምቦ ሆስፒታል 17ኛ ልጅ ለመውለድ የመጣች እናት አጋጥሟቸዋል። የኢትዮጵያ የጽንስና ማህጸን ሐኪሞች ማህበር (ኢሶግ)የእናቶችና ህጻናትን ሞት ለመቀነስ በሚያስችሉ ክሎቶች ላይ የተግባር ጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ይሰጣል።አምቦ ሆስፒታል ደግሞ ብዙ የተለያዩ የእናቶች ችግር ከሚታይባቸው ሆስፒሎች አንዱ ነው።

ስልጠናውን ለመስጠት ታዲያ የኢትዮጵያ የጽንስና ማህጸን ሐኪሞች ማህበር ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ ነርሶችን በተለይ የተግባር ሂደቱን በተጨባጭ እንዲያዩ ወደዚህ ሆስፒታል ጠርቶ ነበር። ይህን ስልጠና እየመሩ ነበር ባለሙያውን ያገኘሁዋቸው።ዛሬ የተለያዩ ልምዳቸውን ሊያወጉን ዶ/ር ወንድወሰን በለጠ ከእኛ ጋር ይገኛሉ።

ኢሶግ፡- መደበኛ ባልሆነ መንገድ ስናወጋ አንድ ጉዳይ አጫውተውኝ ነበር። ጥያቄየን በሱ ልጀምር። 17ኛ ልጅዋን ለመውለድ እዚህ አምቦ ሆስፒተል እርስዎ ስላገኙዋት እናት ይንገሩኝ።

ዶ/ር ወንድወሰን፡- አዎ እንዳልኩህ የዚህ አካባቢ የአምቦ እናት ፈርቲሊቲ (አንዲት እናት በአማካይ የምትወልደው ልጅ ቁጥር ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ አንዲት 17ኛ ልጅዋን ልትወልድ ደርሳ የመጣች እናት አጋጥማኛለች። 16/ወልዳ ማለት ነው። የመጣችውም ችግር ገጥሞአት ነው። 17ኛው ጽንስ አልወለድም ብሎ ማለት ነው። ከቆየችበት ጊዜ በላ ቆይታ ቢሆን ኖሮ ማህጸንዋ ተተርትሮ ልትሞት ትችል ነበር። እና እንደ እድል ሆኖ ከሩቅ ቦታ ነው ቶሎ መጣች። በሰላም አዋለድናት። በሁዋላም ከእሱዋው ጋር ተስማምተን ከአሁን በሁዋላ አልወልድም ስላለች ማህጸንዋ ተቋጠረ።

አምቦ ለመታከም ህሙማን ከብዙ ወረዳዎች ይመጣሉ። እና እዚህ አካባቢ 10፤12፤14፤ ልጆችን መውለድ የተለመደና በተደጋጋሚ የሚገጥመን ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ታዲያ የእናቶች ሞት መጠን እየጨመረ ይሄዳል።

ሌላው በዚሁ አካባቢ የሚታየው ደግሞ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ጽንስ ማቋረጥ አሰርተው ብዙ ሴቶች ይመጣሉ። የሚገርመው ከኢህ ከአምቦ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ካሉ ገጠር አካባቢዎች ሁሉ ተነካክተው ይመጣሉ። ህጻናት ገና የራሳቸውን እድገት ሳይጨርሱ አረ ገና ሳይጀምሩ የመጀመሪያ የወር አበባ ሳያዩ ተደፍረው አርግዘው ይመጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ እዚህ አካባቢ የሚታየው ከማህጸን ውጭ እርግዝና ነው። በተደጋጋሚ እዚህ አምቦና ከአካባቢው እናቶች በዚህ ችግር ይመጣሉ። ለምሳሌ ባለፈው 26/ እና 27/ የሚሆኑ እናቶች ቀዶ ጥገና ተሰርቶላቸው ሄደዋል።

ጥያቄ፦ ከማህጸን ውጭ የተረገዘ ልጅ ለመወለድ ይደርሳል

ዶ/ር፦ አይ እርግዝናው የሚፈጠረው ማህጸን ውስጥ መሆን ሲገባው እንቁላል ከሚመረትበት ኦቫሪ ወደ ማህጸን ዘር መተላለፊያ ቱቦ (ፋሎፒያን ቲዩብ) ውስጥ ይሆናል። ይህ የዘር መተላለፊያ ቱቦ ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ጽንሱ እያደገ ሲሄድ መሸከም ያቅተውና ይፈነዳል። ያኔ ነፍሰ ጡርዋ ትደማለች። ስለሚያማቸውም ወደ ሆስፒታል ይመጡና በቀዶ ጥገና ይታከ ማሉ። ከዚህ ውጭ ግን አንዴ የተለየ ነገር ገጥሞኛል። ጽንሱ በተገቢው ቦታ በማህጸን ውስጥም ወይም ደግሞ ይናል ብለን በምንገምተው በዘር ማስተላለፊያ ቱቦ ውስጥ አይደለም የተቀመ ጠው። እርግዝናው ከማህጸን ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው ሆዷ ውስት አድጎአል።ልጇ የተጣበቀው የታችኛው የአንጀት ክፍል ደንዳኔ ላይ ነው። በራሱ መሸፈኛ ሆድ ውስጥ ቁጭ ብሎ አገኘነው። ሴት ነች። ሰባት ወራት ሆኖአታል። 900/ግራም ትመዝናለች። የጭንቅላትዋ ቅርጽ ትክክል አልነበረም። እግርዋ ጠማማ ነበር። ካዋለድናት በሁዋላ ህጻንዋ 36/ሰአት (አንድ ቀን ተኩል) ቆይታ ሞተች። እናት በጤና ወደቤት ተመልሳለች።

ጥያቄ፦ በዚህ በአምቦ ሆስፒታል የማህጸንና ጽንስ ክፍል በአጠቃላይ እለት እለት ያለው የስራ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል

ዶ/ር፦ በሶስት ክፍል የሚታይ ነው። የተለያየ ችግር ያለባቸው በመኝታ ክፍል ተኝተው የሚታከሙ አሉ። በአመት እስከ 1500/እናቶች እናዋልዳለን። ከዚህ ውስጥ ከመቶ 12 እጅ በቀዶ ጥገና የምናዋልዳቸው ናቸው። ከመቶ 10 እጅ ደግሞ በተለያዩ መሳሪያዎች እገዛ ይወልዳሉ ። ቀሪዎች በተለመደው መንገድ አምጠው የሚወልዱ ናቸው። በቀን 4/እና 5/ሴቶችን እናዋልዳለን።

ሌላው ክፍል (ኦፒዲ) የተመላላሽ ሕክምና ክፍል ነው። በዚህ የተመላላሽ ክፍል በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በተለይም በማህጸንና በማህጸን እጢ ችግሮች ምክንያት የሚመጡ እናቶችን እናያለን። በየቀኑ ከ10-15 ሕሙማንን እናያለን። እዚህ ክፍል ውስጥ ከምናያቸው በሳምንት ከ4-6 ለሚሆኑ እናቶች ቀዶ ጥገና እንሰራለን።

በየቀኑ ከጽንስ ማቋረጥ ችግር ጋር በተያያዘ የተለያየ ችግር ገጥሞአቸው አንድ ወይንም ሁለት ሴቶች ይመጣሉ። ለእነዚህ የተሟላ እርዳታ ለማድረግ እንሞክራለን።
ማክሰኞና ሐሙስ እኔ ቀጠሮ የተያዘላቸውን ከ40-50 የሚደርሱ ህሙማን አያለሁ።
ሌላኛውና ሶስተኛው ክፍል ኤችአይቪ ከእናት ወደልጅ እንዳይተላለፍ አገልግሎት የምንሰጥበት ይህ አሁን ያለንት ክፍል ማለት ነው አለን።በዚህ ክፍል ደግሞ የኤችአይቪ ምርመራ እና የምክር የክትትል ስራ ይሰራል።
ጥያቄ፦ ምን ያህል ባለሙያዎች አላችሁ በዚህ በማህጸንና ጽንስ ሕክምና ክፍል
ዶ/ር፦ እኔ አለሁ። የማህጸንና ጽንስ ሕክምና እስፔሻሊስት። አንድ ከፍተኛና ጀማሪ አዋላጆች አለን።
ጥያቄ፦ ከዚህ አኩዋያ ታዲያ ጥራት ያለው ሕክምና መስጠት ይቻላል
ዶ/ር፦ እ....እ....እ....እዚህ ላይ ከበድ ይላል። 75/በመቶ የሚደርሱ ስራዎች የሚሰሩት በድንገት ነው። ቀዶ ጥገና ብዙ ጊዜ በሌሊት ነው የሚሰራው። የምጥና የወሊድ ነገር ብዙ ጊዜ ለሊት ይበዛል። ውርጃ አጋጥሞአቸው ወይንም ተነካክተው ፤የማህጸን መተርተር፤ምጥ ተራዝሞባቸው ለሊት ይመጣሉ። ያን ጊዜ ለሊት እንሰራለን።
እንደገና ቀን ደግሞ ሌላ ቀዶ ጥገና እሰራለሁ። ባለን ኃይል ለእያንዳንዱ ሕሙማን ጊዜ ሰጥቶ መስራት ቻላል ማለት ይከብዳል። ወደ ተመላላሽ ሕክምና ከሩቅ ወረዳዎች የሚመጡ እናቶች አሉ። ያለሁት እስፔሻሊስት ሐኪም እኔ ነኝ። እነዚህ እናቶች ችግራቸው ከፍ ያለ ይሆንና ወደ እኔ ይመራሉ። በእኔ ለመታየት ደግሞ ማክሰኞን ወይንም ሐሙስን መጠበቅ አለባቸው። ጥራት ያለው ሕክምና ስንል ችግራቸው በጊዜ ተለይቶ ሳይጉላሉ በወቅቱ ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግና እረፍት እንዲያገኙ ማድረግን ሁሉ ያጠቃልላል። ሆኖም በዚህ ኃይል ጥራት ያለው ደረጃውን የጠበቀ ሕክምና ማድረግ አይቻልም። የምንሰራው የምንችለውን ያህል እንጂ የተሟላና ጥራት ያለው ሕክምና አስቸጋሪ ነው።
ጥያቄ፦ ወደፊት ስራዎን በዚሁ አይነት እዚሁ ይቀጥላሉ
ዶ/ር.....ብዬ አስባለሁ። የሚያግዝ ባለሙያ ቢገኝ ጥሩ ነው።
ጥያቄ፦ ቤተሰብ እዚሁ አምቦ ናቸው
ዶ/ር፦ .....አዎን ባለቤቴም አንድ ልጅ አለኝ እዚሁ አምቦ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ነው የምንኖረው። ለድንገተኛ ስጠራ እንድቀርብ ሆስፒታሉ መኖሪያ እዚሁ ግቢ ውስጥ ሰጥቶኛል።
ጥያቄ፦ ድንገተኛ ሕሙማን ይበዛሉ
ዶ/ር፦ ..... በጣም ይበዛል። ለሊት ቀዶ ጥገና በድንገተኛ ሰርቼ ቀን ደግሞ እንደገና

እሰራለሁ።ሁሌ ንቁ ሆነህ ነው የምትተኛው ። እንደሌላው ራስህን ጥለህ ሰላም ሆነህ አትተኛም። በማንኛውም ሰአት ልትጠራ ትችላለህ። በተለይ ከእናቶችና ከወሊድ ጋር የተያያዘ ነገር ጊዜ ሊሰጠው የሚችል ነገር አይደለም። ለጠዋት ሲነጋ ይቆየኝ አትልም። የግድ መጥተህ ማየት አለብህ። ያው የሚፈጥርብህ ያለመመቸት ሁኔታ አለ። ግን ሰው የማይለምደው ነገር የለም። ትለምደዋለህ፡ ፡ ሣቁ።

## «ለህይወት መዳን ምክንያት እሆናለሁ ብዬ ነው የማስበው»

ወጣት የህክምና ባለሞያ ስትሆን የጽንስና የማህፀን ስፔሻሊስት ነች። ዶ/ር ሊያ ታደሰ። ባለፈው የኢትዮጵያ የጽንስና የማህፀን ሀኪሞች ማህበር 15ኛ አመታዊ ጉባዔ በተካሄደበት እለት ወጣት ባለሞያዎችን ወክላ ለመንግስት መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ለባለሙያዎችና ለማህበሩ ጠንከር ያሉ መልእክቶችን አስተላልፋ ነበር። እነዚህ መልእክቶች የጤና ባለሙያዎች በተለይ ደግሞ የጽንስና የማህፀን ስፔሻሊስቶች በአዲሱ ሚሊኒየም የእናቶችንና የህጻናትን ሞት ለመቀነስ በአጠቃላይም በሥነ ተዋልዶ ጤና የተሻሉ ለውጦችን ለማየትና ለማሳየት መደረግና መሟላት አለባቸው ተብለው የሚታሰቡ ሁኔታዎችን ከወጣት ባለሙያዎቹ አንፃር አንስታ አቅርባለች። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአንክሮ እንደሚያጤነውም ተጠቁሟል። እኔም ከዶ/ር ሊያ ጋር አጠር ያለ ጊዜ ወስጄ ቃለምልልስ አድርጌአለሁ።

ጥያቄ፦ በቅድሚያ ላነሳልሽ የምፈልገው ጥያቄ ብዙ ጊዜ ሴቶች ሴቶችን የበለጠ ሊረዱና ሊያክሙበት ወደሚያስችላቸው የጽንስና የማህፀን ህክምና ስፔሻሊያዜሽን ትምህርት ገብተው ሲማሩና በሥራው ሲሠማሩ አይታይም ለምንድን ነው?

ዶ/ር ሊያ፦ አዎ ልክ ነው። በአጠቃላይ የሴት ሀኪሞች ቁጥር አናሳ ነው። እንደገና ደግሞ ወደ ህክምና ትምህርት ገብተው ከተማሩት ጠቅላላ ሀኪሞች (Generala Practitioners) ውስጥ ወደ ጽንስና የማህፀን ስፔሻላይዜሽን ፕሮግራም የሚመጡ የሴት ሀኪሞች ቁጥር ደግሞ በጣም አነስተኛ ነው። እንደኔ አስተሳሰብ የዚህ ዋና ምክንያቱ የሚመስለኝ ሥራው እጅግ በጣም አድካሚ መሆኑ ነው፣ ሙያው በተለይ ከወሊድ ጋር የተያያዘ መሆኑ ደግሞ አድካሚነቱን ያብሰዋል። ከወሊድ ጋር መያያዙ ሥራው ሰዓት (ጊዜ) ሳይመረጥበት የሚሠራ በመሆኑ አድካሚ ያደርገዋል። በዚህ ይሆናል እንግዲህ ወደ ሌላ ፊልድ የሚገቡትና በዚህ ሙያ ያለነው የሴት ሀኪሞች ቁጥር ያነሰው።

ጥያቄ፦ እናቶች የእርግዝና ጊዜያቸውን ጨርሰው በወሊድ ጊዜ ከጭንቀታቸው መገላገል መቻል እሰደሳች ቢሆንም በሥራው ሂደት ያለው አስቸጋሪ ሁኔታ ምንድን ነው ?

ዶ/ር ሊያ፦ በእኛ ሀገር ከመውለድ ጋር ያለው ህክምና ያለመዳረስ ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ በተለይ በገጠሩ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ይታወቃል። አንዲት እናት ምጥ መጥቶባት ህክምና ልታገኝ ካልቻለች እስከሞት የሚያበቋት ችግሮች ያጋጥሟታል። ህክምና ብታገኝ በሰላም መገላገል እና የልጅ እናት መሆን የምትችል ሴት ስትሞት ያሳዝናል። በቀላሉ ልጇን መውለድ ስትችል ህክምና ካለማግነት ብቻ የምትሞት እናት በጣም ታሳዝናለች። ከዚህ ሌላ ደግሞ የኛ የባለሙያዎች ቁጥር ደግሞ አለ። በጣም አነስተኛ ነው። በሚገባን ደረጃ ለመሥራት ደግሞ የጤና ተቋማት አለመኖርና የጤና ተቋማት ደግሞ በበቂ መሣሪያዎች (Material) አለመሟላት ሌላው ችግር ነው። በአጠቃላይ የሥነ ተዋልዶ ችግሮች፣ አንዲት እናት መውለድ ሳትፈልግ የመውለድ ሁኔታ፣ የእርግዝና መከላከያ ያለማግኘት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ሴቶች በራሳቸው አለመወሰናቸው፣ ተገዶ መዳር፣ መጠለፍን እንዲሁም በቤተሰብ ጉዳይ የውሳኔ አካል አለመሆናቸውና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ የሚያጋጥሙን ችግሮች ናቸው።

ጥያቄ፦ 15ኛው የኢትዮጵያ የጽንስና የማህፀን ሃኪሞች ማህበር አመታዊ ጉባዔ ሲካሄድ አንዷ ተናጋሪ አንቺ ነበርሽ የንግግርሽ ዋና ነጥብ ምን ነበር ?

ዶ/ር ሊያ፦ እኛ እንደባለሙያ ልንሰጠው የምንፈልገው (ሰርቪስ) አገልግሎት እና ልናየው የምንፈልገው፣ ልናመጣው የምንችለው ለውጥ አለ። በተለይ በእናቶች በአጠቃላይ በሥነ ተዋልዶ ጤና ላይ ለውጥ ማየት እንሻለን። ሆኖም ባለሙያው ይፈልሳል። ነገር ግን እነዚህ የሚፈልሱ ባለሙያዎች የሚፈልሱት ማገልገል ስለማይፈልጉ ብቻ አይመስለኝም። ይልቅስ ለመሥራት ሚያስችል ሁኔታ (atmospher) እና ለሥራው ተመጣጣኝ የሆነ ነገር ያለመኖሩ ይመስለኛል። ባለሙያው እንዳይሠራ የሚያደርጉ ምክንያቶችን ደግሞ ከስር ማየት ያስፈልጋል። መፍትሔ መስጠት አለብን። ብዙዎቻችን እዚህ መሥራት የምንፈልግ ይመስለኛል። ለምሳሌ እኔ እዚህ አገር የምኖረው በምርጫዬ በፍላጎቴ ነው። እዚህ ብኖር ለውጥ አመጣለሁ። ለህይወት መዳን ምክንያት እሆናለሁ ብዬ ነው የማስበው። ብዙዎቹም ይህን የሚጋሩኝ ይመስለኛል። መንግስት በጤና ባለሙያ ላይ በተለይ ጫና የሚያደርግ ይመስለኛል። በጫና

ባለሙያው ራሱን ሰጥቶ እንዲሠራ ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም። አሁን እየወጡ ያሉ ነገሮች አሉ። የዝውውር ሁኔታ ዲግሪ ያለመስጠት፣ የሚሉና ሌሎችም መመሪያዎች ይሰማሉ። ይሄ ብቻውን ግን የሚሠራ አይመስለኝም፡ ፡ ይልቅስ እንዴት ባለሙያው በተገቢ ሁኔታ እንዲሠራ ማድረግ ይቻላል? የሚለው ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

የጤና ባለሙያው ደግሞ ሀገሪቱ ከምትችለው በላይ የሆነ ነገር የሚጠይቅ አይመስለኝም። የሀገሪቱን አቅም እናውቀዋለን። ለምሳሌ የጽንስና የማህጸን ሃኪሞች ብዙ ጊዜ ከደም ጋር ንክኪ ያለው ሥራ ነው የምንሰራው። አሁን ኤች አይ ቪ አለ። ሌሎችም እንደ ሄፐታይተስ ያሉ ተላላፊ በሽታዎች አሉ፡ ፡ ስለዚህ የህይወት ዋስትና (Life Insurance) ያስፈልገናል። የህግ ከለላ ያስፈልገናል። ሌላው ለጤናው ሴክተር በቂ በጀት አይደለም የሚመደበው። ይህ ሊታሰብበት ይገባል። የጤና ተቋማት ሊገነቡ ይችላሉ። ሆኖም በጤና ተቋማቱ ውስጥ በቂ ማቴሪያሎች ወይም መሣሪያዎች ከሌሉ ሥራ መሥራት አይቻልም። አንድ ሃኪም አንድ ጤና ተቋም ተመድቦ ሄዶ መሳሪያ በማጣት ብቻ አንዲት እናት እያያት ከሞተችበት ተስፋ ይቆርጣል (Frustrate) ያደርጋል ስለዚህ ሊሸሽ ይችላል።

እኛ ደግሞ እንደባለሙያ ከፊታችን የተጋረጡ ብዙ ችግሮች ሊኖሩብን ይችላ። ቁጥራችን ደግሞ ከመነሻውም ዝቅተኛ ነው። በሀገሪቱ በሞላ ያለውን ፍላጎት ማርካት አንችል ሆናል። ነገር ግን ተስፋ ከመቁረጥና ከመሸሸ ለውጥ ለማምጣት ሥራችንን ግዴታ አድርገን መውሰድና መስራት ይኖርብናል።

ጥያቄ፡- ቀደም ሲል እንደገለጽሽው በተለይ በገጠር በርካታ እናቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ ህክምና አጥተው ይሞታሉ። ባለሞያዎች ደግሞ ከተማ በተለይ አዲስ አበባ የመከማቸት ሁኔታ ይታያል። ለምሳሌ እኔ በቅርቡ ባየሁት በአምቦ ሆስፒታል ለ1.2 ሚሊዮን ሰዎች አገልግሎት በሚሰጥ ሆስፒታል ውስጥ ያሉት አንድ የጽንስና የማህፀን ሃኪም ናቸው። እንደወጣት ባለሞያ ምን አስተያየት አለሽ?

ዶ/ር ሊያ፡- በአጠቃላይ ቅድም እንደነገርኩህ የሃኪም ቁጥር ትንሽ ነው። የጤናውን ፍላጎት (demand) ማሟላት አይችልም። ዋናው የጤና

ተቋማቱ አለመኖር ሁኔታና ቢኖሩም እንኳ የመሣሪያዎች ያለመሟላት ሁኔታ አለ። ሆኖም ግን ባለሙያው ቢያንስ የተወሰነ ጊዜ ከከተማ ወጥቶ (በገጠር) መሥራት ያስፈልጋል። ገጠር ሄዶ የሚሠራው ግን ከተማ ካለው የተሻለ ቢያገኝ ጥሩ ነው እላለሁ።

ጥያቄ፦ /ንግግሯን አቋርጬ ገብቻለሁ/ በተሟላባቸው ቦታዎችስ ለምሳሌ ሌላ ያየሁት የላሊበላ ሆስፒታልን ነው። የተሟላና ደረጃውን የጠበቀ ነው። ግን የማህፀን ሃኪም አይደለም በአጠቃላይ ሃኪም የለም...

ዶ/ር ሊያ፦ /አቋርጣኝ ገብታለች/ ሊሆን ይችላል። ሆስፒታሉ የተሟላ ሆኖ በአካባቢው ያለው የሥራ ሁኔታ ያለመመቸት ደግሞ ሊኖር ይችላል። ከዚሁ አንጻር ሃኪሙ እዚሁ (በከተማ) ሊቀር ይችላል።

ጥያቄ፦ የሀገሪቱ የእድገት ደረጃስ ሁሉም ነገር ሁሉም ቦታ ተሟልቶ ይገኛል?

ዶ/ር ሊያ፦ አዎ ከእኛ ከባለሞያዎች የሚጠበቅ አለ ያልኩትም ይሄን ነው። የሞራል ግዴታን መወጣትና ችግርም ቢኖር ተቋቁሞ መስራት ይኖርብናል።

አመሰግናለሁ።

# የሴት ልጅ ሶስት የስቃይ ምዕራፎች

-ወንድ ልጅን ብልትህን እቆርጥብሃለው ብትለውስ?
-የትኛውም ሃይማኖት የሚፈቅደው አይደለም
-ቢደረግ ጥሩ ነው የሚባልበት የህግና የጤና መሠረት የለም፣
-ብልጅነትህ ጆሮህን የቆነጠጠህን እንዴት ትረሳዋለህ?

አንድ አሰቃቂ ድርጊት ወይም አጋጣሚ ተከስቶ ሁኔታው ካለፈ በኋላ ሲያወሩት ልዩነቱ በእጅጉ ሰፊ ነው። የድርጊቱን እጅግ አነስተኛ ገጽታ ብቻ ነው ወሬው ወይም ፁሁፉ የሚገልጸው። ሲወራ ቀላል ድርጊቱ ሲከወን ግን እጅግ ግዙፍ የሆነ ብዙ ጉዳይ አለ።

ሴቶች ልጆች በህይወት ዘመናቸው ሦስት የስቃይ ምዕራፎችን ያልፋሉ። አንዱ በመጀመሪያ ሲገረዙ፣ ሁለተኛው ይህች የተገረዘች እህት ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲባዊ ግንኙነት ስትፈጽምና በኋላም ስትወልድ ነው ይባላል። በስቃይ እግርና እጇ ተይዞ አይኗ ታፍኖ አካሏ ይተለተላል። ይቸው ህፃን በኋላ እናት ስትሆን ሴት ልጇን ይዛ እንደገና ታስገርዛለች።

ብልት አካባቢ ትላልቅ የደም ሥሮች አሉ። ያውም ደም የሚያመጡ /artries/ እነዚህ ሥሮች በግርዛት ሳቢያ ከተነኩ ያች ልጅ ከባድ ውስብስብ ችግር ውስጥ ትገባለች። በደም መፍሰስ የተነሳም ግርዛት እስከ ሞት ሊያደርስ ይችላል። በድርጊቱ ሳቢያ የሚኖረው ህመምና ስቃይ ህፃናቶቹ የሚቋቋሙት አይደለም። በዚሁ ምክንያት የሽንትና የብልት መስመር ተጥሶ ለፌስቱላ ልትዳረግ ትችላለች፡ ፡ ለተለያዩ ቁስለቶች /infections/ ይጋለጣሉ /የፊኛ፣ ሽንት መቋጠርና አጠቃላይም የመሽናት ችግር፣ በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም፣ በወሊድ ጊዜ ስቃይ፣ የወር አበባ በቀላሉ ያለመውረድና ከፍተኛ የህመም ስሜት የመሳሰሉት ሁሉ ከሴት ልጅ ግርዛት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ናቸው/ የእርስዎ ልጅ የዚህ ሁሉ ስቃይ ተቀባይ ትሆን? የት ይቀርላታል። በሀገራችን 72 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች የተገረዙ ናቸው። አብዛኛዎቹ ማለት ነው። በግርዛቱ ልዩነት አይነት ስቃዩ ሊበዛም ሊያንስም ይችላል እንጂ አብዛኞቹ ሴቶች የሚጋሩት ተመሳሳይ ህመም አለ። የግርዛት አይነት በአቢይነት በአራት ምድብ /type/ የሚታዩ ናቸው።

እነዚህ ቀላል ከሚባለው ከመጀመሪያው ደረጃ የሴቶችን ብልት እስከመተልተል /መዝጋት/ ደረጃ የሚደደርሱ ናቸው፡፡
በመጀመሪያ ደረጃ የሚመደበው ከላይ ያለውን ሽፋን በእንግሊዝኛ /clitories/ ተብሎ የሚጠራው ወይም የሴቶች የወሲብ ስሜት እንዲቀሰቀስ የሚረዳውን ሽፋን ወይም የሴትነት መለያዋን ሽፋኑን የማንሳት ወይም ራሱን የመቁረጥ ሁኔታ ነው፡፡
ሁለተኛው ደግሞ ይህንኑ ክሊቶሪስ Clitories ሙሉ በሙሉ እና የሴትዋን ብልት ከንፈር አብዛኛውን ወይም በጠቅላላው ያነሱታል፡፡
ሦስተኛው የውጪውን የሴቷን ብልት ከንፈር ሙሉ በሙሉ፣ ከላይ እስከታች እንዲነሳ ይደረጋል /infibulation/ በዚህም ብልቱን በመስፋት ለማጥበብ ይሞከራል፡፡ ይሄ ከፍተኛ ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ ለብዙ ህመም የሚያጋልጥ ነው፡፡ ይህ የግርዛት አይነት ግራና ቀኝ ያለው ክፍል ተጣብቆ እንዲዘጋ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ይህ የግርዛት አይነት በሱማሊያና አፋር ክልሎች በብዛት የሚታይ ነው፡፡
አራተኛው ምድብ ደግሞ በመርፌ /ወይም በተለያዩ ስለቶች/ ግራና ቀኙን ተልትሎ፣ ቆርጦ ወይም አቃጥሎ መዝጋት ወይም ከንፈሩን የመለጠጠት የማስረዘም ሁኔታ ይኖራል፡፡ ምንም አይነት ወሲባዊ ግንኙነት እንዳይደረግና ለወሲብ እንዳይጋብዝ የማድረግ ነው አላማው፡፡ በዚሁ ግርዛት ስም የሚፈጸሙ በርካታ ድርጊቶች በተለያዩ የአለም ክፍሎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ የሴቶች ብልት ውስጡ ተቧጦ እንዲቆስል ይደረጋል፡፡ ይህም እንዲጠነክርና እንዲጠብ በሚል የሚሠራ ነው፡፡ አሁንም በተመሳሳይ እውስጡ የሚያቃጥል ኬሚካል ወይም ቅጠላ ቅጠል ሌላም ሌላም ነገር በመጨመር ለማጥበብ የሚሞከርበት ሁኔታ አለ፡፡
የግርዛት አይነቶቹ ከመጀመሪያው ሁለተኛው፣ ከሁለተኛው ሦስተኛው፣ እየከፋ ስቃዩም እየጨመረ በጤና በኩልም የበለጠ ውስብስብ ችግር እየፈጠረ የሚሄድ ነው፡፡ ይህ የሴቶች ግርዛት ለምን እንደሚደረግ የተገረዙት ሴቶች በውል የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ አብዛኞቹ የሚያስታውሱት ስቃዩን ነው፡፡ የሴቶች ግርዛት የሚካሄደው በዚህ እድሜ ነው የሚል ገደብ የለውም፡፡ በአንዳንድ

አካባቢዎች ገና አራስ ቤት/ እንደተወለደች/ ልትገረዝ ትችላለች፣ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ እድሜያቸው ሰባት፣ ስምንት፣ 13 ወይም ሊያገቡ ሲሉ፣ አንድ ከወለዱ በኋላ በድጋሚ የሚገረዙበት ሁኔታ ሁሉ እንዳለ ይታያል፡፡ መነሻ ምክንያት ሆነው በአቢይነት እናቶች ሲገልጹ የሚሰሙት የሴቶቹን ጸባይ ለመግራት፣ እንዳይንቀዠቀዡ፣ የንጽህና ወይም የድንግልና መገለጫ፣ ከልጅነት ወደ አዋቂነት መሸጋገሪያ በሚሉና ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ተያይዞ የሴቶች ብልት ትልተላ ይካሄዳል፡፡

የሚገርመው ነገር ብዙውን ጊዜ ይሄን ሥራ የሚሠሩት /የሚገርዙት/ አሮጊት እናቶች ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው የማንኛው ሰው አይን እድሜ በጨመረ ቁጥር /በመነፅር በሌሎች ህክምናዎች ካልታገዘ/ የማየት ብቃቱ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ከዚህ ሌላ የሰውነት አቅም /የእግር የእጅ/ እየቀነሰ፣ እየፈዘዘ ወይም ጡንቻ እየዛለ ይሄዳል፡፡ በመሆኑም አሮጊት እናቶች በዚህ ሁኔታ ላይ ሆነው ግርዛቱን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከገመቱትና እነሱ ትክክለኛ ግርዛት ነው ብለው ካሰቡት /ትክክለኛ የሚባል ግርዛት አይነት ባይኖርም/ ካሰቡት ውጭ የመቁረጥ የመተልተል /አጋጣሚ አላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት የደም መፍሰስና የሞት አደጋ ሊከተል ወይም በሴቶች ላይ የእድሜ ልክ ጠባሳ ሊቀር ይችላል፡፡...

ይህ የግርዛት ሂደት የሚካሄድው በትግል፣ በጉልበት ወይም በማስገደድ ነው፡፡ የሴቷ /የህፃኗ/ እግርና እጅ በጉልበት ተወጥሮና ታስሮ፣ እያለቀሰችና ዋይታ እያሰማች፣ በሌላት አቅም ሁሉ እየታገለች፣ ያለምንም ማደንዘዣ ነው የሚሠራው፡፡ በዚህ ጊዜ ሊኖር በሚችለው ትግልና እንቅስቃሴ ምክንያት ከተገመተው ወይም ከተፈለገው ውጪ ሊቆረጥ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሚደርሰው ህመም፣ ቁስለትና ስቃይ ጥሎት የሚያልፈው የመንፈስ ጭንቀት በስነልቦናዋ ላይ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል፡፡

እንኳን በምላጭ /ስለት/ መተልተል ይቅርና በልጅነት ጆሮአችንን ድብን አድርገው የቆነጠጡንን ወይም የገረፉንን አእምሯችን በቀላሉ አይረሳም፡፡ ግርዛቱ ጥሎት በሚየያልፈው ጠባሳ ምክንያት ስነልቦናቸው የተረበሸ ይሆናል፡፡ ወሲባዊ ግንኙነት ሊያስፈራቸው፣ ለዚህ ያላቸው አመለካከትም የተሳሳተ ሊሆንና ወንድ ጋር ላይቀርቡ ይችላሉ፡፡

የወሲባዊ ግንኙነቱን ጉዳይ ካነሳን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በግርዛት ሳቢያ ብዙ ጊዜ ጥቃት የሚደርስበት ክሊቶሪስ /ስሜት እንዲቀሰቅስ የሚረዳው የብልት ክፍል/ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቷ ለወሲብ ያላት ፍላጎት የቀነሰ ወይም ጭራሽ ስሜቱ የሌላት ልትሆን ትችላለች፡፡ በዚህ በተቆረጠው የስሜት አካልና በአካባቢው ከሚነካው ነርብ ጋር በተያያዘም ወሲባዊ ግንኙነት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ህመም ስለሚሰማቸው /የመገረዙን ያህል ህመም ሊሰማቸው ስለሚችል/ ጨርሶ ወሲባዊ ግንኙነትን ሊጠሉ ይችላሉ፡፡
ይህች እህት በሆነ አጋጣሚ ያልተፈለገ እርግዝና ቢፈጠርባትስ? ሌላው ግርዛት የሚያስከትለው ሰቆቃ የሚታይበት ማዕዘን ይህች እህት ህጉ የሚፈቅድላት ሆኖ ፅንሱን ልታቋርጥ ብትፈልግና አሊያም በራሱ ጊዜ ቢወርድ፣ እንደገና ስትገረዝ በነበረው ደረጃ ስቃይ ውስጥ ትገባለች፡፡ ተፈጥሮ በመጀመሪያ አስተካክሎ የፈጠረው አካል በነበረበት ስለሌለ በባለሞያው በተገቢው መንገድ መሣሪያ በማስገባት ለመጥረግ አዳጋች ይሆናል፡፡ አግብተው ልጅ ለመውለድ ሲፈልጉ እንኳን የግርዛቱ አይነት ታይቶ አንዳንዶቹን በቀላሉ ስቲች /ቀላል ቀዶ ጥገና/ በመስራት ማዋለድ ሲቻል ብዙዎቹን ግን ከላይ ከሆዳቸው በኩል ቀዶ ጥገና በመሥራት ማዋለዱ የሚቀልበት ብዙ አጋጣሚ እንዳለ ባለሞያዎቹ ይገልጻሉ፡፡ ባለሞያና የህክምና ጣቢያዎች በሌሉበት አካባቢ ከሆነ ግን ፅንሱ /ልጁ/ በቀላሉ መውጣት አይችልም፡፡ ምጡ ረዥምና ከባድ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ፅንሱ የመታፈንና እዚያው የመሞት እድል ሊገጥመው ይችላል፡፡
የተገረዘች እህት የወር አበባ የማየት እድሜ ላይ በምትደርስበት ጊዜስ? ከብልቷ ጋር የተያያዙ ማናቸውም ነገሮች ስቃይ አሉባቸው፡፡ የወር አበባ በየወሩ በሴቶች ላይ የሚታይ ክስተት ነው፡፡ ይህ ፈሳሥ በቀላሉ ለመውረድ መውጫ ቧንቧ ስለሚጠብበት ወይም ስለሚዘጋበት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይወጣ በመቅረት ውስጥ የመጠራቀም እድል ይኖረዋል፡፡ ከተጠራቀመ ደግሞ የባክቴሪያ ጥሩ መራቢያ ይሆናል፡፡ በዚህም ለተለያዩ በሽታዎች ትጋለጣለች፡፡ ከዚህ በተጨማረም የተገረዙ ሴቶች በወር አበባ ወቅት ከሌሎች በተለየ ህመሙ ይጸናባቸዋል፡፡ ምክንቱም የወር አበባው በተገኘው መንገድ እንደተፈለገ ስለማይወጣ ነው፡፡

ሌላው ወደመጨረሻ የምንመለከተው የኤች. አይ. ቪን ጉዳይ ነው፡፡ ግርዛት ብዙ ጊዜ የሚፈጸመው የግንዛቤ ደረጃቸው ዝቅ ባለባቸው የገጠር ክፍሎች ነው፡፡ ግርዛቱ ደግሞ በምላጭ /በተለያዩ ስለት ነክ ነገሮች/ የሚሠራ ነው፡፡ በእድሜያቸው ተመሳሳይ የሆኑ ህፃናቶች በተራ በአንድ ስለት የመግረዝ ሁኔታ ደግሞ የተለመደ ድርጊት ነው፡፡ በዚሁ ጊዜ ታዲያ ኤች. አይ. ቪን ጨምሮ ሌሎች በደም የሚተላለፉ በሽታዎች የመተላለፍ እድላቸው ሰፊ ይሆናል፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊትና ድርጊቱን ተከትሎ የሚታየው ስቃይና መዘዝ ለወንዶች ሲባል የሚፈጸም ነው፡፡ ከበላይነቱ ስሜትና ሴቶችን የበታች አድርጎ ለመያዝ ሲባል የሚፈጸም ነው፡፡ ሰብአዊ መብትን ተጋፍቶ፣ አካሏን ተልትሎ፣ ስሜቷን በመግደል ተገዢ ከማድረግ የበላይነት ስሜት ጋር ተያይዞ እንደሚፈፀም ይታወቃል፡፡

በሃገራችን ቀደም ባሉት ጊዜያት 95 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች የተገረዙ ነበሩ፡፡ የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች ከተደረገ በኋላ ደግሞ ወደ 85 በመቶ ዝቅ ማለት ጀመረ፡፡ ብዙ ቅስቀሳና ትኩረት ተሰጥቶበት የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ ደግሞ አሁንም የጠብታ ያህል ቀንሶ ወደ 72 በመቶ የሚሆኑት የተገረዙ እንደሆኑ ይታያል፡፡ ውጤቱ እዚህ ግባ ባይባልም የመቀነሱ ሁኔታ ግን መልካም ይመስላል፡፡

እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ አንድ ጉዳይ ታወሰኝ፡፡ በአንድ ወቅት በጎረቤት ሀገር ኬንያ ናይሮቢ በአንድ ትልቅ ስብሰባ ላይ (የሥነጾታና የሥነተዋልዶ መብትን በተመለከተ) አንዲት ወ/ሮ አንድ ጥናት ያቀርባሉ፡፡ እመቤቲቱ ሙሉ የአበሻ ቀሚስ ለብሰዋል፡፡ በቅድሚያ ራሳቸውን አስተዋወቁ ወ/ሮ ማርታ ተሾመ ይባላሉ፡፡ በአውስትራሊያ ጤና ጥበቃ የህፃናትና ማህበረሰብ ጤና ዳይሬክቶሬት ናቸው «የመጣሁት ከአውስትራሊያ ነው፡፡ የጥናቴ ትኩረት ደግሞ በአውስትራሊያ ስላለ የሴቶች ግርዛት ልምድን ይመለከታል» አሉ፡፡ ታዳሚዎቹ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተገኙ ናቸው፡፡ አብዛኛው እርስ በርስ ተያየ፡፡ ለየራሱም አጉተመተመ፡፡ ከጎኑ ከተቀመጠ ጋርም የሚያወራ ሠውም ይታያል፡፡ ምን ማለታቸው ነው? ሳይሉ አልቀሩም፡፡ ተናጋሪዋ ቀጠሉና የሴቶች ግርዛትን ወደ አውስትራሊያ ይዘውት የሄዱና እዚያም ልጆቻቸውን የሚገርዙትና

የሚያስገርዙት ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሄዱ ስደተኞች መሆናቸውን በተለይ ደግሞ ሶማሊያውያንና ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙበት አብራሩ። ወደአደጉት አገራት የምንወስደውም ከእነሱ የምንቀበለውም የሚገርም ነው።

ይህን ፅሁፍ ወስደው ሞያዊ እርማት ላደረጉልኝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህክምና ፋከልቲ መምህር ፕሮፌሠር ሉክማን የሱፍ ምስጋና አቀርባለሁ።

# በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም-ለምን?

...ይህ ችግር በጣም የበርካታ ሰዎችን /የባለትዳሮችን/ ቤት የበተነ፣ ጥንዶች /ፍቅረኛሞች አለመስማማትና ግንኙነታቸው ለዘለቄታው እንዳይጓዝ ያደረገ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ በሴቶች ላይ የሚከሰት /የሚታይ/ ህመም የችግሩ ስፋት ሊደንቅ ይችላል፣ ከሦስት ሴቶች ውስጥ ሁለቱ በህይወታቸው ዘመን በሆነ ወቅት በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም ይሰማቸዋል፡ ፡

ይህን ችግር ደግሞ ብዙዎች አፍነው ይይዙታል፡፡ ወደ ባለሞያ ሄደው አያማክሩም፡፡ ችግሩ መፍትሄ የሌለው እስኪመስል ድረስ ለቅርብ ጓደኛ እንኳን አያካፍሉም፡፡ በችግሩ ከሚሰቃዩ ከበርካቶች ውስጥ ቢበዛ አምስት በመቶ ሚሆኑት ናቸው በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ የሚሰማቸውን ህመም ችግር ነው ብለው ወደ ባለሞያ /ጤና ተቋም/ የሚሄዱት፡፡

ሆኖም በወሲባዊ ግንኑነት ጊዜ የሚሰማ ህመም የራሱ ምክንያትና መፍተሔ እንዳለው ባለሞያዎች ይተነትናሉ፡፡ ለዚህ ፁሑፍ መነሻ የሆነኝ ጥያቄ ከአንባቢዎቼ ውስጥ ከአንዷ ከደረሰኝ በኋላ ጉዳዩን ሰፋ አድርገው እንዲመለከቱልኝ ከባለሞያ ጋር ቆይታ አድርጌአለሁ ዶ/ር ሙህዲን አብዶ ይባላሉ፡፡ በጳውሎስ ሆስፒታል የጽንስና የማህፀን ህክምና ስፔሻሊስት ሲሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህክምና ፋካልቲ መምህር ናቸው፡፡ ለሰጡኝ ማብራሪያ በቅድሚያ ምስጋናዬን አድርሼ ወደ ጉዳዩ ልመለስ፡፡

በሴቶች ብልትና ማህፀን አካባቢ በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት የሚፈጠር ህመም በህክምና ሳይንስ ዲስፓሮኒያ /Dyspareunia/ ይባላል፡፡ ይህ ህመም ስሜትን ይረብሻል፡፡ ከወሲባዊ ግንኙነት የሚፈለገውን እርካታ እንዳይገኝ ምክንያት ይሆናል፡፡ እርካታ ማጣቱ ደግሞ በሴቷ ላይ ብቻ ላይወሰን ይችላል፡፡ ህመሙ ሲሰማት ግንኑነቱ ሊረበሽና ሊቋረጥ ስለሚችል በተቃራኒ ወገንም ወንዱ እርካታ ሊያጣ ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያት ነው ታዲያ ስምምነት የሚጠፋውና ወደ ግጭትና መለያየት የሚደረሰው፡፡ አንዳንዶች ችግሩን ተሸክመው ትዳራቸው እንዳይናጋ፣ ልጆች ተወልደው ከሆነ ልጆች እንዳይበተኑ ህመሙን ችለው

እያማጡ ያልፈለጉትን ወሲብ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ጉዳይ ግልፅ ያልሆነለት ባል ደግሞ ሚስቱ ለሱ ስሜት የሌላት፣ ሌላ ሰው የወደደች፣ ፍቅሩ ያለቀባት ወዘተ እየመሰለው ግጭት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ችግሩ ተባብሶ ወይንም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሰይታወቅ እንደተዳፈነ እስከመለያየት ሊደርስ ይችላል፡፡ ይኸው ምክንያት ገና ባልተጋቡ ጥንዶች መካከልም ወደፊት ተጣምረው እንዳይዘልቁ ከፍተኛ እክል ሊሆን ይችላል፡፡

በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት የሚከሰት ህመም /Dyspareunia/ የሚመጣው ከተለያዩ ችግሮች /ምክንያቶች/ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ለምሣሌ ግርዛት አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የሚያጋጥማቸው ልምድ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ በተፈጥሮ የሴቷ ብልት /Vagina/ ጠባብ መሆን፣ በብልትና አካባበው የአፈጣጠር ችግር /እንከን/ ሲኖር፣ የማህፀን ጫፍን ከሁለት የሚከፍል ነገር ድንገት ሊፈጠርና አካባቢውን ጠባብ እንዲሆን ሲያደርገው፣ የብልት /Vagina/ ቁመት ከበሩ እስከ ማህፀን በር ድረስ አጭር ሲሆን (በአማይ ከ7 ሴንቲ ሜትር- 9ሴንቲ ሜትር ርዝመት አለው ተብሎ ይታወቃል፡፡ አንዳንዴ ታዲያ ከዚህ ከ7 ሴንቲ ሜትረ በታች ሆኖ ሲገኝ) የተለያዩ የማህፀን እጢዎችና የማህፀን አቀማመጥ አለመስተካከል፣ በማህፀን ላይ የሚፈጠር ኢንፌክሽን /ቁስለት/ እነዚህ ሁሉ በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት ህመም የመፍጠር እድል አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአንጀትና በአንጀት አቅራቢያ የአካል ክፍሎች አካባቢ ችግር ካለ ለምሳሌ የፊንጢጣ የኪንታሮት /ሄሞሮይድ/ መፈጠር ጋር ተያይዞ ይህ ህመም ሊከሰት ይችላል፡፡ የሽንት ፊኛ ኢንፌክሽን በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት በሴቶች ላይ ህመም እንዲከሰትም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ሌላ ዋናው በብዙዎች ላይ ምክንያት ሆኖ የተገኘው ግን በተፈጥሮ በብልት ውስጥ መከሰት የሚገባውና እርጥበት እንዲኖር የሚያደርግ ፈሣሽ ያለመኖር ወይም በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈፀም በሚደረግ ዝግጅትና በግንኙነት ጊዜ ሴቶች በተፈጥሮ የሚያመነጩት ፈሳሽ ይኖራል፡፡ ይህ ፈሳሽ ግንኙነቱን ቀላል፣ ህመም የሌለበትና ምቹ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ይህ መኖር የሚገባው ፈሳሥ በተለያዩ ምክንያቶችና

ከእድሜ መጨመር የተነሳ ከቀነሰና ወይም በጭራሽ ከሌለ ህመሙ እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል።

ከዚህ ውጭ አካላዊ ከሆኑ ምክንያቶች ሌላ የስነ-ልቦና /psychology/ ጉዳይ ደግሞ በሌላ ገፅ የማይታይና በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ለሚፈጠር ህመም ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። ይኸውም አንዲት ሴት ለወሲባዊ ግንኙነት ያላት አመለካከት /ከሃይማት፣ ከባህልና ከወሲባዊ ጥቃት የተነሳ/ የተሳሳተ ከሆነ ግንኙነት ልታደርግ በምትፈልግበት /በምታስብበትና ቅድመ ዝግጅት በምታደርግበት/ ጊዜ ፈሣሽ ላይኖርና ህመም ሊከሰት ይችላል።

የህመሙ አይነት አንድ አይነትና በተመሳሳይ ጊዜ ብቻ የሚታይ ላይሆን ይችላል። ወሲባዊ ግን ኑነቱ ገና /የስጋ ተራክቦ/ ሳ ጀምር ሕመም ሊሰማት ይችላል። ይህ ስነልቦናዊ ችግር እንደሆነ በግልፅ ይታወቃል። የወንድ ብልት ከገባ በኋላ ህመም የሚሰማት ከሆነ ደግሞ ችግሩ ከኢንፌክሽን ወይንም ከላይ ከተጠቀሱት አካላዊ ችግሮች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ይህ ችግር ያለባቸው ሴቶች ደግሞ ህመሙ የሚሰማቸው ከአንድ ወንድ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ብቻ አይሆንም፣ ከማንኛውም ሰው ጋር ባላቸው ግንኙነት ሁሉ ህመሙ ሊሰማቸው ይችላል።

የሆነው ሁሉ ሆኖ ታዲያ ምክንያቱ እስከታወቀ ድረስ ይህ ችግር በህክምና መፍትሄ ይኖረዋል። ህክምናው ስነ-ልቦናዊ ወይም አካላዊ እርዳታ በማድረግ የሚረዳም ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ያለው አብይ ችግር ግን መንስኤው የማይታወቅ ከሆነ መፍትሔው ከባድ ይሆናል። ይህ አጋጣሚ የህክምናውን ሂደትም ረዥም ሊያደርገው ይችላል። በተረፈ አብዛኛው ችግር ከፈሳሽ እጥረት ወይም ያለመኖር ጋር የሚያያዝ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የተፈጥሯዊ ፈሳሹን የሚተካ ሌላ ፈሳሽ /estrogine cream/ በህክምና ይሰጣል። ከኢንፌክሽን ጋር ከተያያዘ ደግሞ የራሱ ህክምና ያለውና የሚታከምም ነው። ችግሩ ከፍ ሲል ደግሞ አንዳንዶቹ በቀዶ ጥገና የሚስተካከሉ ይሆናሉ።

በአጠቃላይ ግን የወሲባዊ ግንኙነት ህመም ከስነ-ልቦና ጋር የተያያዘ ሊሆን ስለሚችል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ወሲባዊ ግንኙነት እንደ ሥራ ሳይሆን ስሜትን ጠብቆ እርካታን ለማግኘትና ለመደሰት የሚደረግ በመሆኑ ከግንኙነቱ በፊት

በሚኖር ጊዜ ለወሲብ በተለይ ሴቶች ዝግጁ የሚሆኑበትን ሁኔታ መከተል ይመረጣል፡፡ ብዙ ወንዶች የራሳቸውን ስሜት ብቻ የሚመለከቱና ለሱ ብቻ የሚሮጡ ከሆነ የመጀመሪያው በወሲብ ያለመርካት ችግር መነሻ እነርሱ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት ወንዶች ልብ የማይሉት የሴቷን ዝግጁ ያለመሆን ሁኔታን ነው፡፡ የዚህ ችግር መፍትሔ ደግሞ እጃቸው ላይ የሚገኝ ይመስላል፡፡ ከዚህ ለዘለሉት ችግሮች ደግሞ በህክምና መፍትሄ ያላቸው በመሆኑ ከመለያየትና የተለያዩ ጥርጣሬዎችን ወደ ህሊና ከማስገባት በፊት በጊዜ ባለሞያዎችን መጎብኘት የሚበጅ ይመስላል፡፡

# «ፈተና የበዛብሽ ዕድሜዬ ከገፋ ስለወለድኩሽ ነው አልኳት»

- የሆሊውድ ዝነኛ ሴቶች ከሥራቸው በተጨማሪ በመውለድና ከልጅ ጋር በተያያዘ/ ለምሳሌ ለመውለድ በሚያደርጓቸው ተደጋጋሚ ጥረቶችና ሕክምና ተጨማሪ ዕውቅና ያገኙ ይመስላል። የታዋቂው ሃሪ ፖተር መጽሐፍ ደራሲ ጄኬ ሮውሊንግ በ37 እና በ39፣ ሚሚ ሮጀርስ በ45 ዓመቷ፣ ሳልማ ሃያክ እና ሃሊ ቤሪ በ41 ጄኒፈር ሎፔዝ በ38 ዓመቷ (መንታ) ተገላግለዋል።
- ዕድሜያቸው የገፋ ሰዎች በእርግዝና ወቅት እንደ ስኳርና ከፍተኛ ደም ግፊት ባሉ በሽታዎች የመጠቃት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።
- 40 ዓመት ካለፋቸው በኋላ የሚወልዱ እናቶች ከወጣቶቹ 14 እጥፍ በቀዶ ጥገና ብቻ ለመገላገል የሚያስገድድ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ።
- ዕድሜያቸው ከፍ ብሎ የሚወልዱ ሴቶች በአብዛኛው በግራ እጃቸው የሚጠቀሙ/ግራኝ ልጆች የመውለዳቸው አጋጣሚ ከፍ ያለ ነው።

ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ምክንያት የሆነኝ ባለፈው ሳምንት የሰማሁት የጎረቤቴ ታሪክ ነው። ጎረቤቴ ዕድሜያቸው ዘግየት ብሎ ከሚያገቡ ሴቶች ልትመደብ ትችላለች። የወለደቻቸው ለጆችም ከዕድሜዋ አንፃር ሲታይ በጣም ልጆች ናቸው። አሁንም እስዋ ወደ አዛውንትነት ልትሻገር ጥቂት በቀራት ዕድሜ እነርሱ ራሳቸውን ያልቻሉ ገና ተማሪዎች ናቸው። ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው ታሪክ የተከሰተው ታዲያ በመጨረሻ ልጇና በጎረቤቴ መካከል በተካሄደ ምልልስ ነው። ታዳጊዋ የጎረቤቴ የመጨረሻ ልጅ ታማሚ ነች። ቤተሰቦችዋ ጤናዋን ለማሻሻል ብዙ ገንዘብ ያፈሰሱና አሁንም መፍትሔ አለ ቢሏቸው ከማፍሰስ የማይመለሱ ናቸው። ልቧን ያማታል ዕለት በዕለት መድሃኒት መጠቀም የግድ ነው። የአከርካሪ አጥንት ችግር ስላለባት የቀዶ ጥገና ሕክምና ለማገኘት ተራዋን እየተጠባበቀች ነው። አካላዊ ጥንካሬዋ እንደ እኩዮችዋ አይደለም። እናቷ ደጋግማ እንደምትለውም በሕፃንነቷም ሮጣ መጫወት የማይሆንላት ቀሰስተኛ ነበረች። ታዳጊዋ ታዲያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዕድሜዋ እየገፋ ሲመጣ እንደሌላው ጊዜ ሐኪም ቤት ለሐኪም ቤት ሲያመላልሷት ዝም ማለቷን አቁማለች።

ለምን ያመኛል? ደጋግማ ማንሳት የጀመረችው ጥያቄ ነበር። መልሱን ደግሞ ማን ሊሰጣት ይችላል? የልጅቷ እናት የሆነችው ጎረቤቴን ያስጨንቃት ነበር።

ባለፈው ሰሞን ታዲያ አስባ የመጣላት መልስ ተደራራቢ የጤና ችግሮች ያጋጠማት እናትዋ ዕድሜዋ ገፍቶ ስለወለደቻት እንደሆነ የሚያመለክት ነበር፡፡ «ፈተና የበዛብሽ ዕድሜዬ ከገፋ ስለወለድኩሽ ነው አልኩዋት ነበር ያለችኝ በራስዋ ቋንቋ» የእናትየዋ ግምት እውነትነትና የዚህ አንድ ምሳሌ ጉዳይ ነገር እንዳለ ሆኖ ይህንን ስሰማ ያስታወስኩት ደግሞ ዕድሜ ገፍቶ የሚመጣ እርግዝናና ወሊድ ሊያስከትል የሚችለው ተፅዕኖ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡

ከላይ ባየነው ምሳሌ ብቻ ሳይሆን ከታች በከፊል በምናያቸውና በሌሎችም በተለያዩ ምክንያቶች በዓለማችን ዘግይተው የሚወልዱ ሴቶች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ የሴቶች በትምህርት መግፋት እየተለመደ በመምጣቱ ሴቶች በወጣትነት ዕድሜያቸው ትዳር መስርተው ልጅ መውለዳቸው ጉዳይ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ሌላው ቀርቶ ቢያገቡም የተለያዩ ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት በሚል ከመውለድ የሚዘገዩ ሴቶች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ጉዳይ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ከላይ የጠቀስነው ራስን የማሻሻል ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው ብዙ ሕዝባችን በሚኖርበት የገጠር አካባቢ ያለ እውነታ ነው፡፡ ይኸውም ከከተማ ርቀው ያሉ የገጠር ሴቶች የወሊድ መከላከያ አገልግሎት የንማያገኙበት ሁኔታና ያላቸው መረጃ በቂ አለመሆን ተዳምረው ተፈጥሮአቸው እስኪያቆም ልጅ ለመውለድ የመቻላቸው አጋጣሚ ነው፡፡ በመሆኑም ዕድሜያቸው ከገፋ በኋላም ልጅ ሊወልዱ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡ በ2005 በተካሄደው ሕዝብና ጤና ጥናት ውጤት መሠረትም አሁንም በመውለድ ዕድሜ ክልል ያሉ (ከ15 እስከ 49 ዓመት ያሉትን ያካትታል) የሃገራችን ሴቶች አማካይ ወሊድ መጠን 6 ልጆችና ከዚያም በላይ መሆኑ ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡

ዘግይቶ መውለድ ፋሽን የሆነበት ሌላ ቦታ ደግሞ ሆሊውድ ነው፡፡ የሆሊውድ ዝነኛ ሴቶች ከሥራቸው በተጨማሪ በመውለድና ከልጅ ጋር በተያያዘ/ ለምሳሌ ለመውለድ በሚያደርጓቸው ተደጋጋሚ ጥረቶችና ሕክምናዎች ተጨማሪ ዕውቅና ያላቸው ይመስላል፡፡ ከእነኝህም ቼሪ ብሌይር በ45 ዓመቷ፣ ማዶና በ41፣ የጎርደን ብራውን ባለቤት ሳራ ብራውን በ40 እና በ42 ዓመቷ ልጅ

ወልደዋል፡፡ ከዚህ ሌላ የታዋቂው ሃሪ ፖተር መጽሐፍ ደራሲ ጄኬ ሮውሊንግ በ37 እና በ39፣ ሚሚ ሮጀርስ በ45 ዓመቷ፣ ሳልማ ሃያክ እና ሃሊ ቤሪ በ41 ጄኒፈር ሎፔዝ በ38 ዓመትዋ (መንታ) ተገላግለዋል፡፡ ዘግይቶ መውለድ በተለይም ከ35 እና 40 ዓመታቸው በኋላ የሚወልዱ ግሰቶች ጉዳይ በተለይ በውጭው ዓለም ተመራማሪዎች ዘንድ በርካታ ጥናት የተደረገበትና በሳይንሳዊ ምርምሮች ሰፊ ሽፋንም የተሰጠው ነው፡፡ በቅርብ የሚወጡ ጥናቶች እንደሚሉት በዓለማችን በተይም የተሻለ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ባሉ ሴቶች ዘንድ ዘግይቶ ቤተሰብ መመስረትና መውለድ እየተለመደ የመጣ ክስተት ሆኗል፡፡ ከእነኝህ ምክንያቶች አንዱ ሴቶች ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል እያሳዩ የመጡት ከፍተኛ ፍላጎት ነው፡፡ ከዚህ ሌላ በወጣትነታቸው ቤተሰብ መስርተው የቆዩትም ቢሆኑ ቆይተው ምናልባትም ከሌላ የሕይወት ጓደኞች ተጨማሪ ልጆች ለመውለድ እያሳዩ ያሉት ፍላጎት ከፍ ማለቱ ሌላው ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ከኑሮ መሻሻልና ለሴቶች ምቹ ሁኔታዎች መፈጠር አኳያ አማካይ የመኖሪያ ዕድሜ መጨመሩ ሌላ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

«በዕድሜ የገፉ እናቶች፣ መጸነስ፣ እርግዝናና ወሊድ ከ35 ዓመት በኋላ» የተሰኘው መጽሐፍ ተባባሪ አዘጋጅ ዶ/ር ጁሊያ ቤሪማን እንደምትለው ሴቶች በሰላሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሆነው የሚያጋጥሟቸው እርግዝናዎች የታሰበባቸውና ተፈላጊ የሆኑ ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ ሴቶች በኑሯቸው የሚፈለጉትን ያገኙና ደስተኛ መሆናቸውንም ትጠቅሳለች፡፡ በዚህ ዕድሜ እየገፋ በሚመጣበት ወቅት የሚፈጠር እርግዝና ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በተመለከተ እነኝህ ሴቶች ከእርግዝናው በፊት ከወጣቶቹ ይልቅ እንደ ሪህ፣ የደም ግፊት፣ ስኳር በመሳሰሉ በሽታዎች የተጠቁ ሊሆኑ መቻላቸው አንዱ ነው፡ ፡ ከዚህ ሌላ በእርግዝና ወቅት እንደ ስኳርና ከፍተኛ ደም ግፊት ባሉ በሽታዎች የመጠቃት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የብሪቲሽ ሜዲካል ጆርናል ያሳተመው ጥናት እንደሚለው ዕድሜያቸው ገፍቶ የሚወልዱ ሴቶች በተለይ የመጀመሪያ ልጆቻቸው በስኳር በሽታ የመያዛቸው አጋጣሚ ከፍ ያለ ነው፡፡

በተጨማሪም ሴቶች ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር በተለይም ከሰላሳዎቹ የዕድሜ ክልል የመጀመሪያ ዓመታት ካለፉ በኋላ የሰውነታቸው ቅልጥፍና እየቀነሰ በእርግዝና ወቅት ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ችግሮችም የበለጠ ተጋላጭ እየሆኑ ይሄዳሉ፡፡ በብሪቲሽ ሜዲካል ጆርናል ጽሑፍ እንደሚለው 40 ዓመት ካለፋቸው በኋላ የሚወልዱ እናቶች ከወጣቶቹ 14 እጥፍ በቀዶ ጥገና ብቻ ለመገላገል የሚያስገድድ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ፡፡

በዴንማርክ የተከናወነ አንድ ሰፊ ጥናት ዕድሜያቸው ከገፋ የሚፀንሱ ሴቶች ቢያንስ ሦስት ያልተፈለጉ ውጤቶች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ ባይ ነው፡፡ እነኝህም ውጤቶች ውርጃ፣ ከማህፀን ውጪ የሚፈጠር እርግዝና እና ሕይወት የሌለው ልጅ መገላገል ናቸው፡፡ በዚሁ ጥናት ዕድሜያቸው የገፋ ሴቶች የአካል ጉድለት ያለበት ፅልጅ መውለዳቸው አጋጣሚ ከፍ ያለ ነው፡፡

ሌላው ዕድሜ ገፍቶ መውለድ ለሴቶች የሚያመጣው ችግር በመጨረሻው የእርግዝና ወቅት በማህጸን ውስጥ የሚከሰት የጽንስ ሞት ነው፡፡ ይህ ችግር ከ35 ዓመታቸው በኋላ በሚጸንሱ ሴቶች ላይ ከ440 አንዱ ሲያጋጥም በወጣቶች ላይ ግን ከ1000 አንድ እርግዝና ብቻ ይህ ችግር ያጋጥማል፡፡

በ2006 የወጣ አንድ ሪፖርት ደግሞ በመላው ዓለም መወለድ ካለባቸው ዕድሜ ቀደም ብለው የሚወለዱ ሕፃናት እየበዙ መምጣታቸውን ሲጠቅስ ለዚህ ተጠቃሽ ምክንያቶች ደግሞ ዕድሜ ከገፋ መውለድና ከመጠን ያለፈ ውፍረት ሆነዋል፡፡ እነኝህ ከጊዜው ቀደም ብሎ የሚወለዱ ሕፃናት ደግሞ ለሞትና ለአካል ጉድለት የሚጋለጡበት ሁኔታ ከፍ ያለ ነው፡፡

ከችግሮቹ ወጣ ብለን ዕድሜ ከገፋ በኋላ የሚፈጠሩና በሰላም የሚቋጩ እርግዝናዎች ውጤቶችን በሚመለከት የቀረቡትን የጥናት ውጤቶች እንመልከት፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ ዕድሜ ከገፋ በኋላ መንታና ሦስት ልጆች ባንዴ የመገላገል ዕድሉ ሰፋ ያለ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በአሃዝ ደረጃ ዕድሜያቸው ከፍ ብሎ የሚወልዱ ሴቶች በአብዛኛው በግራ እጃቸው የሚጠቀሙ/ግራኝ ልጆች የመውለዳቸው አጋጣሚ ከፍ ያለ ነው፡፡ በብሪታንያ በአሁኑ ወቅት ከጠቅላላው ሕዝብ 13 በመቶ ወንዶችና 11 በመቶ ሴቶች ግራኞች ናቸው፡፡ ይህ አሃዝ ቀደም ብሎ ከነበረውና በአንፃራዊ መልኩ ሴቶች በወጣትነት

ዕድሜያቸው ይወልዱ በነበረበት ዘመን/ ለምሳሌ በ1910 3 በመቶ ብቻ ነበር/ አነስተኛ እንደነበር ተጠቁሟል።

በዓለማችን ከፍተኛውን የዕድሜ ጣሪያ የያዙ እናቶችን ስናይ ደግሞ እ.ኤ.አ. በታህሳስ 2006 በላንተን አሜሪካ ከተደረገላት የሕክምና እገዛ በኋላ ጸንሳ በቀዶ ጥገና መንታ ወንዶችን ለመገላገል የበቃችው ማሪያ ዴል ካርመን በውሳዳ ዴል ላራ የተሰኘች ስፔናዊት ሴት ክብረ ወሰኑን ይዛ እናገኛለን። ምን ይሆናል መንትዮቹ 3 ሳምንት ዕድሜ ሲሆናቸው በተደረገላት ምርመራ የካንሰር በሽተኛ ሆና ተገኝታለች። ይህቺ ሴት ለመውለድ የበቃችው 67ኛ ልደት በዓልዋን በምታከብርበት ዋዜማ ነበር። ስፔናዊቷ ክብረወሰኑን የነጠቀችው በአንድ ዓመት ከምታንሳት ሮማኒያዊት አድሪያና ኤሊስኩ ነበር። አድሪያና በ2005 1.4 ኪሎ ግራም ብቻ የምትመዝን ሴት ልጅ በቀዶ ጥገና ተገላግላለች።

*********************

# «ቀደም ሲል ልጅ አለኝ፤ አሁን ልጅ መውለድ እንደማልችል ተነገረኝ»

የስኳር በሽተኛ ነኝ። በሽታውን ያወቅኩት በቅርቡ ሲሆን፣ በሽታው ሳይዘኝ በፊት ከጋብቻ ውጪ የተወለደ አንድ ልጅ አለኝ። አሁን ካገባኋት ሴት ግን ቀደፀም ሲል አርግዛ ስትወልድ ሞተብን። ከሁለት ዓመት በፊትም ሞክረን ሳይሳካ ቀረ። በአሁኑ ሰዓት ልጅ ለመውለድ ባለቤቴ በጣም ስለምትጓጓ እንመርመር ብላ እሷም እኔም በቤተሰብ መምሪያ በኩል አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎልን በእኔ በኩል በዘር ፍሬዬ ላይ በአንደኛው ላይ ችግር ያለ በመሆኑ የመውለድ አቅም እንደሌለኝ ተነገረኝ። በእኔ በኩል ምናልባት ከስኳሩ አለመውረድ የመጣ በመሆኑ ሲወርድ ሊስተካከል ይችላል ብልም አልሆነም። እንዲያውም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄጄ ተጨማሪ ምርመራዎችን እንዳደርግ ተነገረኝ። ከምርመራው በኋላ በአጠቃላይ መውለድ አትችልም አሉኝ። ይህም እኔንና ባለቤቴን ሐሳብ ላይ ጣለን። አዲስ ተጋቢዎች ስንሆን ዘር የመተካትና ወልደን የመሳም የሩቅ ሕልማችን በአጭር ሊቀጭ ዳር ዳር እያለ ስለሆነ እሷም ዕድሜዋ እየገፋ ስለሆነ ነገሩ በጣም አሳስቦኛል።

እኔም ከሁለት ዓመት ወዲህ በስኳሩ ምክንያት የስንፈተ ወሲብ ችግር እየገጠመኝ ስለሆነ ተቸግሬያለሁ። ይህንን ችግር ለመፍታት የሐበሻ ሕክምና ሞከርኩ አልሆነልኝም። የተለያዩ ቦታዎች ምርመራ ባደርግም የሚሆን አይደለም። በዚህ የተነሳ ተቸግሬያለሁና እባካችሁ ምክር ለግሱኝ።

*ከአንባቢዎቻችሁ አንዱ*

መካንነት ወይም ያለመውለድ ችግር በዓለማችን በብዙ ጥንዶች ዘንድ የሚያጋጥም ችግር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይ እንደ አፍሪካና እንደ አገራችን ባሉ ማኅበረሰቦች ዘንድ ዘርን አለመተካት አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ልጅ መውለድ ከሚሰጠው ማኅበራዊ ዋጋ አንፃር ያልወለዱ ጥንዶች በቤተሰቦቻቸውም ዘንድ ይሁን በሚያውቋቸው ሁሉ የሚቀርብላቸው ጥያቄ ልጅ ለምን አትወልዱም? የሚል ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም እየፈለጉና ለመውለድም ጥረት እያደረጉ በሕክምናም ጭምር እየታገዙ ያሉ ጥንዶች

በሚበዛባቸዉወ ጉትጎታ ምክንያት ለሌላ ጭንቀት ይዳረጋሉ። የሰው አለመረዳትና ጉትጎታም ሌላ ራስ ምታት ይሆንባቸዋል። በተለይም ሴቶች በትዳር ውስጥ ልጅ ላለመውለድ እንደ ምክንያት ስለሚወሰዱ ተመርምሮ ከማረጋገጥ በፊት ለተለያዩ ወቀሳዎችና ትችቶች ይጋለጣሉ። እንመርመር ማለትን በመፍራትም የእነርሱ ጥፋት መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ሳይቀር ባሎቻቸውን ወልደህ አምጣ እስከማለት የሚደርሱ ሴቶች ቤት ይቁጠራቸው።
ከላይ የተመለከታችሁት ታሪክም ከእነኝህ ልጅ አለመውለድ ትልቅ ማኅራዊ ሳንካ ከፈጠረባቸው ሰዎች የአንዱ ታሪክ ነው። ባለታሪኩ በያለበት ሄደው ቢጨንቃቸው ነው በዚሁ ጋዜጣ ላይ የምናወጣቸውን ስነ ተዋልዶን የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች በማየታቸው ለእኔም መፍትሔ ቢገኝ ብለው በፖስታ ሳጥን ያደረሱን። ይኸው ያነበባችሁት ታሪክ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ አንባቢያን ከሚልኳቸው ደብዳቤዎች የአንዱን ጠያቂ ጉዳይ የሚመለከት ነው። የጠያቂያችንን ጥያቄ ለመመለስ ጉዳዩ ቀጥተኛ እና በተለያዩ የሕክምና ባለሙያዎችም መልስ የተሰጠበት ስለሆነ ከዚህ በታች የምንለው ነገር በቀጥታ እሳቸውን ላይመለከት ይችላል። የምናነሳቸው ነጥቦች ግን በአጠቃላይ መካንነት ከምን ይመጣል? ለመካንነት የሚዳርጉ ችግሮች ምንድናቸው? ምልክቶችስ ሕክምና ምን ይመስላል ለሚለው አንዳንድ ነጥቦችን ለመመልከት የሚሞክር ነው። በዚህ መሠረት ከተለያዩ ምንጮች የወንዶችን መካንነት አስመልክነተ ያገኘናቸው ምላሾች ዝርዝር እንደሚከተለው ይነበባል።
መረጃዎቻችን ማብራሪያቸውን የሚጀምሩት መካንነት ለዘመናት ከሴቶች ጋ ብቻ ተያይዞ የሚከሰት ችግር እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱን በመጥቀስ ነው። ይህም ከላይ ከጠቀስነው ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ነው። ሆኖም ከዓለማችን የመሀንነት ችግር ግማሾቹ ከወንዶች ጋር የሚገናኙ እንደሆኑ መረጃዎቹ ይገልጻሉ። በዓለማችን አብረው ከሚኖሩ ጥንዶች ከ15 – 20 በመቶ የሚሆኑት ልጅ መውለድ የማይችሉ ሲሆን፣ ከእነኝህ ጥንዶች 50 በመቶው ልጅ መውለድ ያልቻሉት በወንዶቹ ችግር ምክንያት ነው። ይህም ማለት ከዓለማችን በመወለድ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ወንዶች ከ7 – 10 በመቶ የሚሆኑ አባት ለመሆን የማይችሉ ናቸው ማለት ነው።

እናም ለጥንዶች ልጅ እንዳይወልዱ ከዳረጓቸው ምክንያቶች አንዱ በወንዶች በኩል ያለው ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ በወንዱ ላይ ያሉ አንዳንድ ችግሮች በአለመውለድ ችግሮች ላይ የሚደመሩና ማርገዝንና ልጅ ማግኘትን አስቸጋሪ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ልጅ መውለድ ያለመቻል ችግር ሲፈጠር ሁለቱም ጥንዶች ምርመራ ማከናወን ይገባቸዋል፡፡ እንደ ባለሙያዎቹ ገለጻ ጥንዶች መካንነት አጋጠማቸው የሚባለው ደግሞ ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ተኩል ያለ ምንም መከላከያ ግንኙነት ሲያደርጉ ቆይተው ሴቲቱ መጸነስ ካልቻለች ነው፡፡

መካንነት በወንዶች በተለያዙየ ምክንያቶች እንደሚመጣ ሊመጣ እንደሚችል መረዳዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከእነኝህ ምክንያቶች አንዳንዶቹ የወንድ የዘር ፍሬ ከወንድ ፈሳሽ (ሲመን) ጋር አብሮ እንዳይወጣ የሚያደርጉ አካላዊ ችግሮች ሲሆኑ፣ ሌሎች ምክንያቶች የወንዱ የዘር ፍሬም መጠንና የመባዛት አቅም የሚያሳንሱ ችግሮች ናቸው፡፡ እነኝህን ችግሮች ለማስከተል ከሚችሉ መንስዔዎች መካከል በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ (የአባላዘር) በሽታዎች የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛሉ፡፡ እንደ ከርክርና ጨብጥ የመሰሰሉት በሽታዎች በወንዶች ላይ መካንነት የሚያመጡ ሲሆን አልፎ አፀልፎ በሽታዎቹን በመታከም ከዚህ ጋር የሚመጣ የመካንነት ችግርን ማስወገድ ይችላል፡፡

በተፈጥሮ (ሲወለዱ ጀምሮ) የሚኖር የአካል ጉድለት ወይንም ዘግይቶ የሚመጣ የአካል ጉዳት የዘር ፍሬ ማመንጫ (ማስተላለፊያዎች ላይ በሚኖር የመዘጋት ሁኔታ የሚመጣ መካንነት ሌላው ዓይነት በወንዶች መካንነትን የሚያመጣ ችግር ነው፡፡ እንደ ፕሮስቴት ያሉ በወንዶች የመራቢያ አካላት ላይ የሚመጡ በሽታዎችና በዘር ፍሬዎች አካባቢ ምክንያት የሚመጡ የማስተላለፊያ መዘጋቶች በቀዶ ጥገና መፍትሔ ሊገኝላቸው ይችላል፡፡

በአንዳንድ ወንዶች ዘንድ በተፈጥሮ የዘር ፈሳሻቸው ወደ ውጪ በመውጣት ፋንታ ወደ ውስጥ የሚመለስ መሆኑ ሌላው ከመካንነት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቀስ ነጥብ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር በስኳር ሕመም በአንዳንድ የሕክምና ዓይነቶች እንዲሁም በፊኛና ፕሮስቴት አካባቢዎች ላይ በሚደረግ ቀዶ ጥገና ምክንያት ሊመጣ ይችላል፡፡ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ በዘር

ከሚመጡና በጥቂት ግለሰቦች ላይ ብቻ በሚከሰቱ ችግሮች (በዘር የሚተላለፍ በሽታ) ምክንያት መካንነት ሊመጣ ይችላል፡፡ ሆርሞኖች መዛባትም ሌላው ለመካንነት የሚያበቃ ጉዳይ ነው፡፡

ለወንዶች የስንፈተ ወሲብ ችግር በመውለድ ላይ ችግር ሊያመጣ/ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል የተጠቀሰ ሲሆን፣ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ምክንያቶች ለስንፈተ ወሲብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነኝህ ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች ሐኪም ዘንድ ቀርበው ስለችግሮቻቸው ማማከርና መፍትሔ መሻት ያስፈልጋቸዋል፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት እንደጠያቂያችን ያለ የብልት መቆም ችግር በዚህም ምክንያት ግንኙነት ያለመፈጸም ችግር ከመካንነት ጋር የሚገናኝ አለመሆኑ ነው፡ ፡ ይኸውም እንዲህ ዓይነቱ ችግር ያለባቸው ወንዶች የዘር ፍሬያቸው ተወሰደ በላብራቶር ከሴቷ እንቁላል ጋ እንዲገናኝ ተደርጎ ልጅ መውለድ የሚችሉ መሆኑ ነው፡፡ እንዳለ መታደል ሆኖ ይህ ሕክምና በሀገራችን ውድ ከመሆኑ ባሻገር በሀገራችን ደረጃ በሙከራ ላይ ያለ ነው፡፡

የተመለከትናቸው መረጃዎች እንደሚሉት አብዛኞቹ የመካንነት ችግር ያለባቸው ወንዶች ግንኙነት በመፈጸም በኩል ምንም ዓይነት ችግሮች የሌሉባቸው ጤናማ የወሲብ ሕይወት ያላቸው ናቸው፡፡

ዋናው ጉዳይ ለመካንነት የሚያጋልጡ ችግሮች የተለያዩ በመሆናቸው ግለሰቦች ሐኪም ዘንድ በመቅረብና ተከታታይ ሕክምናዎች ምርመራዎችን በማድረግ ችግሮቻቸውን በመለየትና መፍትሔም መፈለግ ያለባቸው መሆኑ ነው፡፡

********************

# ‹‹ቫይረሱ ካለበትና ከሌለበት ሰው ጋር የሚደረገው ግንኙነት የተለያየ ነው››

‹‹በቅርቡ ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር መውጣት ጀምሬያለሁ። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለመተላለፍ የሚችፀልበትን አጋጣዝማና መንገድ እንዲሁም ያለዙሀበትን ሁኔታ አደገኛነት አውቃለሁ። ነገር ግን እንደኔ ባለ አጋጣሚ ውስጥ ስለነበሩና ለኤች.አይ.ቪ የመጋለጥ ሁኔታ ስለገጠማቸው ሰዎች የሰማሁት ነገር የለም። ጥንቃቄ የተመላበት ግንኙነት ብናደርግ ለኤች.አይ.ቪ የመጋለጤ ዕድል እንዴት ነው?››

*አንዷት ሴት ለዘርፉ ባለሙያ ያቀረበችው ጥያቄ*

******

‹‹የተለያየ የኤች.አይ.ቪ ውጤት ላላቸው ሰዎች ልጅ መውለድ ይቻል ይሆን? እኔ ከቫይረሱ ነፃ ስሆን ጓደኛዬ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ ይገኛል። ልጅ ማግኘት ይቻላል የሚባል ከሆነስ እንዴት? የሚጠይቃቸውስ ነገሮች ምንድናቸው? ልጅ ለማግኘት በጣም እንፈልጋለንና መፍትሔው ምን ይሆን?››

*ልጅ የፈለጉ ጥንዶች ለኤክስፐርቶች የሰነዘሩት ጥያቄ*

******

‹‹የተለያየ የኤች.አይ.ቪ የምርመራ ውጤት ያላዠው ጥንዶች፣ አንዳቸው ቫይረሱ ሲገኝባቸው ሌላኛቸው ነፃ የሚሆኑ የወሲብ ተጓዳኞች (በባለሙያዎቹ አጠራር ዲስኮርዳንት ካፕልስ) ቁጥር በሃገራችን እየጨመረ መጥቷል። ይህ የሚያሳየው በትዳርም ይሁን በጓደኝነትና አብሮ በመኖር ሁልጊዜም ኮንዶም መጠቀም ግድ እና አስፈላጊ መሆኑን ነው››

*የኡጋንዳ የጤና ጥበቃ የሥራ ኃላፊ*

******

‹‹በኢትዮጵያ የተለያየ ውጤት ያላቸው ወንድና ሴት ተጓዳኞች በኤች.አይ.ቪ ለመያዝ ከፍተኛ ዕድል ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ነገር ግን በኢትዮጵያ ለጥንዶች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሉም አልያም ከቁጥር የሚገቡ አይደሉም››

*የፌደራል ኤች.አይ.ቪ መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት*

******

‹‹እንደ አጋጣሚ ዓረብ አገር ለመሄድ ምርመራ ሳደርግ ቫይረሱ እንዳለብኝ ተነገረኝ፡፡ የዛሬ ስድስት ዓመት፡፡ ነገሩን የከፋ ያደረገው ደግሞ የእኔ ስለቫይረሱ ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት ዕውቀት አለመኖር ነበር፡፡ በወቅቱ ለእኔ ሁኔታው ከባድ ነበር፡፡ ውጤቱ ያልተጠበቀ ስለነበር አጠገቤ የነበሩት ሁሉ ደነገጡ፡፡ ከአምስት ዓመት በላይ የኖርኩበት ትዳሬ፣ ሁለቱ ልጆቼ ምንም ሊያጽናኑኝ አልቻሉም ነበር፡፡ ራሴን አገለልኩ፣ ቤት ዘግቼ ማልቀስ ነበር ሥራዬ፡፡ ቆይቼ ልጆቼንና ባለቤቴን ትቼ በጠፍ ጨረቃ እንጦጦ ማርያም ፀበል ቦታ ሄጄ ተቀመጥኩ፡፡ እዚያ የነበሩትን መሰሎቼን ብዛት ሳይ በትንሹ ተስፋ አደረግኩ፡፡
ቀጥሎ ባለቤቴ አፈላልጎኝ ያለሁበት ድረስ መጣ፡፡ እየመላለሰ ሲጠይቀኝ እሱም እንደሚያመው ነገረኝ፡፡ እሱ ካለባት እኔም ይኖርብኛል ብሎ ስላሰበ መሰለኝ እኔ ላይ ይታዩ የነበሩ ምልክቶች ይታዩበት ነበር፡፡ ምን ችግር አለ እንሂድና አንተም ልጆቹም ተመርመሩ፣ ካለባችሁም እዚሁ ተቀምጠን አምላካችንን እንለምናለን አልኩት፡፡ ሁላችንም ሜሪ ጆይ ሄደን ተመረመሩ፡፡ ውጤቱ ሁለተኛዋ ልጄ ከእኔ ጋር ተመሳሳይ ከመሆኗ በስተቀር ባለቤቴና የመጀመሪያ ልጃችን ከቫይረሱ ነፃ ነበሩ፡፡
ማመን አልቻልኩም፡፡ በወቅቱ ያለኝ እውቀት አናሳ ስለነበር ምንም ሊገባኝ አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር ነፃ ካደረገው ከማን ጋር እሚገታለሁ? ነበር ያልኩት፡፡ በወቅቱ እሱ ምንም አላለም፡፡ በእኔ በኩል ትዳር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ሁለታችንም ሌሎች ጓደኞች ነበሩን፡፡ ከዛሬ 11 ዓመት በፊት ስንጋባ ደግሞ ከተዋደዱ መጋባት እንጂ ምርመራ የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ ከእናት ወደ ልጅ ሕክምና በሌለበት ዘመን የመጀመሪያ ልጄን ስወልድም ያለጥንቃቄ ነበር፡፡ ጡትም ጠብቷል፡፡ ከማግባቴ በፊት ይዞኝ ቢሆን ልጄ ይተላለፍበት ነበር? መቼና እንዴት ያዘኝ የሚለውን አላውቀውም፡፡
የተለያየ ውጤት ይዞ አብሮ መኖር የሚለውን አላመንኩበትም፡፡ አያስኬድም ብዬ ነበር የወሰንኩት፡፡ መፍታት እንዳለብን ወሰንኩ፡፡ በእሱ በኩል እንዳንለያይ ይፈልግ የነበረ ቢሆንም በእኔ ግፊት ትዳራችን ተደመደመ፡፡ ብዙ ሰዎች ለምን ሌሎች ይኖሩ የለምን? ቢሉኝም አዎን እኔ ግን አልቀበለውም ነበር መፀልሴ፡፡ ተመርምሮ ሌላ እንዲያገባ እኔም መንገዴን እንድቀጥል ተማመንን፡፡ ጥንቃቄ

እያደረጉ መኖር ቢቻልም አንድ ቀን መጋለጥ ይኖራል ብዬ እሰጋለሁ፡፡ በዚህ ላይ ቫይረሱ በደምሽ ውስጥ ኖሮ ከጤነኛ ሰው ጋር የምታደርጊው ግንነነትና ካንቺ ጋር አንድ ዓይነት የኤች.አይ.ቪ ውጤት ካለው ሰው ጋር ተሳስበሽ የምታደርጊው ግንኙነት በጣም ይለያያል፡፡ በቅርቡ ከቫይረሱ ጋር ከሚኖር ሰው ጋር ጋብቻ ፈጽሜያለሁ፡፡››

******

የተለያየ የኤች.አይ.ቪ ውጤት ሁኔታ ያላቸው ጥንዶች ጉዳይ አሁንም በዓለም ላይ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ሴትና ወንድ ለብዙ ዓመታት ያለኮንዶም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሰፈጽሙ ኖረው በሆነ አጋጣሚ በጋራም ሆነ በተናጠል ምርመራ ሲያደርጉ የአንዳቸው ውጤት ከሌላቸው የተለያየ የሚሆንባቸው ጊዜያት ብዙ ባይባልም የሚከሰት አጋጣሚ ነው፡፡

ባለሙያዎቹ ይህ ሁኔታ ኤች.አይ.ቪን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችል ክስተት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የወሲብ ሕይወት ጉዳይ በተለይም ከማን ጋር መቼ ወሲብ መፈፀም አለብኝ/ እችላለሁ? የዝማለው ጉዳይ ግለሰባዊ መብት እና የግል እንደመሆኑ እዚህ ውስጥ ገብቶ ጓደኛህ/ሽ ቫይረሱ ስላለበት/ ስላለባት አብረሽው መኖር አትችይም/አትችልም ማለቱ የማይቻል ነው፡፡ ነገር ግን ውሳኔው እንደየግለሰቡ የተለያየ ሆኖ ኤች.አይ.ቪ ካለባቸው ተጓዳኞቻቸው ጋር ለመኖር ለሚያስቡ ሁሉ ምን ዓይነት ሥጋቶች አሉባቸው ለሚለው ለአብነት ኤክስፐርቶች ከላይ በመግቢያችን ላይ ለተቀመጡት ሁለት ጠያቂዎች የሰጧቸውን መልሶች እንመልከት፡፡

‹‹ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር መውጣት ጀምሬያለሁ፡፡ ጥንቃቄ የተመላበት ግንኙነት ብናደርር ለኤች.አይ.ቪ የመጋለጤ ዕድል እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሴን መጀመር የምፈልገው ማንኛውም ጤናማ የወሲብ ሕይወት እየመራ ያለ ሰው ራሱን ከኤች.አይ.ቪ መቶ በመቶ የማከካልበት እርግጠኛ መንገድ የሌለው መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ የተለያየ የኤች.አይ.ቪ ውጤት በሚኖራቸው የወሲብ ተጓዳኞች ጉዳይ የተለያዩ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ ኒው ኢንግላንድ ጆርናል ኦፍ ሜዲስን በ256 ተመሳሳይ ሁኔታ ባላቸው ጥንዶች ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ በጥናቱ በናሙና ከተወሰዱና ሁልጊዜም በአግባቡ ኮንዳም ከሚጠቀሙ 124 የተለያየ የኤች.አይ.ቪ ውጤት ያላቸው ጥንዶች

መካከል አንዳቸውም ለቫይረሱ አልተጋለጡም። ሁልጊዜ ኮንዶም ከማይጠቀሙ 121 ጥንዶች መካከል ደግሞ 12 ያህል በቫይረሱ ተይዘዋል። ሁልጊዜም ኮንዶምን በአግባቡ መጠቀም ቫይረሱን ወደሌለበት ሰው ላለማሻገር ወሳኝ አማራጭ ሆኗል። ኮንዳም ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል ወሳኝ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ የማይሠራበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ይህም የሚሆነው በአግባቡ ካለመጠቀም የተነሳ ነው።
የተለያየ ውጤት ላላቸው ጥንዶች ልጅ ማግኘት ጉዳይን በተለከተ በኤች.አይ.ቪ የመያዝ አደጋን የሚቀንሱ (ሙሉ በሙሉ ማስወገድ አይቻልም) እና ለመፀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ያለጥንቃቄ የሚፈፀም ወሲብ ምንጊዜም ቫይረሱን ወደሌላው ተጓዳኝ የማስተላለፍ ዕድል አለው። በሕክምና ዘዴ ተጠቅሞ የወንዱን የዘር ፍሬ ማፀዳት አንዱ መንገድ ነው። ይኸው ድርጊት ኤች.አይ.ቪ ካለበት ወንድ ወደሌለባት ሴት የሚደረገውን ቫይረሱን የማስተላለፍ ዕድል ይቀንሳል። ለበለጠ መረጃ ደግሞ በአካባቢ የሚገኙ የፅንስና ማህፀን ሐኪሞችን ማማከር ተገቢ ነው።››
የደማቸው ውጤት የተለያየ የሚሆኑ ጥንዶች ጉዳይ በሀገራችን በሰፊው ጥናት ካልደተረገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። የፌደራል ኤች.አይ.ቪ መከላከያ ጽ/ቤት የጠቀሰው የ2005 የሕዝብና ጤና ጥናት ለምሳሌ ምርመራ ከተደረገላቸው 2674 ጥንዶች መካከል 1.8 በመሃተው የተለያየ ውጤት ያላቸው እንደሆኑ አስቀምጧል። እነኝህ ጥንዶች እንዴት በጥንቃቄ መኖር እንደሚችሉም ይሁን ልጅ በመውለድና በሌሎች ፆታዊ ግንኙነት ነክ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያማክራቸው ባለሙያ ማግኘትን ይሻሉ። በእርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን የተለያየ ውጤት ያላቸውን ጥንዶች ማማከር የጤና ባለሙያዎች ፈተና እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።
ከላይ እንደተጠቆመው ኮንዶም በሚጠቀሙበት ወቅት የሚፈጠረውንና ለኤች.አይ.ቪ ለመጋለጥ የሚዳርገውን ስህተት በተመለከተ ከላይ የሰፈሩትን ጥያቄና መልሶች የተገኙበት ድረ ገፅ (የዲስኮርዳንት ካፕልስ ድረ ገፅ) ያሰፈራቸውን ምክሮች በማስቀመጥ ጽሑፌን ላብቃ።

- በምትጠቀሙበት ኮንዶም ላይ በምንም ዓይነት ቅባት ነክ ነገሮች ማለትም የምግብ ዘይት፣ ቫዝሊን የመሳሰሉትን ነገሮች አትጠቀሙ። ይህ ኮንዶሙን ያሰሳዋል
- ኮንዶሙን በጥርሳችሁ ሳይሆን በእጃችሁ ቅደዱት
- ኮንዶም ሙቀት እንዳይነካው ተጠንቀቁ፣ ስትገዙ የመጠቀሚያ ጊዜው አለማለፉን አይታችሁ አረጋግጡ።

********

# የእናቶቻችን ጠላት ማነው?

ይድረስ ለውድ ወንድሜ አቸናፊ ሁነኝ ባለህበት፡፡ ዛሬ ይህንን ደብዳቤ የምጥፍልህ የምስራች ልነግርህ አይደለም፡፡ ለወራት በሬን አዘግቶ በእንባ ያጠበኝን፣ ዓለም ላይ ብቻዬን የቀረሁ ያክል ብቸኝነት ውስጥ የዘፈቀኝን መርዶ ላረዳህ ነው ይህችን ደብዳቤ መጫጫሬ፡፡ እውነታው መራራ ቢሆንም ልትሰማው ግድ ነው፡፡ ዜናው ቢመርህም እያቃረህም ቢሆን ዋጠው፡፡ አዎ ሚሽቴ፣ እናታለሜ ሞታለች፡፡ ዳግም ወደዚህ ምድር ላትመለስ አሸልባለች፡፡

«ፍሬው ያማረ ዘር እንዲበዛለት፣ አባት ደስ ይለዋል ልጅ ሲወለድለት» ይል ነበር የከተሜ ዳንኪራ፡፡ እኔ ግን ልደ ሲወለድልኝ ከመደሰት ይልቅ አለቀስኩ፤ ደም አነባሁ፡፡ ከበርካታ ሰዓታት ምጥ በኋላ ውድ ባለቤቴ ልጄን (ልጄን) ሰጥታኝ አሸለበች፡፡ የአባትነት ወጉን አሳይታኝ ተደስቼ ሳላበቃ የልጅነት ሚሽቴ አረፈች፡፡ ልጄን አቅፌ አነባሁ፡፡

ምጥ የጀመራት አመሻሹ ላይ ነበር፡፡ የቀኗ ዝንበር ወደ ማደሪያዋ መከተት ስትዠምር ድንገት የያዛት ምጥ ከባድ ነበርና ታለሁበት ተጠርቼ ወደ ጎጆዬ ስዘልቅ የድህነት አጋሬ መደቡ ላይ ተንጋላ ታምጣለች፡፡ ላብ ሁለመናዋን ደፍቋት ውሃ የተደፋባት እንጂ ያላባትም አትመስል፡፡ አይኖቿ የእንባ ዘለላዎችን ያጎርፋሉ፡፡ ሳያት ሆዴን ባር ባር አለኝ፡፡ በመንደሩ ሴቶች ተከባ ነበርና በእነሱ ፊት ላለማልቀስ ወደ ደጅ ወጥቼ ተከብቶቹ በረት ታዛ ስር ጉልበቴን አኮራምቼ ቁጭ አልኩኝ፡፡ ወንድ ልዥ ብቻውን ነው የሚያለቅስ ይባልም አይደል፡፡ ሚሽቴ ስታምጥ የከበቧት የቀያችን ሴቶች ማርያም ማርያም ሲሉት ይሰማኛል፡፡ አምጦ መውለድ የሴት ወጉ ነው ይባላልና ሚሽቴም ከአፍታ በኋላ በሰላም ተገላግላ መንደርተኛው እልልታውን ያቀልጠዋል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡ ግና ያሰብኩት ቀርቶ ምጧ ለሰዓታት ዘለቀ፡፡ ይሄኔ «ማርያም ማርያም» የሚሉትን የመንደሩን ሴቶች ድምፅ ተከትዬ ወደሰማይ ቀና አልኩኝ፡፡ «የጭንቅ አማላጅቷ ምነው ሚሽቴን ዘነጋሻት» አልኩኝ፡፡ ግና ጠሎቴን የሰማችኝ አልመሰለኝም፡፡

ተዛው ተከብቶቹ በረት ታዛ ቁጭ ብዬ ስንቆራጠጥ ጀንበር ጠልቃ የምሽቱ ዳፍንት ወረሰኝ፡፡ የምሽቱ ቅዝቃዜ እየበረታ ሲመጣና የሚሽቴም የምጥ ድምፅ ጠንክሮ እረፍት ቢነሳኝ ወደ ጎጆዬ ዘልቄ «ኧረ እናንተ ሰዎች ግዴለቻችሁም

ተሃኪም ዘንድ እንውሰዳት» አልኩኝ። ሰሚ አልነበረኝም። «ሂድ ወዲያ ምጥን ለመንደራችን ብርቅ አደረከው እንዴ! ሁላችንም አምጠንም አይደል የወለድን። ደሞስ በይህ ሰዓት ምን ሃኪም ነው የሚኖር።» በአንደ በኩል እነሱ ትክክል ናቸው። በይህ ምሽት ምን ሃኪም ይኖራል? እንደው ቢጨንቀኝ እንጂ እንዲህ ማለቴ ለቀኑም ቢሆን ስንት መንገድ ተጉዘን ነው ተሃኪም ዘንድ የምንደርስ። ምን አባቴ ላድርግ?ዥ

እኩለ ሌት ገደማ የሚሽቴ የምጥ ድምጥ እየሰለለ እየሰለለ መጣ። እምጥ ልግባ እስምጥ ግራ ገባኝ። ልዩህ ይሆን? እሪ ብዬ ጮሄ ይውጣልኝ ይሆን? ምን አባቴ ልሁን? ተአፍታ በኋላ ግን ከጎጆዬ ውስጥ የሕፃን ለቅሶ ተሰማ። ኋላም የቀያችን ሴቶች የእልልታ ድምፅ ተከተለ። ቅድም በጭንቅ ልጮህ እንዳልቃጣኝ ሁሉ አሁን ደግሞ በደስታ መጮህ አማረኝ። ግና ጉሮሮዬ ተለጉሞ አልላቀቅ አለኝ። የመንደሩ አዋላጅ እትዬ እልፏ ወደኔ መጥተው «እንኳን ደስ አለህ» ተማለታቸው ተጎጆዬ ውስጥ ከፍተኛ ጩኸት ተሰማ። ሮጠን ወደ ውስጥ ስንዘልቅ እታለሜ፣ ሚሽቴ ላይ ተጠምጥማ ታለቅሳለች። አሄሄ ሚሽቴ ሞታለች። የሆነውን ሁሉ ማመን አልቻልሁም። ደነዘዝኩ። እውነት እውነት እልሃለሁ ለቀናት እንባ አልወጣኝም። ዓይኖቼ እንባ ማንጠብ አቅቷቸው ልቤ ግን ደም አንብቷል። ለምን! ኧረ ተወኝ ወንድም ዓለም! ያችን የመሰለች ብርቱ ሴት በምጥ መተች ቢሉ ማን ያምናል? ብቻ ሞተችብኝ። ስለሆነው ሁሉ ራሴን ወቀስኩት። የአባት ወግ ይድረሰኝ ብዬ ያስረገዝኳት እኔም አይደለሁ? አዎ ገዳይዋም እኔ ነኝ። ምጥ ነው እንዳትሉኝ።

ወንድምህ ፍሬው ሁነኝ

**********

በዓለማችን ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ችግሮች ሳቢያ በእያንዳንዱ ዓመት 585,000 ያህል እናቶች ለሕልፈት ይዳረጋሉ። ሌሎች በርካቶች 50 ሚሊዮን እናቶች ደግሞ በእርግዝና በወሊድ ችግሮች ሳቢያ በየዓመቱ ለማይሽር የጤና ችግር ይዳረጋሉ።

የችግሩ መነሻና መድረሻ በአብዛኛው ድህነት የሚፈጥረው ነውና ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚከሰተው ሞት በታዳጊ ሃገራት እናቶች ላይ ይበረታል። ከ500,000 በላይ እናቶች በእርግዝናና በወሊድ ችግሮች ሳቢያ ይሞታሉ ስንል፣

ሚሊዮኖች ደግሞ ለአስከፊ የጤና ችግር ይዳረጋሉ ስንል አብዛኛውን ቁጥር የሚሸፍኑት ወይም 99 በመቶ የሚሆኑት ሰለባዎች እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ምስኪን እናቶች ናቸው፡፡

*******

የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ እንደሚጠቁመው እያንዳንዷ ጀንበር ወጥታ እስክትገባ በእያንዳንዷ ቀን 1,600 እናቶች ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ችግሮች ሳቢያ ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡

በእስያና ከሰሃራ በታች ባሉ አፍሪካ ሃገራት የሚኖሩ እናቶች ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ችግሮች የግንባር ቀደሙን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ለምሳሌ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሃገራት ከሚኖሩ 16 እናቶች መካከል አንዷ ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተየያዘ ለሞት ትዳረጋለች፡፡ ይህንን ስሌት ካደጉት ሃገራት እናቶች ጋር ስናነፃፅረው ልዩነቱ በብዙ መቶ እጥፍ ይጎላል፡፡ በሰለጠኑ ዓለማት ከሚኖሩ ከ2,800 እናቶች መካከል አንዷ ብቻ ናት ከወሊድ ጋር በተያያዘ ለጤና ችግር ወይም ለሞት የምትዳረገው፡፡ ልዩነቱ የትየለሌ ነው፡፡

ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ችግሮች ሳቢያ በርካታ እናቶችን በሞት የምታጣው ሃገር አፍሪካዊቷ ሴራሊዮን ስትሆን ከ100,000 እርጉዝ እናቶች መካከል 2,000 የሚሆኑት ለሞት ይዳረጋሉ፡፡ ተከታዩን ደረጃ የምትይዘው ደግሞ አፍጋኒስታን ነች፡፡ ከ100,000 እርጉዝ እናቶች የ1,900 እናቶች መጨረሻ ሞት ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ብዙ እናቶች በእርግዝናና በወሊድ ሳቢያ አይሞቱባትም ተብላ በመጨረሻነት የተመዘገበችው አውስትራሊያ ስትሆን ከ100,000 አራቱ ብቻ ናቸው ለህልፈት የሚዳረጉት፡፡

************

ወደሃገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ትንሽ ቆየት ያሉ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ ከ100,000 እርጉዝ እናቶች 850 የሚሆኑት ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ቀላል ቁጥር አይደለም፡፡ እዚህ በሃገራችን ኢትዮጵያ በእርግዝናና በወሊድ ጣጣ ከ14 ነፍሰጡር እናቶች አንዷ ለሕይወት ሕልፈት ትዳረጋለች፡፡

ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት የተደረገ አንድ ጥናት እንዳመለከተው በመዲናችን አዲስ አባ ከ100,000 ነፍሰጡር እናቶች መካከል ከእርግዝና ጋር

በተያያዙ ችግሮች ሳቢያ 566 የሚሆኑት ሕይወታቸውን ያጡ ነበር። ዛሬስ? የችግሩ ስፋት የት ደርሶ ይሆን? ቤት ይቁጠረው። ለዛሬ አበቃሁ። የሳምንት ሰው ይበለን። ሰላም እና ጤና ለምስኪን እናቶቻችን ይሁን።

************************

# ለደረሳችሁ … እንኳን አደረሳችሁ!

የዕድሜ ኸረት ፍሰት ሄዶ በሮ ቀናት በቀናት ሚዛን ተቆጥሮ፣ ተቀምሮ ትናንት አረጀ አፈጀ በታሪክ ቋት ተከተተ እነሆ ለአዲስ ዕድሜ ቀመር አዲስ ዓመት ባተ

****

ትናንት ዛረን እየወለደ፣ ቀናት በቀናት እየተተካኩ እነሆ አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ተተካ፣ አሮጌው ሚሊንየም ተሰኝቶ አዲሱ ሺሕ ገባ። ዛሬ የአዲሱ ዓመት የአዲሱ ሚሊኒየም አራተኛ ቀን ላይ እንገኛለን። መስከረም 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የዓመቱም የአዲሲም ሚሊኒየም የመጀመሪያ ቅዳሜ! እንኳን አደረሳችሁ። ክቡራትና ክቡራን አንባብያን ሰላም ለእናንተ ይሁን!

****

በዚህ ባለንበት የፈረንዳቹ ዓመት 2007 ብቻ እዚህ በሃገራችን ኢትዮጵያ ከ977 ሺሕ በላይ ሰዎች ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ጋር ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል። ይህ መረጃ እስከ ዛሬ ከምናውቃቸው መረጃዎች ሁሉ የለየና አዲስ ነው። እስከ ዛሬ ከ1.3 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ከቫይረሱ ጋር ይኖራሉ ተብሎ እንደሚገመት ነው ሲነገረንና እኛም ስንናገር የነበረው። ኸው አዲሲ መረጃ ግን በቅርቡ ይፋ የሆነ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ መረጃ ነው። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ሁለት የተለያዩ ጥናቶች ያወጡትን የተለያየ መረጃ ለማስታረቅና ወደ አንድ መረጃ ለመምጣት በተደረገ ጥናት የተገኘ ውጤት ነው ይህ አዲሱ መረጃ። በዚህም መሠረት በዚህ በያዝነው በ2007 የፈረንጆቹ ዓመት በሃገራችን ከ977 ሺሕ በላይ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ይገመታል።

****

አዲሱን ዓመት፣ አዲሱን ሚሊኒየም በሙሉ ጤና በፍቅር በደስታ ከነሙሉ ቤተሰቦቻችን ወዳጅ ዘመዶቻችን የተቀበልነውን ያህል በዚያ በሸኘነው ዓመት ብቻ የቅርብ፤ በጣም የቅርብ ሰዎቻችንን በሞት ተነጥቀን ሃዘን የገባን ስንቶቻችን ነን? ስንቶቻችን ነን የምንወዳቸውን የምንሳሳላቸውን፣ የምንናፍቃቸውን ከአጠገባችን እንዲርቁ የማንፈልጋቸውን ሰዎች በሞት የተነጠቅን። የሁሉም የሞት ምክንያት የተለያየ ቢሆንም ስንቶቻችን ነን የቅርብ ሰዎቻችንን የሞት መንስኤ ጠንቅቀን የምናውቅ? የስንቶቻችን ቤተሰቦች፣

ወዳጅ ዘመዶች በመኪና አደጋ ሞቱ? የስንቶቻችንስ በወባ? የስንቶቻችንስ በሳንባ ነቀርሳ? የስንቶቻችን ዘመዶችስ በኤድስ ለሕልፈት ተዳረጉ? ምናልባትም አብዛኞዎቻችን የወዳጅ የዘመዶቻችንን የሞት መንስኤ በትክክል አናውቀው ይሆናል። የሞታቸው መንስኤ ለየቅል ነውና ከአንድ አጠቃላይ ድምዳጀሜ ላይ መድረስ አይቻል ይሆናል። ግና የቅርብ ጊዜ መረጃ እንደሚጠቁመው እስከ ወርሃ ጥር 1999 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ ባለፈው የፈረንጆቹ 2006 ብቻ ማለት ነው ከ88 ሺሕ በላይ ሰዎች በኤድስ መሞታቸው ተገምቷል።

*****

በተለያዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎች፣ ወይም በመኪና አደጋ፣ ወይም በተለያዩ በሽታዎች በወባ፣ በካንሰር፣ በሳንባ ነቀርሳ እና በሌሎች ገዳይ በሽታዎች ከሚሞቱትም በላይ ምናልባትም በብዙ እጥፍ የሚልቁ ኢትዮጵያውያን በኤድስ ሳቢያ ሕይወታቸውን ያጣሉ። በኤድስ ከሚሞቱትም ባልተናነሰ በየዓመቱ አዳዲስ ሰዎች በቫይረሱ ይያዛሉ። ይህ አባባል እንዲህ በጥሬው ሲወራ የተጋነነ ይመስላል። ግና መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት በ2006 ብቻ ከ122 ሺሕ በላይ ኢትዮጵያውያን ደም ውሰጥ ቫይረሱ እንደተገኘ ተገምቷል።

***********

ከሁለት ወራት በፊት በሰኔ ወር ይፋ የሆነው አዲሱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ መረጃ እንደሚጠቁመው በሃገራችን ከ977 ሺሕ በላይ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ቢሆንም በአሁኑ የፀር ኤች.አይ.ቪ መድሃኒቱ የግድ የሚያስፈልጋቸው 258 ሺሕ ያህሉ ብቻ ናቸው።

************

በኤች.አይ.ቪ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የኤች.አይ.,ቪ ሥርጭትና የኤድስ የገዳይነት መጠን ከዓመት ዓመት እየጨመረ ሊመጣ ይችላል። እንደ መረጃዎቹ ከሆነ የኤች.አይ.ቪ የሥርጭት መጠን ከመቀነስ ይልቅ የመጨመር ዝንባሌን ነው የሚያሳየው። ምናልባትም የሥርጭቱ ፍጥነት በተገመተው መጠን የሚቀጥል ከሆነ አሁን 977,394 የተገመቱት ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ቁጥር ከ3 ዓመታት በኋላ በ2010 እ.ኤ.አ ወደ 1,216,988 ሊያድግ

ይችላል። ይህንን ስንሰማ የሥርጭቱን መጠን የመቀነስ ኃላፊነት በሁላችንም እጅ ውስጥ እንዳለ እንረዳለን። ቢያንስ የዛ ቁጥር አካል ላለመሆን አንድ ነገር ማድረር እንችላለን። ራሳችንንና ወገኖቻችንን ከኤች.አይ.ቪ እንጠብቅ። እናም የአዲሱ ዓመት፣ የአዲሱ ሚሊንየም ጤናማ ዜጋ እንሁን! ለደረሳችሁ እንኳን አደረሳችሁ! የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅር፣ የደስታ ዘመን ይሁንልን!

*****************

# ከኔጌቲቭና ፖዘቲቭ የደም ዓይነቶች የሚፈጠር ፅንስ

- **የደም ዓይነታችሁ እንደሚጣጣም አረጋግጣችኋል?**

‹‹የደሜ ዓይነት ኦ ኔጌቲቭ መሆኑን ስረዳ ባለቤቴ ደግሞ ፖዘቲቭ የደም ዓይነት ያለው ነው፡፡ ይህ የሚያሳው የፀነስኩት ፅንስ ፖዘቲቭ የደም ዓይነት ሊኖረው መቻሉን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሰውነቴ የፅንሱን ደም እንደ ባዕድ በማየት ሊዋጋው እንደሚችል ተነግሮኛል፡፡ እባካችሁ በዚህ ላይ ተጨማሪ መረጃዎች ብትሰጡኝ?››

አንዲት ሴት ‹‹በርክሌይ ፓረንትስ ኔትወርክ›› ለተባለው የቤተሰብ ጉዳዮችን የሚመለከት ድረ ገፅ ያቀረበችው ጥያቄ ሲሆን፣ ከተመለሱላት መልሶች ጥቂቶቹ ደግሞ ከዚህ በታች ያሉትን ይመስላሉ፡፡

*******

‹‹የደም ዓይነት አለመጣጣም የሚያመጣው ችግር ሊፈታ የሚችል ነው፡፡ የመጀመሪያ እርግዝናሽ ነው? እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው ውርጃ ወይንም የተቋረጠ ፅንስም እንደ እርግዝና እንደሚቆጠር ነው፡፡ የመጀመሪያሽ ከሆነ የሚያስፈልግሽ (RH O-GAM) የተባለ መድሃኒት በእርግዝናው አጋማሽና ሕፃኑ ከተወለደ በኋላ መውሰድ ነው፡፡ ይህ መድሃኒት ጊዜያዊ ‹‹አር ኤች ፋክተር››ን የሚከላከሉ ሴሎችን በመፍጠር የእናትየው ሰውነት መከላከያውን እንዳያመርት ያደርጋል፡፡ ሁሉንም ሁኔታ ለመወሰን ግን ሐኪምሽ ሁኔታሽን እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርብሻል፡፡ መፀነስሽን ካወቅሽ ጊዜ ጀምሮ ምርመራ አድርገሽ የማታውቂ ከሆነ አሁኑኑ ወደ ሐኪም ቤት ሄደሽ ምርመራዎችን ማድረግ ይኖርብሻል››

በጤና ባለሙያ የተረጋገጠ መላሽ

*****

‹‹ከባለቤቴ ጋር የተለያየ አር ኤች ፋክተር ያለው የደም ዓይነት ነው ያለን፡፡ አንቺን ያጋጠመሽ ቅስተት ከእኔ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዋናው ጉዳይ ከሐኪም ጋር መነጋገር ነው፡፡ ሐኪምሽ ምን ጊዜ የሚያስፈልግሽ መድሃኒት መወሰድ እንዳለበት ያውቃል፡፡››

ተመሳሳይ ሁኔታ አጋጥሟት የሚያውቅ ወላጅ

******

«እኔ ኦ ኔጌቲቭ የደም ዓይነት ሲኖረኝ የልጆቼ አባት ኦ ፖዘቲቭ ነው። ልጆቼ ኣ ፖዘቲቭ የደም ዓይነት የኖራቸው ሲሆን፣ የባለቤቴን የደም ዓይነት ነው የወሰዱት። ያንቺም እንደዚህ ቢሆን አይገርምም። ይህ ሁኔታ የሚየስከትለውን ችግር ለማስቀረት በእርግዝናዬ ወቅትና ከወለድኩ በኋላ መድሃኒት ተሰጥቶኝ ነበር። የተሰጡኝ በሁለቱ እርግዝናዎቼ መካከል ሲሆን፣ በመካከሉ የማስወረድ አደጋ ገጥሞች ነበር። መድሃኒቶቹን መውሰድሽ ወሳኝ ሲሆን፣ የዘመናዊው ሕክምና የፈጠራቸው ተአምራቶች እንደ ማለት ናቸው። ተፈጥሮ እርስ በርሱ የሚቃረን ሲሆን፣ ያስገርማል። ቀደም ባሉት በእናቶቻችን ዘመናት ተቃራኒ የደም ዓይነቶች ካላቸው ሰዎች በመፈጠራቸው ምክንያት ተመሳሳይ ፅንሶች ማደግ የማይችሉ ነበሩ። አሁን ግን ይህ ችግር ተቃሏል። »

ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበረችና ሁለት ልጆችን መውለድ የቻለች ሴት

*******

አንዷት ሴት መፀነሷን ካወቀች በኋላ ከሚደረጉ ምርመራዎች መካከል የተለያዩ ዓይነት የደም ምርመራዎች ይገኙበታል። መሠረታዊ ከሚባሉ የደም ምርመራዎች ባንዱም «አር ኤች ፋክተር» (RH negative) ይሆናል ማለት ነው። በአጠቃላይ 85 በመቶ የሚሆኑት ሰዎች ኤች አር ፖዘቲቭ ናቸው። አንዷት አር ኤች ኔጌቲቭ የሆነች ሴት አር ኤሃት ኔጌቷቭ የደም ሁኔታ ካለው ሰው ብትፀንስ ከሁለቱ የሚፈጠረው ልጅ የጤና እክሎች ሊያጋጥሙት የመቻሉ ዕድል ሰፊ ነው።

ይህቺን አጭር ማብራሪያ ያስቀደምኩት አር ኤች ኔጌቲቭ የሆነች ነፍሰጡር ባለቤቱን ይዞ ሐኪም ቤት የሄደና ችግር ውስጥ እንደሆነ የተነገረው አንድ አንባቢዬ ላለበት ሁኔታ ማብራሪያ የሚሰጥ በመሆኑ ነው የዛሬ ርዕሰ ጉዳያችን። አር ኤች ኔጌቲቭ መሆን ምንድነው? ከላይ እንደተጠቀሱት እና የተለያየ አር ኤች ፋክተር ያላቸው ሰዎች ተጋብተውም ይሁን ሳይጋቡ ጽንስ ቢፈጠር አልያም ልጅ መውለድ ቢፈልጉ የሚያጋጥማቸው ሁኔታ ምንድነው? መፍትሔውስ? ለሚለው ከተለያዩ የመረጃ ምንጬች የተገኙ እውነታዎችን ለማሳየት እንመክራለን በዚህ ጽሑፍ።

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የተለያየ አር ኤች ፋክተር ካላቸው ወላጆች የተገኘ ልጅ በእናቲቱ ማለትም አር ኤች ኔጌቲቭ ደም ሁኔታ ካላት ሴት ውስጥ ሆኖ የፅንሱ የደም ዓይነት ግን ከአባቱ ጋር ተመሳሳይ አር ኤች ፖዘቲቭ ሊሆን ይችላል። መረጃዎቻችን እንደሚጠቁሙትም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካላቸው ወላጆች ከሚወለዱት ልጆች ግማሽ ያህሉ የአባታቸውን የደም ሁኔታ ይይዛሉ።

ይህ የተለያየ አር ንአች ፋክተር የመኖር ሁኔታ (RH incompatibility) ይሉታል በሕክምናው ቋንቋ በእናቲቱ የመጀመያ እርግዝና ወቅት የከፋ ችግር ሊፈጥር እንደማይችል ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ። ይኸውም ያልተለመደ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ የፅንሱ ደፀም እናትየው ደም ዝውውር ውስጥ የሚቀላቀልበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ነው። ሆኖም በወሊድ ወቅት የእናትየውና የፅንሱ ደም ሊቀላቀል የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህ በሆን ደግሞ እናትየው ሰውነት ከራሱ የተለየ የሆነውን የደም ዓይነት እንደ ባዕድ አካል በመቁጠር የሚከላከልበትን ሴል በመፍጠር የእናትየው ሰውነት የገቡትን የደም አካላት ያጠፋል ማለት ነው።

ይኸው በመጀመሪያ ፅንስ ብዙም ጉዳት አያመጣም የተባለው ክስተት እንደገና ቢፈጠርና አር ኤች ኔጌቲቭ የሆነች እናት አር ንአች ፖዘቲቭ የሆነ ፅንስ ቢኖራት ሰውነቷ የፅንሱን የደም ሴሎች እንደ ባዕድ አካል በመቁጠር እነርሱን የሚዋጋ የመከላከያ ሴል ማምረት ይጀምራል። በዚህም ምክንያት የፅንሱ የደም ሴሎች ለእብጠትና ለመሰነጣጠቅ ሊዳረጉ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የፅንሱ የደም ሴሎች በአደገኛ ሁኔታ እያነሱ እንዲሄዱ ያደርጋል። ይህ ክስተት በሕክምናው አጠራር hymolytic ወይም RH disease of the newborn ይታወቃል።

ይህ ሁኔታ እንዴት መፍትሔ ያገኛል? ወደሚለው ስንመጣ ሕክምናው እንደዛሬው ዘመን ሳይሰሻል ለመፍታት አስቸጋሪ እንደነበር መረጃዎቻችን ያስቀምጣሉ። ባለንበት ጊዜ ግን ይህ ክስተት እንዳጋጠማት የታወቀ ሴት በመጀመሪያ እርግዝናዋ ወቅት በ28ኛው የእርግዝና ሳምንት እና በወለደች በ72 ሰዓታት ውስጥ በሚሰጥ መድሃኒት ይሰጣታል። ይህ መድሃኒት እንደ ክትባት የሚያገለግልና ሰውነቷ ተጨማሪ መከላከያ ሴሎችን እንዲያመርቱና ወደፊት

በሚያጋጥሟት እርግዝናዎች ላይም ተመሳሳዩ ውስብስብ ሁኔታ እንዳያጋጥማት የሚያደርግ ነው፡፡

አንዲት ነፍሰጡር ሴት የያዘችው ፅንስ ከእርስዋ የደም ዓይነት ጋር ተቃራኒ የሆነ አር ኤች ፋክተር ያለው መሆኑን መለየት የምትችልበት ምንም ዓይነት አካላዊ ሁኔታና ምልክት የለም፡፡ ማወቅ የምትችለው በሚደረግላት የደም ምርመራ ብቻ ነው፡፡ በምርመራ ውጤቷ ኔጌቲቭ ከሆነች ባለቤቷ ሲመረመርና ከእርሷ ጋር ተመሳሳይ ይሁን ተቃራኒ የአር ኤች ሁኔታ እንዳለው ሊለይ ይገባል፡፡ ከሁሉም የተሻለው ደግሞ ጥንዶች ልጅ ለመውለድ ሲያስቡ የደም ዓይነታቸውን ምርመራ ቢያደርጉ ክስተቱ እንደሚኖር ተገምቶ ጥንቃቄ እንዲደረግና አስፈላጊውን ሁኔታ በሐኪም ክትትል ሥር በመቆየት የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በነገራችን ላይ ይህ ከላይ ጀምሮ ስናብራራው የቆየነው ክስተት በተለምዶ በሃገራችን «ሾተላይ» እየተባለ የሚታወቀው ክስተት ነው፡፡ በዘልማዳዊው ሁኔታ መፍትሔ እንደሌለው ተደርጎ ሲወሰድ የኖረ ሲሆን፣ ከሕክምና ዕድገት ጋር ግን መፍትሔ ተገኝቶለታል፡፡

ወደጠያቂዬና ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ልትኖሩ ለምትችሉ ሰዎች ማስታወስ የሚገባው ጉዳይ ደግሞ መድሃኒቱ ሊወሰድ የሚገባበት ጊዜ ከመቅረቡ በፊት ከሐኪሞቻችሁ ጋር በመነጋገርና በጤና ማዕከላት በመገኘት መድሃኒቱ መኖሩንና በተፈለገበት ወቅትም ሊሰጣችሁ እንደሚችል እርግጠኛ መሆን መቻል አለባችሁ፡፡ በተረፈ እንደ መረጃዎቻችን መድሃኒቱ ውጤታማነቱ በሚገባ የተመሰከረለት በመሆኑ ሥጋት ሊገባችሁ አይገባም፡፡ ከሐኪም ክትትል ጨርሶ አለመጥፋትና በሐኪም የሚሰጡ ትዕዛዛትን መቀበል ደግሞ ወሳኝ መሆኑን ሁልጊዜም ማስታወስ ይገባል፡፡

**********

# «ማስተርቤሽን»ን ማቆም ይቻላል? ማቆም የሚገባውስ ለምንድነው?

- ማስተርቤሽን የዓይንን ብርሃንን ማጣትን ሊያስከትል ይችላል
- በኋለኛው ዘመን ለስንፈተ ወሲብ ይዳርጋል
- የአዕምሮ ሕመም ሊያመጣ ይችላል
- የወሲብ ፍላጎትን ጨርሶ ያጠፋል
- ዘር ፍሬን ይቀንሳል
- እጅ ላይ ፀጉር እንዲወጣ ያደርጋል

ከላይ ከተቀመጡትና በማስተርቤሽን ዙሪያ ከሚነገሩ ሌሎችም አባባሎች የትኞቹ እውነት ናቸው? የትኞቹስ አፈታሪኮች? «ማስተርቤት ማድረግ» የሚያስከትለው አካላዊ ጉዳት አለ? ሥነ ልቦናዊ ተፅዕኖውስ ምንድነው? መልሱን ከዛሬው ጽሑፍ ያገኛሉ፡፡

ለዛሬው የውይይት ርዕሳችን መነሻ የሆነኝ ከአንድ የዚህ አምድ አንባቢ የላከልኝ ጥያቄ ነው፡፡ በዕድሜ ወጣት የሆነው ጠያቂዬ ያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ የብዙ ወጣቶችን ሕይወት የሚመለከት በመሆኑ ወደዚህ ገጽ ሊመጣ ግድ ሆነ፡፡ ይኸው ጉዳይ በእንግሊዝኛው «ማስተርቤሽን» የሚባለውና ራስን በራስ ለማርካት የሚደረገው ሁኔታ (በአማርኛው ሴጋ እየተባለም የሚታወቅ ሲሆን ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን «ራስን በራስ ማርካት» እያልን እንጠራዋለን፡፡) ነው፡፡ ርእሱ ሲነሳ የሚመጣልን ጉዳይ ማቆሙ ለምን አስፈለገ ወይንም ጉዳቱ ምንድነው? የሚለው ሊሆን ይችላል፡፡ ማቆም ይቻላል ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የብዙዎቻችን መልስ «በሚገባ! ምን ያቅታል?» የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የምናወራው ሱስ ሊሆን ስለሚችለውና ሕይወታችንን እንዳንቆጣጠር በማድረግ ትልቅ ተፅዕኖ ሊመጣ ስለሚችል ጉዳይ ነው፡፡

የጠያቂዬን ሁኔታ በአጭሩ ላስቀምጥና ከተለያዩ መረጃዎች ያገኘኋቸውን ራስን በራስ የማርካት አሉታዊ ተፅዕኖዎችና ለመተው ለሚፈልጉ ሁሉ ለመተው የሚረዱ ዘዴዎችን በተመለከተ ስለተጠቀሱ ነጥቦች ወደ ማብራራቱ አልፋለሁ፡፡ ጠያቂዬ ከላይ እንዳልኩት በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ለ10 ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ በየቀኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ ራሱን በማርካት

(ማስተርቤት በማድረግ) ሱስ የተጠመደ ነው። መተው እንደሚፈልግና ለዚህ የሚሆን መፍትሔ እንደጠቆመው ሲጠይቅ ድርጊቱን የገለፀው «ይህንን መጥፎ ልማድ» በማለት ነው።
ራስን በራስ የማርካት ሁኔታ በሁለቱም ፆታዎች ሊኖር የሚችል ልማድ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አዘውትሮ የሚፈፀመው በወንዶች እንደሆነ ይገለፃል። ድርጊቱም በየትኛውም ዓለም ባሉ ወንዶች ዘንድ የሚፈፀም ነው። በሕክምናውና በሥነ ልቦናው ዘርፍ ፀምርምርና ክርክሮች ከተደረገባቸውና እየተደረገባቸው ካሉ ጉዳዮችም አንዱ ነው።
አንድ የሕክምና ጉዳዮችን የሚመለከት ድረ ገጽ እንዳሰፈረው ከአሜሪካውያን እስከ 6 በመቶ የሚሆኑት በወሲብ ሐሳብ የመጠመድ በሽታ ሰለ0በ ሲሆኑ፣ ችግሩ የሚያጠቃው ወንዶችን መሆኑን ጠቁሟል። እንደ ድረ ገፁ ሪፖርት በዚሁ ችግር የተጠቁ ሰዎች በስልክ የወሲብ «አገልግሎት» የሚሰጡ ስልኮችንና የዚሁ ተግባር አከናዋኝ የሆኑ ድረ ገጾችንና ቻት ሩሞችን በመጠቀም ተግባር በመጠመድ ሥራ ለመሥራት እስከማይችሉበት ሁኔታ ድረስ ደርሰዋል። የዚሁ ድረ ገፅ መረጃ እንደሚለውም ራስን በራስ የማርካቱ ድርጊት የሚመነጨው ለወሲባዊ ግንኙነት ከሚኖር አሉታዊ አመለካከት ነው።
ራስን በራስ የማርካት ሱስ በተለያየ መልኩ ሰዎች ሕይወታቸውን በአግባቡ እንዳይመሩ ያደርጋል። የሚሰማን ስሜት የሚወሰነው በምርጫችን ሲሆን የስሜታችን ሁኔታና የደስተኝነታችን መጠን ለሰውነታችን ከምናደርገው እንክብካቤ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው። ሰዎች የማስተርቤሽን ልማድ ሰለባ ሲሆኑ የአዕምሮ ጤናቸው ላይ ተፅዕኖ ሊፈጠርባቸው ይችላል። ከሕይወታችን በአንዱ ክፍል የማንቆጣጠረው ነገር በኖረ ቁጥር ደስተኛነታችን ምሉዕ ሊሆን አይችልም።
ማንኛውም ሰው ሰውነቱን ከተፈጠረበት ምክንያት ውጪ ለሆነ ተግባር ሲጠቀም በደመነፍስ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ይሰማል። ራስን በራስ የማርካት ሁኔታም ከዚህ ብቻ ሳይሆን ራስን ከመግዛት ጋር ተቃራኒ ነው። የማስተርቤሽን ሱሰኛ የሆነ ሰው ሰውነቱን የሚገዛው ራሱ ሳይሆን የተገላቢጦሽ ሰውነቱ እሱን ይገዛዋል። ሱሰኛ የሆነ ሰው ድርጊቱን የመፈፀም ፍላጎትና ስሜት ሲያጣ

ድርጊቱን የመፈፀም ፍላጎትና ስሜት ሲመጣ ድርጊቱን ከመፈፀም ውጪ አማራጭ አይኖረውም። ይህም በራስ መተማመንንና ሕይወትን በአግባቡ መምራትን ሁኔታ በእጅጉ ይጎዳል።

በሥነ ልቦና በኩልም ራስን በራስ የማርካቱ ሁኔታ አስከፊ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ይጠቀሳል። ስንፈጠር ሕይወታችንን እንድንመራ ወደፊት የሚሆነውንና የሕይወታችንን አቅጣጫ እንድንመራ ተደርገን ነው። ራስን በራስ የማርካት ሱስ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው።

በተለይ በጋብቻ ውስጥ አልያም ከፍቅረኛ ጋር አብሮ በመኖር ሒደት ሰውነታችንን ፍቅርን ለማጎልበትና ቀረቤታንም ለማጠናከር እንጠቀምበታለን። ስሜታችንን ለሌላው ሰው የማጋራት አንድ ዘዴ ሲሆን፣ ማስተርቤት በማድረግ ሊገኝ የሚችል አይደለም። በተጨማሪም ራስን ማርካት አንድ ሰው ራሱን ወዳድ ብቻ እንዲሆን ያደርጋል። ለሌላው ተጓዳኝ ማሰቡን የማያቆም በመሆኑም ግንኙነቱን ይጎዳዋል።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት ከሥነ ልቦናው ተፅዕኖው ሌላ ማስተርቤሽን አካላዊ ጉዳትንም ሊያመጣ ይችላል። ይህም ድርጊቱን መፈፀም ከተጀመረ ማቆሙ አዳጋች መሆኑግ ወደ ሱስም ካደገ ከመቆም ይልቅ የሚቀጠልበት ሒደት መብዛቱና የሚፈፀምበትን ጊዜም ወደ መጨመር መሄዱ ነው።

ሌላው ሊሰመርበት የሚገባ ነጥብ ሰውነታችን ግንኙነት ለማድረግ እንጂ ለማስተርቤሽን የተፈጠረ አለመሆኑ ነው። ራስን ማርካት ከሌላ ሰው ጋር ሊፈጸም የሚችል ጤናማ ወሲብና በዚህም ሳቢያ የሚገኘው ሥነ ልቦናዊና አካላዊ እርካታ ተቃራኒ ነው። ባለሙያዎቹ እንደሚሉትም ጤናማ ወሲብ በሚፈፀምበት ወቅት የሚመነጩና ደስተኛነታችንን የሚጨምሩ ሆርሞኖችን ማጣት ሌላው ራስን በማርካት ሱስ የመጠመድ ውጤት ነው። እናም እንደ ባለሙያዎቹ ማስተርቤሽን ጉዳት እንጂ ጥቅም የሌለው ድርጊት ነው።

የተለያዩ እምነትና አመለካከት ያላቸው ሰዎችም ማስተርቤሽን ስህተትና ኢሞራልም የሚደገፍ ተግባር አለመሆኑን ይጠቅሳሉ። ሰዎች የተለያየ እምነትና አመለካከት ያላቸው እንደመሆኑ ይህንን ለየግለሰቡ እንተውውና ድርጊቱ

በጥቅሉ ቢያንስ ከዚህ በታች የተቀመጡት አሉታዊ ውጤቶች ያሉት መሆኑን ጠቅሰን እንለፍ። እነኚህም፦

- ስለራስ ብቻ ማሰብን ይጨምራል
- በራስ መተማመንን ይቀንሳል
- የፈጠራ ችሎታ ያዳክማል
- ከሰዎች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ፍላጎትን ይቀንሳል
- ሰዎች ቢያውቁ ምን ይሉኛል? የማለትና የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል።

በሌላ በኩል ራስን በራስ የማርካት ሁኔታ (ማስተርቤሽን) በሕክምና የሚሰጠውን አተያይ በተመለከተ አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች ከላይ ካነሳናቸው ነጥቦች በተቃራኒ ማስተርቤት ማድረግ አካላዊ ጉዳት አያመጣም ካሉ በኋላ ከላይ በመግቢያው ላይ የተጠቀሱት በሙሉ አፈታሪኮች መሆናቸውን ስንነግራችሁ «በደስታ ነው» ይላሉ። እነኝሁ ባለሙያዎች ድርጊቱ ሥነ ልቦናዊ ጉዳት እንደሚያመጣና በተለይ ለባለትዳሮችና በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ላሉ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላቸውን ሕይወት ሊያበላሽ እንደሚችል ያምኑበታል። እናም ከላይ የጠቀስናቸውንና እነኝህ ጉዳቶችን ሊመጣ የሚችለውን ሱስ እንዴት ማስወገድ ይቻላል ወደሚለው ነጥብ እናልፋለን።

ድርጊቱን እንዴት ማቆም ይቻላል ለሚለው መረጃዎቻችን የሚጠቅሱት ነጥብ ወደ ራስ መመለስ፣ ድርጊቱን መፈፀም ከሚያመጣው ጥፋተኝነት ስሜት ለመገላገል ራስን መመልከት ዋናው እንደሆነ ይገልፃሉ። የመጀመሪያው ነጥብ ድርጊቱን ለመተው ጠንካራ ፍላጎት መፍጠር ነው። ባለሙያዎቹ እንደሚሞክሩት የማናቸውም ስኬት መነሻው ጠንካራ ፍላጎት መሆኑ ግልጽ ነው። አንድን ሱስ መተው ጥረት ደግሞ ራሱን የቻለ የለውጥ ሒደት ነው። ሁለተኛው መሰጠት (Commitment) ሲሆን፣ እንዲመጣ ለምንፈልገው ለውጥ ሒደት መገዛት ነው። ወደ ድርጊቱ ያስገባን/እንድንገባ የገፋፋን ድርጊት ምን እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ሌላው ነጥብ ነው ይህ ምክንያት አሁንም አብሮን ካለ ደግሞ ልናስወግደው መጣር። ድርጊቱን የመፈፀሙን ሐሳብ ለመተው የምናስበውን ነገር የመቆጣጠር ልማድን ማዳበር ሌላው መፍትሔ ነው።

የማቆሙን ጥረት ከጀመሩ በኋላ በአጭር ጊዜ ለውጥ ለማምጣትና ወዲያውኑ ድርጊቱን ለማቆም አዳጋች መሆኑን በመገንዘብ እያሻሻሉ ለመሄድ ጥረት ማድረግ የሚሉት የባለሙያዎቹ ምክሮች ናቸው፡፡ ሁኔታው የባሰ እና ከቁጥጥር ውጪ ሆኗል ተብሎ ከታመነ ደግሞ ሳይካትሪስት ዘንድ መሄድ ያዋጣል፡፡

*************

## «ፅንስ ማቋረጥ የማይቻለው መቼ ነው?»

ይህ ደብዳቤ የደረሰኝ ከ2 ሳምንት በፊት ነበር። እናም ለዚህ አድማጭ ምላሽ የሚሰጥ ዝግጅት ለማጠናቀር ስዘገጃጅ አንዲት አድማጭ በሞባይል ስልኬ ደወለች። የእርሷም ችግር ከእርግዝና ጋር የተያያዘ ነው። ግን ደግሞ ከቀዳሚው አድማጩችን በተቃራኒ የሚጠቀስ ነው። ይህች አድማጫችን ማርገዟን ካወቀች አንድ ወር አልፏታል። ያኔ የምርመራ ውጤቱ መፀነሷን ሲነግራት በደስታ ነበር የቦረቀችው ትዳር ከመሠረተች ገና 3 ወራት ብቻ ናቸው የተቆጠሩት። ከምታፈቅረው ባለቤቷ መፀነሷ ብቻ ሳይሆን እናት ልትሆን መቃረቧን ስታስበው ደስታዋ እጥፍ ድርብ ሆነ። የመፀነሷ ዜና ባሏን የበለጠ አስፈነጠዘው፡ ፡ የዛን ዕለት ምሽት የምትወደው ሆቴል ወስዶ የደስ ደስ እራት ጋበዛት። ከእራት በኋላ ወደቤታቸው ከተመለሱ በኋላ አልተኙም «ሌሊቱን ሙሉ ስናወራ ስናወራ ነው የነጋው» ትላለች። ሁለቱም ልጃቸው ሴት እንድትሆንላቸው ተመኙ። እናም ሊሊቱን ሙሉ ስም ሲመርጡላት አደሩ። ስለአስተዳደጓ፣ ስለምትማርበት ት/ቤት ሁሉ ሲመክሩ ነበር የነጋው። ደስታቸው ወሰን አልነበረውም። «ግን» ትላለች አድማጫችን «ግን ደስታችንን የሚያጨልም ዜና ከሐኪሜ ተነገረኝ» አለች የለቅሶ ሳግ በተናነቀው ድምፀት «ምነው?» አልኳት። በሚያሳዝን ድምፀት «ከባድ የልብ ሕመም አለብኝ» አለችኝ እናም ፅንሱ እንዲያድግ መፍቀድ አንቺን ለሞት አሳልፎ መስጠት ማለት ነው ብሎ በፅንሱ ላይ ያለውን አቋም ሐኪሙ አስረግጦ እንዳስረዳት ነገረችኝ ታሪኳ ልቤን በሃዘን ነካው። እናም ማረጋገጫውን ከሌላ ሐኪም ጠይቄ ላስደምጣት ቃል ገባሁላት። በዚህም ቃሌ መሠረት እነሆ ለሁለቱም አድማጮች ምላሽ የሚሰጡ የሕክምና ባለሙያ አስነብባችኋለሁ።

አነስተኛ ቢሆንም ሳናንገራግር እንዲወለድ ወሰንን ሁለተኛ ልጃችን ጊዜውን ጠብቆ ሲወለድ እጅግ በጣም ደስተኞች ነበርን። በማገኛት አነስተኛ ገቢ ሁለት ልጅ ማሳደግ ያን ያህልም ከባድ አልነበረም። ሦስተኛ ልጅ እንዳይመጣ ግን ትልቅ ጥንቃቄ እናደርግ ነበር። የተለያዩ የወሊድ መከላከያ መንገዶችን እንጠቀም ነበር። ሆኖም በአንዳች ባልጠበቅነው አጋጣሚ ሚስቴ ፀነሰች ሦስተኛ ልጅ ወደቤታችን የማምጣት አቅም የለንም በፍፁም አንችልም። ስለዚህ ፅንሱ

መቋረጥ ነበረበት፡፡ እናም ባለቤቱ ዳግም ለውርጃ እንዳትመጣ ከባድ ማስጠንቀቂያ ከሐዝከሙ ተሰጣት ለ3ኛ ጊዜ ፅንሱን አቋረጠች፡፡ ይህ ከሆነ ሁለት ዓመት ገደማ ቢሆነው ነው፡፡ ባለቤቴ ዳግም እንዳትፀንስ ከፍተኛ ጥንቃቄ እያደረግን እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ግና ከሁለት ሳምንት በፊት ሚስቴ አንድ አስደንጋጭ ዜና ነገረችኝ እንደፀነሰች እውነት እላችኋለሁ ከሚስቴ ተደብቆ በሬን ዘግቼ አነባሁ፡፡ የሰው ልጅ አንዴ ይሳሳታል፤ ስህተት ነው፡፡ ሁለተኛ ይሳሳታል፤ የዋህነት ነው፡፡ ሦስተኛና አራተኛ ሲሳሳት ግን ደደብነት ነው ትል ነበር እናቴ፡፡ አዎ በእኔ የደረሰው ይሄ ነው፡፡ ከሚስቴ ጋር ቁጭ ብለን በስፋት ተነጋገርን፡፡ ግና ፅንሱን ደግሞ ከማስወጣት በስተቀር ሌላ መፍትሔ የለምና ወደ ሐኪም ቤት ሄደች፡፡ ግና ሐኪሙ አንድ መራራ እውነት ነው ለበለቤቱ የነገራት «ከዚህ በላይ ውርጃ መፈፀም አትችይም» አላት፡፡ ይህንን መጥታ ስትነግረኝ ራሴን ማጥፋት ነበር ያማረኝ፡፡ ግን ተጠራጠርኳት ፅንሱ እንዲወለድ ፈልጋስ ቢሆን ያም ይቅርና ሐኪሙ አለኝ ያለችው እውነት ቢሆን እውነታው ምን ድረስ ነው? የሚል ነው የእኔ ጥያቄ፡፡ ሦስት ጊዜ ፅንስ አቋርጣለች፡፡ ለአራተኛ ጊዜ ማድረጓስ ምን አደጋን ያስከትላል? ለዚህ ጥያቄዬ ምላሽ እፈልጋለሁ፡፡ ሳይረፍድ በጊዜ ምላሽ እንደምትሰጣትም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የእናንተው አድማጭ ከአቃቂ፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንድ የዘርፉ ባለሙያ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡ ባለሙያው ዶ/ር አትክልት ፀጋዬ ይባላሉ፡፡ በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ት/ት/ ክፍል ተማሪ ነበሩ፡፡ «ፅንስ እንዳይቋረጥ የሚያደርጉ አስገዳጅ የሕክምና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?» ለሚለው ጥያቄ ማብራሪያ ሲሰጡ ሦስት አበይት ምክንያቶችን ጠቅሰው ነበር፡፡ በተናጥል እንመልከታቸው፡፡

ጠያቂያችን ቀደም ሲል ያነሳው ጉዳይ ፅንሱን በተደጋጋሚ የማቋረጥ ጉዳይ በሕክምና የማይመከር እንደሆነ ነው ባለሙያው የገለፁት፡፡ ስለዚህም ከሁለት ጊዜያት በላይ ፅንስ ያቋረጠች እናት ዳግም ብትፀንስ ፅንሱ አድጎ እንዲወለድ እንጂ እንዲቋረጥ አይመከርም በሕክምና፡፡ ይህ የሚሆነው ለእናቲቱም ለፅንሱም ጤንነት ሲባል ነው፡፡ አንዲት እናት በተደጋጋማ ውርዳ ከፈፀመች በቀጣዩ እርግዝናዎቿ ላይ ላልተፈለገ የፅንስ መቋረጥ እንድትዳረግ ሊያደርጋት

ይችላል፡፡ እናቲቱ ምንም እንኳ ፅንሷን ብትፈልገውም ቀድማ በፈፀመቻቸው ውርጃዎች ተፅዕኖ ሳቢያ ላልተፈለገ የፅንስ መቋረጥ (ውርጃ) ልትዳረግ ትችላለች፡፡

አንዲት እናት በተደጋጋሚ ውርጃ እንዳትፈጽም የሚፈለግበት ሌላም ተጨማሪ ምክንያት አለ፡፡ እናቲቱ ከውርጃ በኋላ አንዳስ ፅንስ ብትቋጥር (ብታረግዝ) እርግዝናው ጤናማ ላይሆን ይችላል፡፡ የሽንት ውሃ መፍሰስ ሊያጋጥም ይችላል፤ ወይም ምጥ ያለጊዜው እንደመጣ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ይላሉ ዶ/ር አትክልት፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ወይም የጤና አደጋዎች መነሻነት ነው አንዲት እናት በተደጋጋሚ ፅንስ እንዳታቋርጥ የሚመከረው፡፡

የሕክምና ባለሙያዎች ፅንስ እንዳይቋረጥ የሚመክሩበት ሌላም ሁኔታ አለ፡፡ ይኸውም የጤና ተቋማትን አቅም ያገናዘበ ነው፡፡ እርግዝና ለማቋረጥ የሰለጠነ የሰው ኃይልና አስፈላጊ ቁሳቁስ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ የፅንስ ማቋረጥ ሥራ እንዲሠራ አይመከርም፡፡ የፅንስ ማቋረጥ ሥራ በማንኛውም በታና ሁኔታ በዘፈቀደ የሚከናወን አይደለም፡፡ ሰፊ ጥንቃቄና ሙያዊ ግዴታና ኃላፊነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው ሥራውን ለማከናወን የሰለጠነ ባለሙያና ቁሳቁስ መኖሩ የግድ መባሉ፡፡

ከዚህ ርዕሰ  ጉዳይ ጋር በተያያዘ አንድ መረጃ ጠቁመን እንለፍ፡፡ የሕክምና ባለሙያዎች ፅንሱ አይቋረጥ ብለው እንደሚመክሩ ሁሉ ፅንሱ ይቋረጥ ዘንድ የመከሩበትም ሁኔታ አለ፡፡ ይህም የሚሆነው የእናቲቱን ጤንነት በማገናዘብ ነው፡፡ ለምሳሌ እናቲቱ ከፍተኛ የልብ ድካም ችግር (Synotic heart disease) ያለባቸው እናቶች ወይም የልብ ድካም ችግራቸው ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ሳንባቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው፣ በሕክምናው ቋንቋ (Vardiac heart diseases with pulmonary hypertension) ያለባቸው ሴቶች እርግዝናውን መሸከም ወይም መቋቋም ስለማይችሉ ፅንሳቸው እንዳይቀጥል ወይም እንዲቋረጥ ይመከራል፡፡

በማጠቃለያችን አንደ ነገር ብለን እናብቃ አንዳንድ መረጃዎች እንደማጠቁሙት በሃገራችን ኢትዮጵያ በእናቶች ላይ ከሚደርሰው ሞት ከ30-50 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚወስደው በውርጃና ከውርጃ ጋር በተያያዘ ችግሮች

ሳቢያ የሚደርስ ሞት ነው። ስለዚህም ከትክክለኛው የሕክምና ባለሙያ ምክር ክትትል ውጪ ምንም ዓይነት የፅንስ ማቋረጥ (ውርጃ) እንዳይፈፀም ይመከራል ግድ ይላልም። ቸር እንሰንብት።

*************

# በውግና በልማድ የታሰሩ መብቶች

በሥራ አጋጣሚ ያገኘኋት ሴት በአንድ ድርጅት በባለጉዳይነት ለመስተናገድ ወረፋ እየጠበቀች ነበር፡፡ ዕድሜዋ በግምት ከ35 ዓመት አያልፍም፡፡ ጉስቁልናዋ ፊት ላይ ይነበባል፡፡ ከአጠቃላይ ሁኔታዋ ደግሞ በኑሮዋ የደላት እንደማትባል ታስታውቃለች፡፡ የተደራረተ ልብስዋ፣ የታቀፈችው ልጅ ንጭንጭ፣ ሀዘን ያጠላበት ፊትዋ ሁሉም ለኑሮዋ መስካሪ ይመስሉ ነበር፡፡ አሁንም አሁንም እያለቀሰ ሰላም ከነሳት የታቀፈችው ልጅም ይሁን ወንድምዋን ለማባበል ያልተሳካ ጥረት የምታደርገው ከፍ ያለች ሴት ልጅዋ እንቅስቃሴ ወ/ሮዋን በሐሳብ ርቆ ከመሄድ አላገዳትም፡፡

ወሬ ለመጀመር ያደረግኩት ጥረት ተሳክቶ የወይዘሮዋን ታሪክ ስረዳ ደግሞ አብረዋት ካሉት ልጆች ሌላ ሁለት ወንዶች ልጆች እንዳልዋትና ልጆችዋን ቤት ትታ መምጣትዋን ተረዳሁ፡፡ ጎረቤቶችዋን እንዲጠብቁላት በአደራ ሰጥታ ነበር ወደ ጉዳይዋ ያመራችው፡፡ ባለቤትዋ ጡረተኛ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ የኑሮ ሁኔታ ሲከብድ ቤት ውስጥ ይሠሩት የነበረው ልብስ ስፌትም አላዋጣ ሲል፣ ልጆቻቸውንና ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር ዘበኝነት ተቀጥረዋል፡፡

እዚሁ አዲስ አበባ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ እየኖረች ስለወሊድ መከላከያ ዘዴዎች ሳትረዳ አትቀርም የሚለውን ግምቴን ለማጣራት የግድ ስለሁኔታው እርስዋን መጠየቅ ነበረብኝ፡፡ መልስዋ ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ ከተለያዩ ምንጮች መስማትዋን የሚጠቁም ነበር፡፡ ነገር ግን በቤትዋ ውስጥ ያላት መብትና ተሰሚነት ወሊድ መከላከያ ለመጠቀም እስከ መወሰን የሚያርስ አልነበረም፡፡

ደጋግማ እንደነገረችኝ ኑሮዋ በአብዛኛው በልጆችዋ አባት ጥብቅ ቁጥጥር የሚመራ ነበር፡፡ በተለይ በዘበኝነት ከመቀጠራቸው በፊት ቤት ውስጥ የልብስ ስፌት መኪና ገዝተው ከሰፈርና ከጎረቤት የሚመጡላቸውን ሥራዎች ዝሰሠሩ እንደ ልብ መውጣት መግባት የማይታሰብ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ እርስዋ እንደምትለው ከጎረቤት ቡና እንዳትጣጣ፣ የለቅሶ ደረሳና የእዝኑን፣ የሌላውን ማኅበራዊ ጣጣ ሁሉ በእርሳቸው ላይ እንድትጥለው ይነግሯት ነበር፡፡ አባወራ

ናቸውና፣ የእርሷና የልጆችዋም ሕይወት በእርሳቸው ጡረታና ከልብስ ስፌት የሚገኝ ሳንቲም ላይ የተመሠረተ ነበርና ያሉትን መቀበል የግድ ነበር።
የወ/ሮዋ ሕይወት ከብዙዎቹ ከገጠር ወደ ከተማ ተሰደው የሚመጡ ሴቶች የለተየ አልነበረም። ከተወደችበት ሰሜን ወሎ ውስጥ የሚገኝ ገጠር ስትሰደድ የመጀመሪያ ማረፊያዋ ሸዋ ሮቢት ነበር። ያገኘችውን ስትሠራ ቆየች። አዲስ አበባ ግበት ሠራተኝነት መቀጠር እንደማያዋጣ ሰምታ በስደትዋ ገፋችበት። መጥታ ሰው ቤት ተቀጠረች። ከቀጣሪዎችዋ በአንዱ ቤት፣ ሦስት ዓመት በቆየችበት እያለች የልጆችዋን አባት ተዋወቀች።
ቆይተው ገጠር ሄደው የቤተሰቦችዋን ይሁንታ ተቀብለው፣ ወደፊት ሕጋዊ ጋብቻ እንደሚፈጽሙ ቃል በገቡላት መሠረት ቃላቸውን አምና በሚስትነት መኖር ጀመረች። ቃላቸው ሳይፈፀም ቀረ። የትምህርት ዕድል ባለማግኘትዋ ጥገኛ ሆና መኖርዋ የግድ ነበር። ከሁሉም በላይ አከግተትላ አራት ልጆች ወልዳለች። የልጆችዋን አባት ቁጣ ስለምትፈራ ስለወሊድ መቆጣጠሪያ አታነሳም። ጎረቤት ከሚገኙ ሴቶች ጋር እንዳትገናኝ በጥብቅ ስለተነገራትም ከጎረቤቶችዋ ስለሰማችው የወሊድ መቆጣጠሪያ አስፈላጊነትም ሆነ አከታትዬ መውለዱ በድህነት ሁኔታቸው ላይ ተደራራቢ ችግር እንደሚፈጥር የሰማችውን ምክር ማካፈል አትችልም።
‹‹ኢንተርናሽናል ፓረንትሁድ ፌዴሬሽን›› ያወጣው መረጀ እንደሚጠቁመው በኢትዮጵያ ከ15 እስከ 19 ባለው የዕድሜ ክልል ከሚገኙ ሴቶች ሦስት በመቶ የሚሆኑት ብቻ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን ተጠቅመው ያውቃሉ። ከእነኝህ መካከል አብዛኞቹ ደግሞ ተከታታይነት ባለው መልኩ ተጠቃሚ የሆኑ አይደሉም።
ይኸው ጥናት እንደሚለው በአብዛኛው የሀገራችን ማኅበረሰብ ዘንድ ወሊድ መከላከያ መጠቀም ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ መኖርን/ውስልትናን ያበረታታል የሚል አመለካከት አለ። በመሆኑም ወሲብ ከሚፈጽሙ የሀገራችን ሴቶች 25 በመቶው ብቻ ውንጠታማ በሆነ መልኩና በአግባቡ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን ይጠቁማሉ። በተለይ ከትዳር ውጪ በሚኖሩ ግንኙነቶች ውስጥ ስለወሊድ መከላከያ ዘዴዎች ተጠቃሚነት ማሰብ የማይቻል ነው።

ለዚህም ነው ጥንቃቄ በጎደለው ወሲብ ምክንያት በሚፈጠሩ እርግዝናዎች ሳቢያ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ አሁንም በመፈፀም ላይ የሆነው፡፡
ሌላው ቀርቶ ኮንዶም መጠቀም/ተጓዳኞቻቸው ኮንዶም እንዲጠቀሙ የሚጠይቁ ሴቶች ታማኝ እንዳልሆነ በመቁጠር በጥርጣሬ የሚታዩበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሴቶች ሙሉ በሙሉ በሥነ ተዋልዓደ ጤና መብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርጓቸውም ለሴቶች ዝቅተኛ ስፍራ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ ማኅበረሰባዊ ልማዶች ናቸው፡፡ እነኝህ ልማዶች ከሴቶች ሥነ ተዋልዶ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቀጥሉ እገዛ አድርገዋል፡፡ ከእነኝህ መካከል ተጠቃሽ የሚሆነው የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻና ጠለፋ ሲሆኑ ሴቶች የሥነተዋልዶ ጤና መብቶቻቸው ተጠቃሚ አለመሆናቸው ለኤች.አይ.ቪ ሥርጭት ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡
ያለዕድሜ ጋብቻ በሴቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና ላይ አደጋ እያስከተለ ያለ ክስተት ነው፡፡ ሴት ልጆች ከማን ጋር መቸ ወሲብ መፈፀም እንዳለባቸው የመወሰን መብታቸውን መገፈፋቸው ሳያንስ ባልዳበረ አካላቸው ወሲብ በመፈፀማቸው ለውስብስብ የጤና ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል ፊስቱላ አንዱና ዋነኛው ሲሆን፣ በለጋ ዕድሜ ከማርገዝ ጋር በተያያዘ በሚፈጠር ችግር ለሞት የሚዳረጉ ሴቶች ቁጥር ቀላል አለመሆኑ የሥነ ተዋልዶ መብቶች ጥሰት በሃገራችን ሴቶች ላይ እያስከተለ ያለውን ችግር አመላካች ነው፡፡
እንደ አስገድዶ መድፈር ያለ ድርጊቶች ደግሞ ሴቶች ከፈለጉት ሰው ጋር ወሲብ ለመፈፀም ያላቸውን ነፃነት የሚጋፉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ያለዕድሜ ጋብቻ ሴቶች ጤናማ ወሲባዊ ሕይወትና የወሳኝነት ሚና እንዲኖራቸው ከሚያግዙ እንደ ትምህርት እና በሲቪል ሕይወት መሳተፍ ያሉ ድርጊቶች የሚያግዱ ናቸው፡፡ በተለይ በሴቶች ላይ የሚሠሩ ተቋማት በተደጋጋሚ የሚያቀርቧቸው ሁኔታዎች እንደሚገልፁት ደግሞ የሴቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና መብቶች ጥሰት ሴቶች በሁሉም መስክ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው ዋና ምክንያት ነው፡፡ የግልና ግለሰባዊ ጉዳይ ከመሆኑ ባለፈ የሥነ ተዋልዶ ጤና መብትና ነፃነት ሴቶች የሌሎች መብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ሴቶች

በተጠበቀ ሁኔታ ሥነ ተዋልዶ ጤና መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ማድረጉ የሚጠቅመውም ለዚሁ ነው፡፡

የገዛ ራስ ሰውነትን ጠንቅቆ ማወቅ፣ በሥነ ተዋልዶ ጤና ሳይንስ አጠራር «ቦዲ ሊትረሲ» ሴቶች ሴትነታቸውን ሰውነታቸውን የሚገድቡበትንና ሥነ ልቦናዊ ፍላጐታቸውን መረዳት አለመረዳታቸውን የሚወስኑበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ፆታዊ ሁኔታዎችንና ከሥነ ተዋልዶ ጋር የተያያዘ ኅብረተሰቡ ነውር አድርጐ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ሴቶች በእውነታ ላይ ብቻ ተመስርተው እንዲወሰኑም የሚረዳቸው ነው «ቦዲ ሊትረሲ» የተሰኘው ፅንሰ ሐሳብ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ሲቪል ሊትረሲ ሴቶች መብቶቻቸውን የሚረዱበት በዚሁም መብቶቻቸውን ለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀት የማያገኙበትን ሁኔታ የሚጠቅስ ነው፡፡ ይልቁንም በቀጥታ በሚመለከቷቸውና ከሕይወታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባላቸው እንደ የወሲብ ሕይወታቸው ላይ የሚወስኑበትን በራስ የመተማመን የሚያገኙበት ነው፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ወይዘሮና መሰሎቿ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች እንዳላቸውም በማይረዱት መልኩ ስንት ልጆች መውለድ እንዳለባቸው፣ መቼና ምን ዓይነት የወሊደ መከላከያ መጠቀም እንዳለባቸው በነፃነት የመወሰን ዕድላቸውን፣ በኢኮኖሚ ጥገኝነታቸውና በሌሎች ምክንያቶችም ሊያረጋግጧቸው ያልቻሉ መብቶችንና ለማግኘት የሚረዷቸውም ናቸው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም የኢትዮጵያ ሴቶች ከሥነ ተዋልዶ ጤናና የከወሲብ ሕይወታቸው ጋር በተያያዘ በውሳኔ ሰጪነት ለመሳተፍ ከሚያግዷቸው ነገሮች አንዱ ሥራ አጥነት/በኢኮኖሚ ራስን አለመቻል ነው፡፡ ይኸው ጉዳይ ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ወሲብ እንዳይፈጽሙ፣ የልጆቻቸውን ቁጥር በተመለከተም መወሰን እንዳይችሉም አድርጓቸዋል፡፡

በአብዛኛው ሴቶች በዕድሜ ከሚበልጧቸው ሰዎች ጋር ጋብቻ መፈፀማቸው የወሲብ ሕይወታቸው ላይ ምንም ዓይነት ድምፅ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ሴቶቹ ዘግይተው መብቶቻቸውን እንኳን ባይሆን ወሊድ መቆጣጠሪያ የመጠቀም ዕድል መኖሩን ቢረዱም በቤተሰቡ ውስጥ የሚወሰኑ ውሳኔዎች፣ ምን ዓይነት ወሊድ መከላከያ መቼና እንዴት መጠቀም አለባቸው በሚለው

ጭምር ውሳኔ ለመስጠት ያላቸው የመደራደር አቅምና ተቀባይነት እጅግ አናሳ ነው።

መሠረታዊ ከሚባሉ መብቶች አንዱ የሆነው የሥነ ተዋልዶ ጤና መብት ለሃገራችን ሴቶች ሩቅ ሆኖባቸዋል። የወደፊት ዕጣቸውን ሙሉ በረመሉ ሊቀይር ከሚችለው ትምህርት የማግኘት ወሳኝ መብት ጀምሮ የሌሎች መብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉ ባሻገር ቀና ብለው እንዳይሄዱ ቀንበር ይጫንባቸዋል። ለኢትዮጵያውያን ሴቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና መብት በወግና በልማንደ የታሰረ መብት ነው። ወግና ልማዱን ጥሰው ወጥተው የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግም ብዙ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል።

****************

# የሴቶች ቀለማት - ነጭ ሐምራዊ እና አረንጓዴ

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1908 ቁጥራቸው 15 ሺሕ የሚጠጋ ሴቶች በኒውዮርክ ሲቲ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ነበር፡፡ በሰላማዊ ሰልፉ ላይ የተስተጋቡት ጥያቄዎችም አለቅጥ ረዝመው የነበሩ የሥራ ሰዓታት እንዲያጥሩ የሚጠይቁ፣ ሴቶች ለሥራቸው የተሻለ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲሰጣቸው አቤት የሚሉና ሴቶች የመምረጥ መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚጠይቁ ነበር፡፡ ይህ ዕለት ከ100 ዓመታት በኋላ ዛሬ የምናከብረው ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ተብሎ እንዲከበር ከተወሰነ ደግሞ ብዙ ዓመታት አልፈዋል፡፡

የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ይፋዊ ድረ ገጽ ያወጣው መረዳ እንደሚለው ማርች 8 በዓል ሆኖ እንዲከበር የሆነው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶች በዓለም አረጃ ለእኩልነትና ለለውጥ በጋራ ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ዕለት እንዲሆን ተወስኖ የተከበረው ደግሞ በ1911 (እ.ኤ.አ.) በኮፐንሀገን ነው፡፡ በያኔዋ ጀርመን ሶሻል ዲሞክራተክ ፓርቲ ኑወስጥ የግሰቶች ክንፍ መሪ የነበሩት ክላራ ዘትኪን ፀይህንኑ ቀን በይፋ በመመረቃቸው የማርች 8 ቀን ታሪክ ሰነሳ አብረው ይታወሳሉ፡፡ ይህንን ተከትሎ በዓለም ዙሪያ ያሉ የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች በየአገራቱና ባሉበት በመሆን ዓለም አቀፍ ቀኑን በራሳቸው መንገድ የሚያከብሩበትን ሁኔታ ማቀድ ጀምረው ነበር፡፡

እ.ኤ.አ. በ1909 በአሜሪካው ሶሻሊስት ፓርቲ አማካኝነት በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች የሴቶች ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲከበር በ1910 በኮፐንሀገን በተደረገ ዓለም አቀፍ የሶሻሊስት ስብሰባ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (የተወሰነ ቀን ባይቀመጥለትም) በዓለም እየተካሄዱ የነበሩ የሴቶች ንቅናቄዎችን ለመደገፍና የመመረጥ መመረጥ መብትን ለማምጣት የሚታገሉትን ለማገዝ በሚል ዓላማ እንዲከበር ሐሳብ ቀረበ፡፡ በዚያው ወቅት በ17 የዓለም ሀገሮች የንማገኙ ከ100 በላይ ሴቶች ይህንኑ ሐሳብ ደግፈው ነበር፡፡

ከዚየ በቀጠሉት ዓመታት ማርች 8 በተለያዩ ዓላማዎች እና መፈክሮች ሲከበር ቆይቷል፡፡ ከ1913 – 1914 (እ.ኤ.አ.) ለምሳሌ ለሰላም ጥሪ ማድረግና አንደኛ ውን የዓለም ጦርነት መቃወም በዚህ ሀገሮች የበዓሉ ዋና ግቦች ነበሩ፡፡ ከ1918 እስከ

1999 ባሉት ዓመታት ማርች 8 ባደጉትና ባላደጉት ሀገራት ሁሉ ዓለም አቀፍ መግባባት የተደረሰበት በዓል ለመሆን በቃ፡፡
ዛሬ በዓለም 14 ሀገራት (አብዛኞቹ የቀድሞው የሶቪየት ኅብረት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ አከል የነበሩ ናቸው) በዓሉ ብሔራዊ በዓል ሆኖ ሲከበር ያለው ባህል ወንዶች ለእናቶቻቸው፣ ለሚስቶቻቸው፣ ለሴት ጓደኞቻቸው እና ለሴት የሥራ ባልደረቦቻቸው አበባና ስጦታ የሚያበረክቱበት ሁኔታ ፈጥሯል፡፡
በዓሉ የፈጠረው የአንድነት መንፈስ ሴቶች መብቶችን ለማስከበር ከባድ ትግልና ንቅናቄ በተደረገባቸው በምዕራቡ ዓለምና ለአውሮፓ ሀገራት ሴቶች በሕግ መብቶቻቸው የተረጋገጡበትን ኑሀኔታ ፈጥሯል፡፡ በአደባባይ የሚሠሩ ሴቶች ቁጥር በርክቶ በሁሉም ዘርፍ ሁለቱ ፆታዎች መሳ ለመሳ የሆኑበትም እውነታ ሊታይ ችሏል፡፡ ይህንን ያየ የሴቶች እኩልነት የተረጋገጠ ሊመስለው ይችላል፡፡ ሆኖም ዛሬም እኩልና አንድ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ወንድና ሴት በኢንዱስትሪ በበለፀጉት ሀገሮች ሳይቀር የእኩል ክፍያ ተጠቃሚ አይደሉም፡፡
የወንዶች የበላይነት የሚንፀባረቅበት የንግድና የፖለቲካው ዓለም ቀርነተ በብዙ ሃገሮች በይፋ የዜጎች ሁሉ መብት እንደሆነ በተደነገገው በትምህርቱም ዓለም ሴቶች ከወንዶች እኩል እየሳተፉ አይደለም፡፡ የጤናውን ነገር አለማንሳት ነው፡፡ በብዙ የዓለማችን ክፍሎች የሴቶች ጤና፣ በተለይ በኤች.አይ.ቪ መከሰት ምክንያት አደጋ ውስጥ ወድቋል፡፡ በኃይል ሚዛን መዛባት (Gender imbalance) ምክንያት ሴቶች በወሲብ ሕይወታቸው ድምፃቸውን ማሰማት የሚችሉባቸው ሁኔታዎች እጅግ ጥቂት ናቸው፡፡
ወደ ሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ ማርች 89 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ሲከበር መቆየቱን እናውቃለን፡፡ በነገራችን ላይ የዘንድሮው በዓል ዓለም አቀፋዊ መሪ ቃል «በሴቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ዕድገትን መቅረጽ» የሚል ነው፡፡ በሀገራችን ዘንድሮ ዕለቱ የማከበርበት አገር አቀፋዊው መሪ ግቀል ደግሞ ስኬቶቻችንን እናክብር (Let us honour our successes) የሚል ነው፡፡
በአፍሪካ ደረጃ በሚካሄድ አንድ የመሪነት/ሊደርሺፕ ሥልጠና ፕሮግራም ላይ የተገኘ ወሳኝ መርህ ስኬትን ማክበር ለነገ በጐ ተግባር መነሻ መሠረትና

መነቃቂያ ሊሆን እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ የዘንድሮው የሃገራችን መሪ ቃል አውጪዎችም ይህንን መሪ ቃል መምረጣቸው ሁልጊዜ ያልተሠሩ ሥራዎችና አሉታዊ ነገሮች ላይ ብቻ ከማተኮር ጥቂትም ቢሆኑ ለተገኙ ውጤቶች እውቅና መስጠት ፀጋ እንዳለው በመገንዘባቸው ይመስለኛል፡፡ ለዚሁ አባባል ተጨማሪ ማጠናከሪያ የሚሆነኝ ሌላው ከላይ ከጠቀስኩት ሥልጠና የተገኘ መርህ ደግሞ ካለፈ ታሪካችን ወደፊት ይዘን የምንጓዘው ነገ ቢኖር በጣም የተሻለ የምንለው ነገር መሆን አለበት የሚል ነበር፡፡ ስለገሀነም ሀገራዊው መሪ ቃል ወሳኝ ትርጉም ያለው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

በሴቶች ጤና በኩል በተለይም በሥነ ተዋልዶ ጤና በኩል የምናከብረውና ጐልቶ እንዲወጣ የምንፈልገው ስኬትስ አለን ወይ የሚለውን ስንጠይቅ ደግሞ ለብዙዎቻችን ባዶ አየር ላይ እንደማፍጠጥ ሊመስል ይችላል፡፡ እጅግ ደሀ ከሚባሉት ሀገራት የምንመደብ በመሆናችን የጤና አገልግሎት ሽፋናችን አናሳ መሆኑ በተለይ መሠረተ ልማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች መሠረታዊ የሚባሉ የጤና አገልግሎቶችን መስጠት ሳይቻል ቆይቷል፡፡ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ከእነኚህ መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ጥራትና ስፋት በተመለከተ መሻሻሎች ቢኖሩም አሁንም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መጠቀም እየፈለጉ ሳያገኙ የሚቀሩ ሴቶች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ባለሙያዎች እንደሚሉት የእነኚህ ሴቶች ቁጥር ከአጠቃላይ የአገልግሎቱ ፈላጊ እስከ 35 በመቶ የሚሆነውን ቁጥር ይይዛል፡፡

ሆኖም በተለይ በሴቶች ጤና በኩል፣ ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የእናቶች ሞት አስጊ ደረጃ ላይ ባለበት ሀገር የምንኖር ብንሆንም እንኳን ይህንን ችግራችንን እንዴት እየተወጣነው ነው? የሚለውን መስማት በዋሻው ጫፍ በኩል ጭላንጭል እንደማየት ሊሆንልን ይችላል፡፡

ከተለመዱት እና በሥነ ተዋልዶ ጤና መጥፎ ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ ከሚገልጽልን መረጃዎች በተቃራኒ የጤና ሽፋንን በአጭር ጊዜ ለማሻሻል እየተወሰደ ያለን አበረታታች ጥረት መመልከት ለዚህ አባባል እንደ አንድ ምሣሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ ይህ ጥረት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን የማሠልጠንና የማሰማራት ፕሮግራም ነው፡፡

መንግሥት ዋነኛ የጤና አገልግሎት ሰጪ በሆነበት ሀገራችን በከተማና በገጠር ያለው የጤና ማዕከላት ስብጥር ኢ-ፍትሐዊ ነው። ይህንን ኢ-ፍትሐዊነት ለማስተካከል የተወሰደው ዋና ዕርምጃ ደግሞ ሠራተኞቹን አሠልጥኖ የጤና አገልግሎት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ማሠማራት ነው።
ይህንኑ ሐሳብ በተመለከተ «ፖፑሌሽን አክሽን ኢንትርናሽናል» የተባለ ተቋም በቅርቡ ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው የፕሮግራም ዓላማ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎቶችን ሽፋን በማሳደግ በ2009 በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጣውን አገልግሎትን ሽፋን የማዳረስ ዓላማ ማሳካት ነው ይኸው ፕሮግራም በመሠረተ ልማት አለመስፋፋት፣ የሠለጠነ የጤና ባለሙያ ከበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶች እጥረት የመሳሰሉት ችግሮች ቢጋረጡበትም እነኝህን ተቋቁሞ ለመሥራት የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፏል። መረጃው እንደሚለው ስትራቴጂዎቹ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞቹን በማሠልጠን የጤና መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ በሠራተኞቹ በኩል የፈዋሽነትና በመካከል ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በየገጠሩ ማጠናከር የሚሉ ናቸው።
መረጃው እንደሚለው የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በተለይ የጤና አገልግሎት የማግኘት ከፍተኛ ፍላጐትና ጥያቄ ባላባቸው የገጠር አካባቢዎች ወሳኝ ነው በዚህ አገልግሎት ምክንያት ለምሣሌ አሁንም አናሳ ቢሆንም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ጥያቄ ሊጨምር ችሏል። ምንም እንኳን አሁንም በቂ መረጃ ካለመኖር የተነሣ የመጠቀሙ ሁኔታ ወኑሰን ቢሆንም በአገልግሎቱ ላይ ባሉ አንዳንድ ችግሮች (ለምሣሌ የወሊድ) መከላከያ አቅርቦት መቋረጥ መኖራቸው ግን በገጠሩ አካባቢ ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ላይ ሠፊ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅ ያሳያል።
በመጨረሻም ዛሬ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች በዓል በቀን እንደመሆኑ ከላይ በርዕስነት ስላስቀመጥኩት የሴቶች ቀለማት ነገር ጥቂት ልበልና ጽሑፌን ላብቃ፡ ፡ የሴቶች ቀለማት ተብለው ዓለም አቀፍ እውቅና የተሰጣቸው ቀለማት ሦስት ሲሆኑ ነጭ፣ ሐምራዊ እና አረንጓዴ ናቸው። ትርጉማቸውም (የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ድረ ገጽ እንዳስቀመጠው) ነጭ ንጽህናን፣ ሐምራዊ ሕልውናን እና

ራስን ማክበርን፣ አረንጓዴ ደግሞ ተስፋንና አዲስ ሕይወትን የሚያመለክት ነው፡
፡

ቀለማቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጡትም ከሴቶች ሶሻልና ፖለቲካ ዩኒየን በዩናይትድ ኪንግደም እ.ኤ.አ. በ1908 ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ሦስቱ ቀለማት በአንድነት በአውስትራሊያና በሌሎች ሀገራት የተካሄዱ የሴቶች ንቅናቄዎችና ትግሎች መለያ ነበሩ፡፡ እነኝሁ ቀለማት በዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የሚለበሱ ሲሆኑ የባነሮችን የፖስተሮች ዋና ቀለማትም ሆነው ቆይተዋል፡፡

***************

# «ያሳለፍኩትን ጭንቅና ሕመም ሳስብ ወንድ ጋ ላለመድረስ መወሰኔን አስታውሳለሁ»

ባለታሪካችን የ23 ዓመት ወጣት ናት። ትምህርቷን ከ7ኛ ክፍል አቋርጣ ኬክ ቤት በገንዘብ ተቀባይነት ትሠራለች። የወንድ ጓደኛ የነበራት ዝሰሆን እርግዝናን ለመከላከል ሁልጊዜም ኮንዶም ይጠቀሙ ነበር። አንድ ቀን ሥራዋ ቆይታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ያላሰበችው ደረሰባት። ለእሷ ከቀኖች ሁሉ የተረገመች በሆነች ቀን የመከራ ዓይነቶች ተደራርበው ደረሱባት።

«አገር ደህና ብዬ መንገዴን ይዤ ስሄድ ዱርዬዎች ያዙኝና ፍላጎታቸውን እንድፈጽም አስገደዱኝ። የወሲብ ፍላጎታቸውን እየተፈራረቁ ተወጡብኝ። ሀዘኔ ከምንም በላይ ነበር።» ትላለች ሁኔታውን ስታስታውስ። በዚህ ዙሀኔታ መደፈሯ አካላክዋና መንፈሳዊ ቁስል አድርሶ የሚያቆም ብቻ አልነበረም። ተከትሎ እርግዝና መጣ። በዚያ ላይ መደፈሯ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አጋልጧት ስለመሆኑ እያሰበች ስጋት ውስጥ ነበረች።

የወንድ ጓደኛዋ ለጊዜው የደረሰባትን አይቶ ቢያፅናናትም ወዲያውኑ ባህርይው ተለወጠና ተለያዩ። አይዞሽ ባይዋ የምትተማመንባቸው እናትዋ ብቻ ነበሩ። ከእርሳቸው ጋር በመመካከርም ዘጠና ብር ከፍላ ዘመናዊ ሐኪም ቤት ሄዳ አስወረደች። የደረሰባት የመደፈር ድርጊትና የወንድ ጓደኛዋ እጅግ በሚያስፈልጋት ጊዜ መራቅ ተዳምረው ለወንዶች ያላት አመለካከት ጥሩ እንዳይሆን አድርገዋታል።

***

ሌላዋ ባለታሪክ የምትኖረው ከሰው ተጠግታ ሲሆን፣ ዕድሜዋ በወቅቱ 24 ዓመት ነበር። ትምህርቷን ከ3ኛ ክፍል ካቆመች በኋላ ለእሷ ሊገኝ የቻለው ሥራ በሆቴል አስተናጋጅነት መሥራት ነበር። አንድ ቀን አሠሪዋ ባል ይሆንሻል ብለው ደንበኛቸው ከሆነ ወንድ ጋር እንድትተኛ አስገደዷት። በወቅቱ ክብረ ንፅህናዋ በግዳጅ እንደተወሰደ፣ ስለወሊድ መከላከያ እና አጠቃቀም ምንም የማታውቅ የነበረ መሆኑንና ማርገዝዋንም ያወቀችው የምትሠራበት ቡና ቤት ባለቤት ሲያባርሯት ብቻ መሆኑን ትገልጻለች። የበለየ የተደናገጠችው ደግሞ ሴትየዋ

ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ አሳፍረው ሲልኳትና ከመጣችም ሰኋላ ለእህትዋ ለመንገር ባሰበች ጊዜ ነበር።
ባል ይሆንሻል ተብላ በግድ አብራ እንድትተኛ የተደረገችውንና የፀነሰችለትን ሰው ከዚያ ዕለት ወዲህ ዳግመኛ አላየችውም። ብታየው አታውቀውም። እህቷ ማርገዟን እንዳረጋገጠች ፅንሱን ማቋረጥ እንዳለባት ወሰነች። እሷም ተስማማች። እንዴት ይሆናል ለማለው ግን ውጤቱን ባለማወቋ ግን በፍርሃት ተውጣ ነበር።
«ምኞቴ ያገኘሁትን ሠርቼ ራሴን ማስተዳደርና ማሻሻል ነው። ሥራ ባገኝ ሰዎች እርጉዝ ሆኜ ቢያዩኝ እንደማይቀጥሩኝ አውቃለሁ። ብወልድም ከነልጄ የማቀጥረኝ አላገኝም። አባቱ የማይታወቅ ልጅም መውለድን አልፈልግም።» በማለት በውሳኔዋ ፀናች። መጠኑን አሁን የማታስታውሰውን ገንዘብ እህቷ ከፍላላት አንዲት ሴት ጋ በመሄድ ማህፀኗን ተነካክታ መራራ ፈሳሽ እንደትጠጣ ተደረገች። ያሳለፈችውን ጭንቅና ሕመም ስታስታውስ ከዚያ ወዲያ ወንድ ጋ ላለመድረስ ወስና እንደነበር ትናገራለች።

***

ታሪኮቹ በዚሁ አያበቁም፣ ብነቀጥል ይቀጥላሉ። ከፅንስ ማቋረጥ ወይንም በተለምዶ አጠራር ከውርጃ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያውያን ታሪኮች በዚህ ብቻ የሚያበቁ አይደሉም። ወይንም አይፓስ ኢትዮጵያ «ደኅንነቱ ያልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥና ውጤቶቹ የተጎጂዎቹ አሳዛኝ ገጠመኞች» በሚል ካዘጋጀው ቡክሌት እንደተወሰዱት ከላይ የተጠቀሱ ታሪኮች መጨረሻቸው ያማረ አይደሉም። አሀዞች እንደሚያሳዩት ደህንነቱ ባልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ ምክንያት የሚሞቱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ቀላል አይደለም። በሃገራችን ብቻ ሳይሆን በወሊድ መከላከያ አቅርቦትና ዕውቀት አላቸው የሚባሉትን የሠለጠኑ ሃገራት ጨምሮ በዓለም በየዓመቱ ከሚከሰቱት እርግዝናዎች ውስጥ 43 በመቶው የማይፈለግ ጽንስ ውጤቶች ናቸው።
በሃገራችንም ቢሆን ያልተፈለገ እርግዝና ሰለባ የሚሆኑት ወጣት ሴቶችና ከአቅማቸው በላይ የሚወልዱ ሴቶች ጭምር ናቸው። ሌላው ቀርቶ ደራርቦ የመውለድን ጉዳት አይተውትም ይሁን ከጤና ተቋማት በተሰጠ በትምህርት ገብቷቸው፣ ወሊድ መከላከያ ለመጠቀም ፈልገው የማያገኙ ሴቶች ቁጥር

አጠቃላይ በመውለድ ዕድሜ ክልል ካሉ ሴቶች ከ40 በመቶ በላይ እንደሚሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሥነ ሕዝብ ጽሕፈት ቤት /ዮኤን ኤፍፒ ኤ/ እ.ኤ.አ. በ2004 ያወጣው መረጃ እንደሚለው በሀገራችን የአንዷት ሴት አማካይ የውልደት መጠን (በመውለድ ዕድሜ ክልል ካሉት ሴቶች) በአማካይ 6 ልጆች ሲሆን፣ በገጠር ይኸው ቁጥር ከፍ ያለ መሆኑን የዓለም ባንክ በ2005 ያወጣው መረጃ ይጠቁማል፡፡
የኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበራት ቅንጅት ያወጣው መረጃ እንደሚለው ደግሞ ከኢትዮጵያውያን ሴቶች 40 በመቶ የሚሆኑት ዕድሜያቸው 19 ሳይሞላ ልጅ ይወልዳሉ፡፡ የዓለም ባንክ መረጃ (በ2004 የወጣ ነው) እንደሚጠቅሰው በመውለድ ዕድሜ ክልል ካሉ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑት 13 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ይኸው መረዳ አክሎ እንደሚያመለክተው ከአጠቃላይ የሀገራችን ወንዶች 17 በመቶው የዚሁ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ዘመናዊ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በገጠር ሴቶች ሁናቴ ስናየው ደግሞ ተጠቃሚዎቹ በመውለድ ዕድሜ ክልል ካሉት 4 በመቶዎች ብቻ ነው፡፡
ኢትዮጵያ አሁንም በእናቶች ሞት ተጠቃሽ ስትሆን ከ100 ሺሕ በሕይወት ከሚወለዱ ሕፃናት 671 የሚሆኑ እናቶች ይሞታሉ፡፡ ይህም (ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት እየቀነሰ የመጣና ከሁለት ዓመት በፊት ከነበረው ከ850 የወረደ ቢሆንም) ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች እንኳን ሲነፃፀር ከፍተኛ ቁጥር ነው፡፡ ለዚህ ቁጥር አንድ ተጠቃሽ ምክንያት/ወይንም ደግሞ አይፓስ ኢትዮጵያ ያወጣው መረጃ እንደሚለው ከአጠቃላዩ የእናቶች ሞት 50 በመቶ የሚሆነው የመጣው/ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ጽንስ ማቋረጥ ምክንያት ከ100 ሺሕ እርጉዞች 90ው እንደሚሞቱ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ ሲያስቀምጥ ያልተፈለገ እርግዝና መከሰት ያለ በመሆኑ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሉ የአገራችን ወጣት ሴቶች 50 በመቶ የጽንስ ማቋረጥ አገልግሎት ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተቀምጧል፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖ ቀደም ካለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተሻለ ሁኔታ ለሴቶች መብቶች በተለይም የሥነ ተዋልዶ ጤና መብቶች መከበር እውቅና ሰጥቷል። የተባለለትና በ1997 ፀድቆ የወጣው የወንጀል ሕግ ጽንስ ማቋረጥ የማያስቀጣቸውን ምክንያቶች ሰፋ ለማድረግ ችሏል። በዚህ መሠረት ሕጉ በሚፈቀደው ለምሣሌ ተገዶ መደፈር ያወጣው አልያም በዘመድ መካከል በተፈፀመ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈጠረ ጽንስ እንዲቋረጥ የሚያስችሉ አንቀጾች አካቷል።

በተጨማሪም በእናቲቱ ጤና ላይ ተፅዕኖ አደጋ ሊያስከትል የሚችል መሆኑና ጽንሱ የማይድን የአካል ጉዳት ያለበት መሆኑ ከተረጋገጠ የሚለው አንቀጾች ጽንስ ማቋረጥ በሕጉ ሊፈቀድ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ሆነው ተቀምጠዋል። በመሆኑም በእነዚህ ሁኔታዎች ሥራ ላሉ ሁሉ በመንግሥት የጤና ተቋማትና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት በሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል።

በመጨረሻም ድርጊቱ ከመፈጠሩ በፊት መከላከል ወሳኝ ነውና ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲያስችሉ ላልተፈለገ እርግዝና ያጋልጣሉ ከሚባሉ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን በመጥቀስ ጽሑፌን ላብቃ።

- ከወንድ ጓደኞቻቸው ጋር በመፈቃቀር በሚደረግ ግንኙነት ላለመውለድ በማወሰዱ ጥንቃቄዎች ላይ ስህተት መፈጠር
- በድንገተኛ ስሜት በመነሳሳት ወሊድ መከላከያ ለመጠቀም በማያስችል ድንገተኛ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ወሲብ መፈፀም
- ፍቅርን ለመግለጥና ኑሮሩ ለማቆራኘት ሲባል በሴቶች ፍላጎት ጽንስ ከተፈጠረ በኋላ በወንዶቹ ክህደት ሲፈጠር
- ሁለቱ ፍቅረኛሞች ልጅ እንዲኖራቸው ከወሰኑ በኋላ አንደኛቸው/ በተለይ ወንዱ ሐሳብ ሲቀይር
- በመዝናናት ወቅት በመጠጥ ኃይል በመገፋፋት የወትሮ ጥንቃቄዎችን መዘንጋት
- ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ የተሳሳተ ግንዛቤ መውሰድ ናቸው።

****************

# ኮረዳዋን ማን ገደላት?

ሰሞኑን አንድ ደብዳቤ ደረሰኝ። ደብዳቤው በእጅጉ ልብን ይነካል ሃዘንን ይጭራል ያኔ የከሌጅ ትምህርታችንን ያጠናቀቅን ሰሞን ለመምህርነት ሥራ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ካቀኑ ወዳጆቼ መካከል የአንዷ ደብዳቤ ነው። ይህንን እውነታ ለአንባቢዎችህ አድርሰው ብላ የፃፈችልኝ ነው። ለአንባቢያን እንዲመች አድርጌ እንዲህ አቅርቤዋለሁ።

እሁድ ጠዋት ነው። ወፎች የማለዳ ዝማሬያቸውን ሲየሰሙ ነበር ከእንቅልፌ የነቃሁት እናም የባጥ የቆጡን ሳስብ የዕለቷ ጀንበር ወከክ ብላ ወጣች። ዛሬ ከቀድሞ ተማሪዎቼ መሃከል የአንዷ ልጃገረድ ምስል ደግሞ ደጋግሞ ወደ ህሊናዬ ይመላለሳል። መሠረት ትባላለች። የዛሬን አያድርረውና መሠረት ከተማሪዎቼ መካከል እጅግ ጎበዟ ናት። በአንድ ወቅት ቀርቤ ሳወራት ራሷን የመለወጥና በትውልድ ቀዬዋ ያሉትን ጎጂ ልማዶች የመቅረፍ ህልም እንዳላት አውግታኝ ነበር። ግና ህልሟን ወደ እውነታ ለመለወጥ የጀመረችውን የድክ ድክ ጉዞ ሳታጋምስ በጅምር ቀረች። ገና 14ኛ ዓመት ልደቷን ከማክበሯ ቀድሞ ለአንድ ጎልማሳ ተዳረች። አለቀሰች ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። አብሬያት አነባሁ። ከጋብቻው ልታመልጥ የምትችልባቸውን የሃገራችንን ሕጎች ጠቅሼ እንደማድናት ቃል ገባሁለት። ግን እያለቀሰች ለመነችኝ በጉዳዩ ማንም ጣልቃ ሳይገባበት በቀላሉ የምታመልጥበት ብልሃት እንዳላት አወጋችኝ። እንዳለችውም በብልሃቷ ከጋብቻው ትድናለች ብዬ ስጠብቅ ደብዛዋ ጠፋ። ባለቤትዋ ይዟት መሰወሩ ተነገረኝ። የምሬን አለቀስኩ። የቅርበ ዘመዴ የሞተ ያህል አነባሁ። መሞኘቴ እንደ እግር እሳት አንገበገበኝ። ከወራት በኋላ ታዲያ የማርገዟን ወሬ ስሰማ በራሴ ተስፋ ቆረጥኩ። ሥራዬን ማቆምም ተመኝቼ ነበር። ግን ያ ሳይሆን እነሆ 10 ወራት አለፉ።

እናስ የተማሪዬ የመሠረት ታሪክ ከ10 ወራት በኋላ ለምን ዛሬ መንፈሴን ይረብሸዋልሳ አንዳች መጥፎ ስሜት እረፍት ቢነሳኝ የአከራዬን ልጅ ይዤ መሠረትን ትኖርበታለች ወደተባለው መንደር አቀናሁ። በበቅሎ የሦስት ሰዓታት መንገድ ነበር። ጉዞው አድካሚ ቢሆንም ከመሄድ ያገደኝ አልነበረም። ከመንደሯ ስንደርስ አንዲት መነኩሴት የመሠረትን የባልዋን ጎጆ ከመድረሴ አንዲት የ17

ወይም የ18 ዓመት ኮረዳ እጇን በቀሚሷ እያበሰች ወደ እኛ ቀረበች። መሠረትን ፍለጋ መምጣታችንን ስነግራት በሃዘኔታ አቀረቀረች። ከአፍታ ዝምታ በኋላም መሠረት ወሯ ገብቶ ኖሮ በድንገት ምጥ እንዳጣደፋትና ሙሉ ሌሊት ስታምጥ አድራ ስቃይዋ ቢጠና ዛሬ በጠዋት በቃሬዛ ተሸክመው ተሃኪም ዘንድ እንደወሰዷት ነገረችኝ። አዘንኩ። ሞተች የተባለ ያህል እንባ በዓይኔ ግጥም አለ። እንባዬንለመግታት ስል ብቻ የጥያቄ ናዳ ልጅቷ ላይ አወረውር ጀመር። ልጅቷ ግና ለእያንዳንዱ ጥያቄዬ ተገቢውን ምለሽ ከመስጠት ይልቅ በአግራሞት መመልከቷ ያመዝን ነበር። ልጅቷ በጥያቄዬ ወደመሰላቸት ከመግባቷ ቀድሞ ግን መንደሩ በለቅሶ ይታመስ ገባ።

አንዱ ከአንዱ እየተቀባበለ ከርቀት ይሰማ የነበረው ለቅሶ ይበልጥ እየቀረበ መጥቶ እኛ ካለንበት ከነመሠረት ግቢ ገባ። ለቅሰው ለመሠረት እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም። ያች ባለብዙ ራዕይ ባለብዙ ህልም ተማሪዬ ከነህልሟ አሸልባለች። ሌሊቱን ሙሉ ያሰቃያት ምጥ ወደ ሆስፒታልም ሳያደርሳት በቃሬዛው ላይ ሳለች ሕይወቷን ቀምቷታል። ቀንበጥ ወጣትነቷን ነጥቋታል። ለማንም ሰው እንዲህ አልቅሼ አላውቅም። ከአንጀቴ አነባሁ። ሕይወቷን ለመታደግ ብዙ ነገር ማድረግ ስችል አለማድረጌ አንገበገበኝ። ወዳጄ ያቺን እንቡጥ ኮረዳ ማን የገደላት ይመስልሃል። ያለዕድሜዋ በማህፀኗ የተሸከመችው ፅንስ ነው ትለኝ ይሆናል። ግን እሱ ብቻ አይደለም ይልቁንም ለሞትዋ ዋናው ተጠያቂ እኛ ነን። ቀድመን ልንታደጋት ስንችል በዝምታ ያለፍን እኛ እነማን ነን? ምንስ አጠፋን? ራስህንና አካባቢያችንን ጠይቅ? ምላሻችሁ ተግባርን ካልወለደ ግን በእርግዝናና በወሊድ ሳቢያ በየቀኑ በርካታ እህቶች በርካታ እናቶች መሞታቸውን ይቀጥላሉ። ታሪካቸውም እንደዘበት ተዳፍኖ ይቀራል። የምሰናበትህ በእንባ ተጋርጄ ነው። ቸር ይግጠመን ወዳጅህ ካለሁበት ገጠር።

የወዳጄ ደብዳቤ በእርግጥም ልብን በሃዘን ይሰብራል። ከርቀት ሳይሆን ከቅርበት ያሉ እህቶቻችንንና እናቶቻችንን ሕይወት በትኩረት እንድንመረምር ይጋብዛል። ወደራሳችን፣ ወደ ውስጣችን ጠልቀን እንድናይ ይገፋፋናል። የገጠሯ ኮረዳ የመሠረት ታሪክ የብዙ ሴቶች ታሪክ ነው። የሚሊዮን ኢትዮጵያውያን፣

አፍሪካውያንና የዓለም ሴቶች አሳዛኝ የዕውነታ ታሪክ ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት በፊት ለንባብ የበቃ የዩኒሴፍ መረጃ እንደሚጠቁመው ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ችግሮች ሳቢያ በየዓመቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ (515,000) የሚገመቱ ሴቶች ለህልፈት ይዳረጋሉ፡፡ ሌሎች በርካታ ሚሊዮን ሴቶች ደግሞ እርግዝናቸውና ወሊዳቸው በሚፈጥርባቸው ጣጣ ሳቢያ ለከፍተኛ የአካል ጉዳት ይጋለጣሉ፡፡

በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት ለሚከሰት ሞት በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም እንዲህ እንደ ኢትዮጵያዊቷ ታዳጊ፣ እንደ መሠረት በአፍላ የልጅነት ዕድሜ ማርገዝ ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ባለሙያዎቹ አበክረው እንደሚገልጹት የልጅነት ጉልበቷ ሳይጠነክር፣ የልጅነት አቅሟ ሳይበረታ በፊት ከ18 ዓመት በታች ባለ ዕድሜ ለእርግዝና የምትበቃ ወጣት ለሞት የመዳረግ አጋጣሚዋ ከፍተኛ ነው፡፡ አንዲት ሴት ከ18ኛ ዓመት ዕድሜዋ በኋላ ነው እንድታረግዝ የማመከረው፡፡ ከ18ኛ ዓመት በታች ባለው ጊዜ ማርገዝ አደጋው ለእናቲቱ ብቻም አይደለም ለሚወለዱት ሕፃናት ከመውለጃ ቀናቸው በፊት የመወለድ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው፡፡ የለጊዜው የሚወለዱ ልጆች ደግሞ ክብደታቸው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ እንዲህ ያሉት አነስተኛ ክብደት ይዘው የሚወለዱ ሕፃናት ታዲያ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው በፊት የመሞት አጋጣሚያቸው ከፍተኛ ነው የሚሆነው፡፡

በአፍላ የልጅነት ዕድሜ (ከ18 ዓመት በፊት) ማርገዝ አደጋ እንዳለው ሁሉ የመውለጃ ዕድሜ ከገፋ (ከ35ኛ ዓመት) በኋላ የሚመጣ እርግዝናም ለእናቲቱ ሆነ ለሕፃኑ ጤንነት አደገኛ እንደሆነ ነው የዩኒሴፍ መረጃ የሚጠቁመው፡፡ ከዕድሜዋ ከገፋው እናት በተጨማሪም በአራት ልጆች በላይ የምትወልድ እናት ለሞት የመዳረግ አጋጣሚዋ በእጅጉ የሰፋ መሆኑን ነው፡፡ ባለሙያዎች የሚመሰክሩት፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ አንዲት እናት ከአራት ጊዜ በላይ የምታረግዝ ወይም የምትወልድ ከሆነ ከአራተኛው እርግዝና በኋላ እንደ ደም ማነስና የደም መፍሰስ የመሳሰሉ ችግሮች በእናቲቱ ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡

በእርግዝናና በወሊደ ሳቢያ ለሚከሰት የእናቶች ሞትና ለሕፃናቱም የሕይወት ሕልፈት ተጠያቂ የሚሆን ሌላም ጉዳይ አለ። ይኸውም ልጅን ሳያራርቁ መውለድ ነው። ባለሙያዎቹ በወሊድ መካከል ያለው ርቀት ከሁለት ዓመት እንዳያንስ ነው የሚመክሩት። የወሊድ ወቅት ከሁለት ዓመት በታች ሲሆን የሕፃናት የሞት አጋጣሚ በእጥፍ ይጨምራል። ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ የተወለደ ሕፃን ከመት ቢያመልጥ እንኳ የአእምሮ ዕድገቱ ከሌሎች ሕፃናት ጋር ሲነፃፀር አብዛኛውን ጊዜ ዝቅተኛ ነው የሚሆነው።

በነገራችን ላይ ከወሊድ በኋላ የእናት ሰውነት የተሟላ ጥንካሬን ለማግኘትና ወደ በታው ለመመለስ በትንሹ የሁለት ዓመት ጊዜራ ይፈልጋል። ስለዚህም ከወሊድ በኋላ ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ዳግመኛ ማርገዝ ወይም ተጨማሪ ልጅ መውለድ በእናቲቱ ጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳትን በማድረስ ለሞት ሊዳርጋት ይችላል። ከዚህም ባሻገር የሚወለደው ሕፃን ከጊዜው በፊት ሊወለድና ዝቅተኛ ክብደትን ይዞ ሊወለድ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። ክብደታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሕፃናት ደግሞ በበሽታ የመጠቃት አጋጣሚያቸው ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከሌሎች ሕፃናት ጋር ሲነፃፀሩ የአንደኛ ዓመት ልደታቸውን ከማክበራቸው በፊት የመሞት አጋጣሚያቸው በአራት እጥፍ ከፍ ያለ ነው።

ችግሩን የሌሎ ችግር አድርገን አርቀን ካሰብነው ለመፍትሔ አንዷትም ዕርምጃ ላንራመድ እንችል ይሆናል። ግና ችግሩ የእናቶቻችን፣ የልጆቻችን እና የራሳችን እንደሆነ አናስብ። እናም የእኒህን የቅርብ ሰዎቻችንንና የራሳችንን ሕይወት እንታደግ። ዛሬ የምንወስዳት ቀላል የምትመስል ዕርምጃ ነገ የበርካቶችን ሕይወት ወደ ቀና መንገድ ትመራ ይሆናል። «አንድ መልካም ነገርን ማድረግ እንደምንችል ራሳችንን ካሳመንን በእርግጥም ማድረግ እንችላለን።» ለዛሬ ይብቃን - ሠላም ለእናንተ ይሁን።

# ሕፃናቱን ከኤች.አይ.ቪ ለመታደግ

በቅርቡ በተካሄዱ ጥናቶችና የወጡ መረጃዎች እንደሚሉት

- 2.2 በመቶ የሚሆነው የሀገራችን ሕዝብ ከቫይረሱ ጋር ይኖራል
- 75 ሺሕ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች በየዓመቱ ያረግዛሉ
- በየዓሙቱ 14 ሺሕ 15 ሺሕ የሚሆነው ሕፃናት ከቫይረሱ ጋር ይወለዳሉ
- ከቫይረሱ ጋር እንዳይወለዱ ለማድረግ የሚያስችለውን ሕክምና ማግኘት የሚችሉት በዓመት ከ2-5 ሺሕ የሚሆኑ ሕፃናት ብቻ ናቸው
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሕፃናትን ማከም አዋቂዎችን ከማከም ይልቅ ከባድ ነው

በአጠናቀቅነው ሳምንት የመጀመሪያ ሁለት ቀናት ይህንን አምድ ከአድማስ አድቨርታይዚንግ ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ የኢትዮጵያ ጽንስህ ማህፀን ሐኪሞች ማኅበር (ኢሶግ) መደበኛ ጉባኤውን አካሂደ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ማኅበሩ የተመሠረተበት 16ኛ ዓመትም አብሮ ተከብሯል፡፡ ማኅበሩ በየዓመቱ በሚያካሂደው ጉባኤ በእናቶችና ሕፃናት ጤና ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በተመለከተ ርዕሶችን መምረጥ ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲቀርቡና ውይይቶች እንዲደረጉ ያደርጋል፡፡ ከላይ የተመለከታችሁት አሀዝም በ16ኛው መደበኛ ጉባኤ ባለሙያዎች ከቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች የተወሰደ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጽንስና ማህፀን ሐኪሞች ፕሬዚዳንት በመሆን ላለፉት ሁለት ዓመታት ያገለገሉትና በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት እንዲገለገሉ በድጋሚ የተመረጡት ዶ/ር አሸብር ጋይም እንደገለጹልንና እኛም እንደተመለከትነው የዚህ ዓመት ገባኤ ዋና ርዕሰ ጉዳይ ከእናት ወደ ልጅ የኤች.አይ.ቪ መተላለፍ ሁኔታ በሃገራችን ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል? ክስተቱን ለማስቀረትስ እንዴት ይቻላል? በሚለው ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህ ርዕስ የተመረጠበትን ምክንያት ዶ/ር አሸብር ሲያስረዱ እንዳሉት 2.2 በመቶ የሚሆነው ማኅረሰባችን እንደሚያጠቃ ከሚነገርለት ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ጋር ተያይዞ በሚደረጉ ግምቶች 75 ሺሕ የሚሆነው ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሴቶች የሚያረግዙ ሲሆን፣ ሕፃናቱን ማከም

አዋቂዎችን ከማከም ይልቅ ከባድ ነው። መድሃኒት አወሳሰዱ እንዲሁ ዕድሜ ልክ የሚወሰድ ከመሆኑ ጋር ለሕፃናት ሲሆን፣ ከባድ ነው። ትልቁ ስትራቴጂ ሕፃናቱ ከቫይረሱ ጋር እንዳይወለዱ የሚያደርገውን ሕክምና ማድረስ የተቻለው ከ2 ሺሕ እስከ 5 ሺሕ ለሚሆኑት ሕፃናት ብቻ ነው። ይህንን ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ማዳረስና ሕፃናቱ ከቫይረዙሰ ጋር መወለዳቸውን ማስቀረት የሚቻለው ከእናቶች ጤና ክብካቤ ጋር የተያያዘ ተግባር የሚያከናውኑ ሁሉ ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲችሉ መሆኑን ዶ/ር አሸብር ይገልጻሉ።

አንዲት እርጉዝ ሴት ለጤና ክትትል በምትመጣበት ጊዜ ወይም ለመውለድ ስትመጣ (ይህ ጊዜ ወደ ጤና ማዕከል ለመምጣት የበጀመሪያዋ ከሆነ) ወይም ልጇን ለማስከተብ ስትመጣ ምክር ሊሰጣት ይገባል። ፈልጋው ከመጣችው አገልግሎት በተጨማሪ የኤች.አይ.ቪ ውጤቷን የማታውቅ ከሆነ ምክር የመስጠት ግዴታ ማንኛውም ባለሙያ ያለበት መሆኑን ይጠቅሳሉ። ምክር ተሰጥቷት ፈቃደኛ ስትሆን ተመርምራ ውጤቷን እንድታውቅ ማድረግ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች ደግሞ ወደ ልጃቸው እንዳይተላለፍ በቅርቡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኤች.አይ.ቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ ባወጣው መመሪያ መሠረት የሚታዘዙትን ክብካቤና መድሃኒቶችን ጭምር መስጠት ይገባል።

ማዋለድ ላይ ያለ ባለሙያጤናማ ልጆች ለማዋለድ ትልቁን ትኩረት ከመስጠት ባሻገር ኤች.አይ.ቪ በደሙ ይዞ የሚወለድ ሕፃን በቤተሰቡ ላይ የሚፈጥረውን ጤና በማየት ሊወልዱ የሚመጡ ሴቶች የሚመረመሩበትን ሁኔታ ማስታወስ የግድ ይላል።

ነፍሰጡር እናቶች ወደ ጽንሱ ቫይረሱን እንዳያስተላልፉ የሚያደርገው መድሃኒት ኖሩን መመሪያውም በግልጽ መሰጠቱ መልካም መሆኑን ዶ/ር አሸብር ይናገራል። ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለፈው ዓመት ባወጣው መረጃ መሠረት 52 በመቶ የሚሆኑት ኢትዮጵያዊ እርጉዝ እናቶች የጤና ክትትል እያደጉ መሆኑ ጥሩ ጅምር በመሆኑ እነኚህንና ከወለዱ በኋላ ለክትትልና ለወሊድ መከላከያ

የሚመጡትን እናቶች በአገልግሎቱ ውስጥ በማስገባት ብዙ እናቶችን መድረስ ይቻላል ይላሉ፡፡

ማኅበሩ ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ እንዳየተላለፍ በሚደረገው ሕክምናና የመከላከል ጥረት ሒደት ውስጥ ድርሻው ምን ነበር ወደፊትስ ምን ያደርጋል? ለሚለው ደግመ ዶ/ር አሸብር እያንዳንዱ የማኅፀንና የፅንስ ሐኪም እንደ ግለሰብ ማለትም የማኅሩ አባላት በያሉበት በየግላቸው እየሠሩ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ማኅበሩ አገልግሎቱ ያነሰባቸው አካባቢዎች የት ቦታ ናቸው? የሚለውን ለማየትና ክፍተቱን የመሙላት ተግባር ለማከናወን በአዲስ አባ ውስጥ ከከተማው የግጠና ቢሮ ጋር በተደረገው ንግግር የግል ተቋማት አገልግሎቱ አለመኖሩን ለይቶ ማወቅ በመቻሉ ይህንኑ ለማስወገድ በከተማው ባሉ የግል ሆስፒታሎችና አገልግሎት ሰጪዎች እንዲሁም 17 በሚሆኑ ልዩ ክሊኒኮች አገልግሎቱ የሚስፋፋበትን ፕሮጀክት ቀርጿል፡፡ ፕሮጀክቱ ጤና ባለሙያዎችን በማሠልጠንና አንዳንድ ቁሳቁሰችን በማሟላት ከሲዲሲ ኢትዮጵፖየ ጋር በመተባበር የሚካሄድ ነው፡፡ በአዲሰ አበባ ከሚሰጠው የጤና አገልግሎት 40 በመቶው በግሉ ዘርፍ የሚሸፈን በመሆኑ በግል ተቋማት አገልግሎቱን ማዳረስ ቀላል አለመሆኑን ዶ/ር አሸብር ሲናገሩ የዚህ ፕሮጀክት ውጤታማነት ታይቶ በሚቀጥለው ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማከሄድ መታሰቡን ተናግረዋል፡፡

በ16ኛው የማኅበሩ ጉባኤ ግን ሲቀርቡ የነበሩ እውነታዎችን በማየትና ወቅታዊ ደረጃውን በተመለከተ በቂ መረጃ በመያዝ የማኅበሩ አባላት በያሉበት በግል በመንግሥትም ይሁን በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ድርጅቶች ሳይቀር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማሳሰብ የተፈለገ መሆኑን ዶ/ር አሸብር ተናግረዋል፡፡

በዚሁ በማኅሩ 16ኛ መደበኛ ጉባዔ ወቅት ከቀረቡት ጽሑፎች መካከል በማኅበሩ ከእናቶች ወደ ሕፃናት ቫይረሱ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የሚካሄደው ፕሮጀክት አስተባባሪ የሰጡት ማብራሪያ ይገኝበታል፡፡ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ፋኩልቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በማስተማር ላይ የሚገኙት ዶ/ር ኢያሱ መስፍን ናቸው፡፡ ከጠቀሷቸው አንዳንድ ነጥቦች ውስጥ

በዘርፉ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያጋጥሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን በተመለከተ ያነሷቸውን አንዳንድ ነጥቦች ስንመለከት እናቶች በእርግዝና ወቅት ለክትትል ወደ ጤና ተቋማት አለመምጣታቸው ዋናው እንደሆነ ዶ/ር ኢያሱ ገልጠውልናል፡፡

ዶ/ር ኢያሱ እንደሚሉት በግሉ ዘርፍ የእርግዝና ክትትል የሚያደርጉና የሚወልዱ ግሰቶች ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ ከእናት ወደ ጽንስ ኤች.አይ.ቪ እንዳይተላለፍ የሚያስችለውን ሕክምና መስጠት አስፈላጊ መሆኑ እንዳለ ሆኖ አገልግሎቱ በግል ሲሰጥ ከመንግሥት የተለየ የሚያደርጉት ነጥቦች አሉ፡፡ ይኸውም የግሉ ዘርፍ ከትርፍ ጋር የተያያዘ ሥራ ከመሥራቱና አገልግሎት የሚሰጠው በክፍያ በመሆኑ በመንግሥት ሙሉ በሙሉ በነፃ ከሚሰጠው ኤች.አይ.ቪ ወደ ጽንስ እንዳይተላለፍ ከሚያደርገው ሕክምና ጋር ይለያያል፡፡ አገልግሎቱ በነፃ መሰጠት አለበት ከሚለውም መርህ ጋር አይሄድም፡፡ እናም በፕሮጀክቱ የግል የጤና ተቋማት የመድሃኒትና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲደረግላቸው በማድረግ በነፃም ባይሆን በተሻለና በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

ለዶ/ር ኢያሱ ያቀረብነው ሌላ ጥያቄ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሴቶች መውለዳቸው ተጨማሪ ጫና የሚያመጣባቸው መሆኑን ነገር ግን በአብዛኛው ቫይረሱን ወደ ሕፃናቱ እንዳያስተላልፉ የሚደረገው ጥረት ሕፃናቱ ላይ ብቻ ትኩረት ያደርጋል በሚለው ወቀሳ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነበር፡፡ በዚህ ላይ በቅርቡ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አማካኝነት በወጣው መመሪያ የመከላከል ጥረቱ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚኖሩት መቀመጡን ከእነዚህ አራት ክፍሎች አራተኛውና የመጨረሻው ለእናቶች ክብካቤና ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ለእናቶች ብቻ ሳይሆን ለቤተሰባቸውም ጭምር ክብካቤ እንደሚደረግ ለሕፃናቱ አባቶች ጭምር እንዲመረመሩ የሚበረታቱበት ሁኔታም እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡

********************

# ስለ ኤች.አይ.ቪ ዕውቀታችን የት ጋ ቆሟል?

- ዛሬም «ተመርምሬ የኤች.አይ.ቪ ውጤቴን ማወቄ ይጠቅመኛል» ከሚለው ይልቅ «ሳላውቅ ልሙት» የሚለው ይበዛል
- ፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት በነፃ ፀእንደሚሰጥ የማያውቁ ሰዎች አሉ
- ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የተገኘ ሰዎች አብዛኞቹ ቀጥለው የት መሄድ እንዳለባቸው አያውቁም
- ፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ከምግብ ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ ያለን ዕውቀት የተጋነነ ነው
- «መድሃኒቱን ካቆምክ ትሞታለህ» በሚለው መልዕክት ላይ ብቻ በመተኮሩ ለመድሃኒቱ ያለው አመለካከት አሉታዊ እንዲሆን አድርጓል

ባለፈው ሳምንት መጠናቀቂያ ላይ በነበርኩበት አንድ ፎረም የቀረበን ጥያቄ ነበር ከላይ እንደ ርእስ የተጠቀምኩት፡፡ በፎረሙ መነሻ ሐሳብ ያቀረቡ ዶ/ር ገብሩ ዳረጌ የተባሉ የፌደራል ኤች.አይ.ቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የኤች.አይ.ቪ ስፔሻሊስት ይህኑ ጥያቄ ደጋግመው አንስተውት ነበር፡፡ ለዚሁ ተደጋጋሚ ጥያቄ መነሻ የሆናቸው ደግሞ በሚያከናውኗቸው የተለያዩ ጥናቶች የሚያጋጥሟቸው እውነታዎች ናቸው፡፡ እነኝህ እውነታዎች የሚያሳዩት ደግሞ ዛሬም «ተመርምሬ የኤች.አይ.ቪ ውጤቴን ማወቄ ይጠቅመኛል»ከሚለው ይልቅ «ሳላውቅ ልሙት» የሚለው መብዛቱ፣ ዛሬም ፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በነፃ መቅረቡን ባለመረዳትም ይሁን ባለማወቅ መድሃኒት በኮንትሮባንድ ገብቶ በውድ ዋጋ የሚሸጥ፣ ለእነሱ ፈጽሞ የማይታሰብ መሆኑን የሚገምቱ ሰዎች መኖራቸው ናቸው፡፡

አሁንም በተለይ ከጤና ሴክተሩ ውጪ ያሉ ሁኔታዎች ኤች.አይ.ቪ ኤድስን የመከላከሉን ዘመቻ አስቸጋሪ እንዳደረጉት፣ በዚህም ምክንያት ሰዎች ከነበራቸው ሕይወትና ተደጋግሞ ከመታመማቸው ጋር ቢጠረጥሩም ለመመርመር ወደ ጤና ጣቢያዎች እየመጡ እንዳልሆነ ነው የሚሰማው፡፡ የኤች.አይ.ቪን ታሪክ የቀየረ የተባለበት ፀረ- ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ተጀምሮ ሰዎች ቫይረሱ በጥድፊያ ወደ ኤድስ ተቀይሮባቸው ወደ ሞት መሄዳቸው

ቀርቷል። ሆኖም ዶ/ር ገብሩ እንደሚያምኑት ፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት በነፃ ከ5 ዓመት በፊት ሲጀመር በቂ መረጃ የተሠራጨበት ሁኔታ አልነበረም። ትኩረት የተሰጠውም «መኑደሃኒቱን ካቆምክ ትሞታለህ» ለሚለው መልዕክት ላይ ብቻ ነበር። ይህም ሰዎች ለመድሃኒቱ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ እንዲሆን፣ መድሃኒቱ የአኗኗር ሁኔታቸውን፣ በአጠቃላይም ኑሯቸውን እንደሚያሻሽልላቸው ሳይሆን ሞታቸውን እንደሚያፋጥነው አድርገው እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል።

የኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ከተቋረጠ ይገድላል መባሉ በሰዎች ዘንድ መጥፎ ስሜት ፈጥሯል። በአንፃሩ አንድ ቀን መድሃኒት መድሃኒት ስላልተወሰደ አይሞትም። ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነገረው አባባል ከፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ጋር የተመጣጠነ ምግብ አብረህ ካልወሰድክ ትሞታለህ የሚል ነው። ዶ/ር ገብሩ እንዳሉት ግን የምግብና ፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ተዛምዶ የሚነገርለትን ያህል አይደለም። መድሃኒቱ ሲወሰድ የሥነ ልቦናም ይሁን የማግተሪያል ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑ እንዳለ ሆኖ የተለየ ምግብ መብላት መድሃኒቱ በተለየ ሀኔታ እንዲሠራ የእንደሚያደርግ መወራቱ ግን ተገቢ አይደለም።

ከዚህ ሌላ መድሃኒቱ በተለይ በተጀመረባቸው ዓመታት ያሉትን ጥሩ ያልሆነ ተፅዕኖዎች በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች የመሠራጨታቸው ጉዳይ ነው። በፎረሙ የተገኙት ተወያዮች ስለዚሁ ጉዳይ የተለያዩ ጥያቄዎች ያነሱ ሲሆን፣ ዶ/ር ገብሩ በሐኪም ክትትልና በሌሎች አጋዥ ማስታገሻ መድሃኒቶች ይህ ሊቀር እንደሚችል ጠቁዋል። በተለይ በመንግሥት የጤና ተቋማት ከሥራ ብዞት የተነሳ መድሃኒቱን የሚወስዱትን ሰዎች ችግር ለመስማትና መፍትሔ ለመፈለግም ጊዜ ላይኖራቸው እንደሚችል ተገልጿል።

በእነኝህና በሌሎች ምክንያቶች የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ለምሳሌ በአዲስ አበባ በሁሉም ጤና ጣቢያዎች አገልግሎቱ ያለ ቢሆንም ሰዎች ግን እየተገለገሉበት አይደሉም። አሁንም ሰዎች ተመርምረው ውጤታቸውን ካወቁ በኋላ የሚቀጥለው ሒደት ምን መሆን አለበት? እንዲሁም የሚያስፈልጋቸው እንኳን ቢሆን ፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ሊያገኙ የሚችሉበትን ቦታ

አያውቁትም፡፡ ሆኖም ግን የት መሄድ አለበት? የሚለውን ለይቶ ማወቅ መረጃዎችንም አስቀድሞ መሰብሰብ ተገቢ ነው፡፡
ከፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ጋር ተያይዞ ቫይረሱ በደማቸው የተገኘ ሰዎች መድሃኒቱን መውሰድ አለባቸው? የሚገባቸው ደረጃ ላይ ደርሰዋል? የሚለውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምርመራዎችን ለማድረግ (ለምሳሌ ሲዲ ገፈር እና ቫይራል ሎድ ለማወቅ) የሚደረጉ ምርመራዎች የሚካሄዱባቸው ማሽኖች መበላሸት በተለይ በክልል የመንግሥት ሆስፒታሎችና የጤና ማዕከላት የተለመደ መሆኑ ሲገለጽ፣ ይኸውም በግል አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቀው ክፍያ ከፍተኛ መሆኑ ችግሩን እንደሚያወሳስበው ግልጽ ነው፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ የከፋ ነገር አለመኖሩን ይህንነ በተያዩ ዘዴዎች ጭምር ማወቅ እንደሚቻልም ነው የተነገረው፡፡
ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይም የኤች.አይ.ቪ ጉዳይ ይወራበት የነበረውን ዘመን እንደረሳነው የሚያሳዩ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ የመጠንቀቅ ጉዳይም ይሁን የ‹‹ሦስቱ መዎች›› ክፍለ ዘመን አልፏል፡፡ ከኤች.አይ.ቪ እንድንጠነቀቅ የሚነግሩን መዝሙሮች፣ መልዕክቶች፣ እንዲሁም ፖስተሮች እንኳን በየቦታው መኖራቸውንና ኤች.አይ.ቪን ማስታወሳቸውን ትተዋል፡፡ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ምርመራ፣ (ምንም እንኳን አሁንም በነፃ አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ዝርዝር በየቦታው ቢለጠፍም ምን ያህል ሰዎች እየሄዱ ይመረመራሉ ዘመቻው ሰዎች ወደ ምርመራ ጣቢያዎች ምን ያህል እየሄዱ ነው የሚለው መረጃ ብዙም ሲሰጥ አይታይም፡፡) የባለሥልጣናት የመመርመር አርአያነት ወዘተም የተረሱ ጉዳዮች ሆነዋል፡፡
ነገር ግን ወሬው መረሳቱ የኤች.አይ.ቪ ሥርጭት መቆሙን አያሳይም፡፡ የምናያቸው የወጣቱ ባህርያት ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ያሉ ብዙ ዜጎች ባሉባት አገር መታየት እንዳለበት አይደለም፡፡ በተለይ በኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች አካባቢ ከሌላው የከተሞች ይልቅ የቫይረሱ ሥርጭት በብዙ እጥፍ ከፍ ያለ መሆኑ የማያሳየውም የዚህኑ ውጤት ነው፡፡ ኤችአይቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በቅርቡ ያወጣ ው ሪፖርትም እነኚህ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በተለይም

አዳዲስ በሚከፈቱባቸው አካባቢዎች የቫይረሱ ሥርጭት ጨምሮ መገኘቱን ነው ያመለከቱት።

ኤች.አይ.ቪ በዓለማችን ከተከሰቱና የተመራማሪዎችንና የሳይንስን ቀልብ በእጅጉ ከሳቡ ክስተቶች ቀዳሚው እንደመሆኑ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች እየተካሄዱበት አዳዲስ ውጤቶች እየተገኙበት ያለ ዘርፍ ነው። ኤች.አይ.ቪ ወደ ኤድስ ለመለወጥ ጥቂት ዓመታት ፈጅቶ ያለመፍትሔ ወደ ውጤት የሚኖድበት ዘመን ያለፈውም በእነኝህ ምርምሮች ውጤት ነው። እኛም የኢትዮጵያውያን እውቀት ግን ኤች.አይ.ቪን በተመለከተ የጠራ አይመስልም። ብዙዎቻችንን ኤች.አይ.ቪ ነቃ ብለን እንድንኖር፣ የሕይወታችንን አቅጣጫ እንዴት ማስኬድ እንዳለብን፣ ብንዘናጋ ሊደርስብን ስለሚችለውም ችግር ያወቅን አንመልስልም በአጠቃላይም የወሲብ ባህሪና አኗኗር ፈጽሞ የተለወጥንበት አካባቢ አይመስልም።

ይህንን የምለው ያለ ምክንያት አይደለም። ከላይ ባያችሁት የኢሜይል አድራሻ ከሚላኩ አስተያየቶች፣ በተለይም ጥያቄዎች አብዛኛውን ድርሻ የሚይዙት ግላዊ ጥያቄዎች ናቸው። በግል የምንጠይቅዎት ጥያቄ እስከ ዛሬ እንደተደረገው በግል የሚመለስና ወደዚህ መድረክም ጨርሶ የማይመጣ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ስለወጣቶች ባህሪ የሚለው ብዙ ነገር እንዳለ ግን ግልጽ ነው። ይኸውም ወጣቶቻችንን በተለይም ሴቶቹን የሚያሳስባቸው ከኤች.አይ.ቪ ይልቅ ያልተፈለገ እርግዝና ጉዳይ ነው። በምን መልኩ በተፈጥሮ መከላከያ ዘዴ ተጠቅመው እርግዝናን ማስቀረት እንደሚችሉ ማወቅ ይፈልጋሉ። አልያም ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ የሚገኝበትን ማወቅ ያስጨንቃቸዋል። ማለት የምንፈልገው ግን በኤች.አይ.ቪ የመያዝ አጋጣሚ ከእነኝህ ችግሮች ሁሉ በላይ ሊያሳስበን የሚገባ ጉዳይ ነውና ራሳችንን መጠበቅ ይገባናል ነው።

********************

# በለጋ ወጣትነት ወሲብ መጀመርና ውጤቶቹ

አንዳንድ ጊዜ ሳናስተውልና አርቀን ሳናስብ የምናደርጋቸው ነገሮች በኋላ ላይ ዕድሜያችን ገፍቶና በሕይወታችን አንዱ ክፍል የማንፈልገውን ዓይነት ውጤት ግሊያመጡ ይችላሉ። ለማንኛውም ጉዳይ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ይህ ጉዳይ ከወሲብ ሕይወታችን ጋር በቀጥታ የሚያያዝና ብዙውን ውጤቱም በግልጽ የሚታይ ነው። ከቀላል ምሳሌ ብንጀምር ለስሜታችን ተገዝተን ያለጥንቃቄ የምናደርገው ወሲብ ላልተፈለገ እርግዝና ሊያጋልጠን ይችላል። ይህም ንፅህናው ያልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ ውስጥ እንድንገባ ሊዳርገን ይችላል። በዚህም ሳቢያ ልጆች ለመውለድ ስንፈልግ እንዳንወልድ የሚያደርጉ ችግሮች ሊፈጠሩብን ይችላል። በተጨማሪም ይኸው ለጥንቃቄ የሚደረግ የወሲብ ግንኙነት ለኤች.አይ.ቪ ኤድስና ለአባላዘር በሽታዎች ወዘተ ያጋልጠናል። በውጤቱ እንደሚከተለን ዓይነት ሁኔታ የሕይወታችን አቅጣጫ በጥቂቱና ሙሉ በሙሉ ሊቀየር ይችላል።

ይህንን ገጽ ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች እንዳወቅነውና እንደተነጋገርነው ከኤች.አይ.ቪ መምጣት በፊት በነሩት ዓመታት ቀደም ብሎ የወሲብ ሕይወት እንዲያው እንደነገሩ ነበር። በዛሬ በቋንቋና አገላለጽ ልቅ ወሰብ የሚባለው እውነት ያኔ አልነበረም። ወይንም በልቅ ወሲብ ምክንያት የሚመጡብን ቀውሶች ያን ያህል አስጊ አልነበሩም። ከዚህ አልፎ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ (የአባላዘር) በሽታዎች እንደ ከባድ ታይተው ለዚህ የተጋለጡ ሰዎች የሚወቀሱበት ሁኔታ የነበረ አይመስልም። በዕድሜ የገፉት (ቀደም ብሎ በዚህ ገፅ ጭምር እንዳነበባችሁት) እንደሚሉት እንደ ልብ ላለመሆን ግዴታ የጣለው የኤች.አይ.ቪ ሥጋት ነው።

ነገር ግን በአባላዘር በሽታዎች የመያዝ ሁኔታ እንደሚታሰበውና ድሮ እንደሚባለው «ቦርችሌ» ሄዶ ተሰልፎ አንደ ቀን ክኒን አምጥቶ ያንን በመውሰድ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ጉዳቱ ከዚህም የዘለለ ሊሆን የሚችልባቸውም ብዙ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች የተለያዩ ዓይነት ዘላቂ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም። ሆኖም ይህ ጉዳትና ተፅዕኖ በሰፊው እንዳይወራ

የኤች.አይ.ቪ ጉዳይ መጥቶብን ሌሎቹን የአባላዘር በሽታዎች ከዘነጋናቸው ቆየን። ለነገሩ ኤች.አይ.ቪ ጉዳይ መጥቶብን ሌሎቹን የአባላዘር በሽታዎች ከዘነጋናቸው ቆየን። ለነገሩ ኤች.አይ.ቪን ለማስቀረት ሊኖረን ስለሚገባው ጤናማ ባህሪ አንድ በአንድ የመወሰንና ኮንዶም የመጠቀምንም ጉዳይ አጠንክረን እየሄድንበት ኅብረተሰባችንም ለእነኝህ መርሆዎች እየተገዛ አይደለም። ዛሬ የረሳናቸውን የአባላዘር በሽታዎች ጉዳይ እንድናነሳ ያስገደደንም ይህ ጉዳይ ነው።

የአባላዘር በሽታዎችን የመከላከሉ ነገር ኤች.አይ.ቪን ለማስቀረት የሚደረገው ጥረት አንድ አካል መሆናቸው ግን ግልጽ ነው። ስማቸው እንደሚገልፀው የአባላዘር በሽታዎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ናቸው። በጥቅሉ ለእነኝህ በሽታዎች ሊያጋልጡ ይችላሉ ተብለው የሚታመኑት ደግሞ ወሲብ በወጣትነት ዕድሜ (ቀደም ብሎ) መጀመር፣ ከአንድ በላይ የወሰብ ጓደኛ ማበጀት (እዚህ ላይ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከአንድ ሰው ጋር ብቻ እየፈፀሙ ነገር ግን እንደመሳሳም ያሉትን ቅርበች ከአንድ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ማድረግ ለበሽታዎቹ ሊያጋልጥ እንደሚችል ተጠቅሷል) እንዲሁም ያለ ምንም ጥንቃቄ (መከላከያ) ግንኙነት መፈጸም ናቸው።

እዚህ ላይ ስለእነኚህ በሽታዎች መረጃ ያገኘሁባቸው ድረ ገፆች ያሰፈሩትን መረጃ መግለጽ አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳን ራሱን የቻለ ርዕስ የሚያስፈልገው ወደፊትም ልንመለስበት የምንችለው ቢሆን የኮንዶም ጉዳይ ወሳኝ በመሆኑ ሊነሳ ይገባል። ይኸውም የምንጠቀምበትን ኮንዶም ስንወስን ጥንቃቄ ልናደርግና በቂ እውቀትም ሊኖረን የሚገባ መሆኑ ነው። ወደ ሃገራችን የሚገቡት ኮንዶሞች ጥራታቸውን የጠበቁ ለመሆናቸው የሚመለከተው አካል ተገቢውን ፍተሻ እያደረገ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ቢቻልም እንኳን መረጃ ጠቃሚ ነውና ሊጠቀስ የግድ ነው።

እንደመረጃዎቹ ልንጠቀመው የሚገባውና ከአባላዘር በሽታዎችና ከኤች.አይ.ቪ ሊከላከል የሚችለው ከላቴክስ (Latex ከተባለ ማቴሪያል) የተሠራ ኮንዶም ብቻ መሆኑ ነው። ካልሆነ ግን ሌላ ዓይነት ኮንዶሞች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን የሚያመጡ ተህዋሲያንን የሚያሳልፉ ሊሆኑ

የሚቻላቸው ነገር በመረጃዎቹ ተሰምሮበታል፡፡ ከዚህ ሌላ እንደ ዲያፍራምና ስፓርሚሳይድ ያሉ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን እርግዝናን እንጂ በግብረ ሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎችን ሊከላከሉ እንደማይችሉ ሊታወቅ ይገባል፡፡
የአባላዘር በሽታዎች ነገር ሲነሳ አብሮ የሚነሳው በተለይ ቀደም ብሎ ባለዙወና በለጋ ወጣትነት ወቅት የሚፈጸመው ወሲብ ያለ ጥንቃቄ የመፈጸም ዕድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ ለጋ ወጣቶች ኮንዶም ለመጠቀም ቢያስቡ እንኳን ከየት ያገኛሉ? የሚለው አሳሳቢና የመግዛቱም ሁኔታ (ከዋጋው አንፃር ባይሆንም ለወጣቶቹ ከሚሰጠው ቦታ አንፃር) አሳፋሪ ከመሆኑ ጋር የማይታሰብ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ወቅት በአባላዘር በሽታዎች የመያዙ አጋጣሚ ኖረ ማለት ደግሞ ከኋላ ሕይወት ጠንቅ የሚሆን ውጤት ሊያስከትል የመቻሉ አጋጣሚ ሊኖር ቻለ ማለት ነው፡፡
እነኚህ በሽታዎች ሊኖራቸው የሚችለውን ዘላቂ ጉዳት በጥቂቱ ለመመልከት ከሚታወቁት ዋና ዋና በግበረ ሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎች ብናነሳ ቻላሚዲያ እየተባለ የሚጠራውና ጥንቃቄ በጎደለው ግንኙነት የሚከሰተው የአባላዘር በሽታ በወቅቱ ካልታከመ በወንዶች የፕሮስትት ዕጢን በማሳደግ የመራቢያ አካላት ተርባራቸውን በአግባቡ እንዳያከናወኑ ያደርጋል፡፡ በሴቶች ላይ ደግሞ ከሚያመጣባቸው ጉዳት መካከል በእርግዝናቸው ወቅት ወደ ፅንሱ ሊተላለፍ ይችላል፡፡
ሌላው በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ በብዛት የሚታወቀውና ጨብጥ እየተባለ የሚጠራው በሽታ ሲሆን የልብና የሆድ ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል፡፡ በወቅቱ ካልታከሙት ብቻ ሳይሆን የታዘዘልዎትን መድሃኒት በሚፈልገው መፀልኩ ካልወሰዱ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ኢንፌክሽኖች የልብ ችግር የቆዳ በሽታ እና የዓይን መታወር ሊያጋጥምዎ ይችላል፡፡ ሌላው በሽታ ቂጥኝ ከፀጉር መርገፍና በቆዳ ላይ ሽፍታ ከማውጣት ይጀምርና የአንጎልን ሥራ ወደ ማቆም ሊዘልቅ ይችላል፡፡
በአብዛኛው ከጨብጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣውና በሴቶች ላይ የሚከሰተው «ፕልቪክ ኢንፋላማቶሪ ዲዚዝ» በሴቶች ላይ የመሃንነት ችግር ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡ በሴቶች ላይ ከሚከሰቱ የመሃንነት ችግሮች 30 በመገተው የሚሆኑት በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ የአባላዘር በሽታዎች ሳቢያ የሚመጡ ናቸው

በጨብጥ ከሚጠቁ ሴቶች ከ10 እስከ 40 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ፔልቪክ ኢንፍላዳቶሪ ዲዚዝ ለተባለው በሽታ ተጋላጭ ናቸው።
ሌላው አደገኛ (የአባላዘር) በሽታ ሄፒታይተስ እየተባለ የሚጠራ ሲሆን፣ ከመተላለፊያ መንገደች አንዱ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። ይህ በሽታ በጣም አነስተኛ (ወይንም ምንም ዓይነት) ምልክቶችን የሚያሳይ ሲሆን፣ የድካም ስሜት ከእነኝህ ምልክቶች ይገኝበታል።
ሄፒታይተስ ምንም ዓይነት መድሃኒት የሌለው ሲሆን፣ ምልክቶቹን ግን ማከም ይቻላል። ምልክቶቹ ካልታከሙ የጉበት መበላሸት፣ የጉበት ካንሰር ብሎም ዓመት ሊያስከትል ይችላል ካልታከሙ ከእናት ወደ ጽንስ ሊተላለፍ የሚችል ነው።
በአጠቃላይ ግን ልናውቀው የሚገባን ነገር በግብረ ሥጋ ግንኙነት የማተላለፍ በሽታዎች ወደ ሐኪም ዘንድ ቀርቦ ለመታከም የማያስደስቱ ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይ በሀገራችን በአጠቃላይ ለሕክምና ካለን ግምትና በአጠቃላይም ሕመም ሲሰማን ወደ ሐኪም ቤት ከመሄድ ይልቅ በተለያየ ዘዴ ራሳችንን ለማከም ጥረት የምናደርግ በመሆኑ በሽታዎቹ ስር ከሰደዱ በኋላ ልናውቃቸው/ ወደ ሕክምና ልንሄድ የመቻላችን አጋጣሚ ሰፊ ነው። ነገር ግን በጊዜ ሐኪም ቤት ከሄድን ዘላቂ ጉዳት ሳያመጡ ልንደርስባቸውና ጥንቃቄ ብናደርግ ልንከላከለቸው እንችላለን። በተለይ በመራቢያ አካላቶቻችን አካባቢ ትንሽም ቢሆን ለየት ያሉ ስሜቶችና ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወደ ሐኪም ዘንድ መሄድም ኋላ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን የማይጠገን ጉዳት ለማስቀረት ያስችላል።

********************

# የወሲብ ፊልም ውጤቶች

- የወሲብ ፊልሞች በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ጥቃቶችን ያባብሳል?
- ፖርኖግራፊ መመልከት የተቃራኒ ጾታ ፍቅርን ይቀንሳ?
- ፖርኖግራፊ ለቤተሰብ መበተን ምክንያት ሊሆን ይችላል?
- የወሲብ ፊልሞች ሴቶች እንደ ወሲብ ዕቃ እንዲተዩ ያደርጋሉ?
- አደገኛ ወሲብ ባህሪ እንዲያዳብሩ ያደርጋል?

## በዓለማችን ፖርኖግራፊ

- ከ10 ቢሊዮን በላይ ዶላር በየዓመቱ ገቢ ያስገኛል
- ፖርኖግራፊ ከሚመለከቱት አብዛኞቹ ዕድሜያቸው ከ12-17 የሚሆን ታዳጊዎች ናቸው
- ከፖርኖግራፊ መጽሔቶች አንባቢዎች 82 በመቶው የሚይዙት ወንዶች ሲሆኑ ድረ ገጾችን ከሚመለከቱት 77 በመቶውም እንዲሁ ወንዶች ናቸው፡፡

ለመሆኑ ወሲብ የሞላባቸው ፊልሞችን መመልከት፣ ራቁት ዳንስ ቤቶች መሄድ እንዲሁም መጽሔቶችና ድረ ገጾችን መጎብኘት በአጠቃላይ ፖርኖግራፊ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ዛሬ በተለያዩ ምክንያቶች በእኛም ላይ የተደቀነ ጉዳት ሆኗል፡፡ በግሎባላይዜሽን መምጣት ምክንያት በሁሉም የዓለም ክፍል ያሉ ሕትመት ውጤቶችን ለማግኘት ከመቻላችን ውጪ በኢንተርኔት አገልግሎት ምክንያት ኢትዮጵያውያንም ለዚህ ክስተት ተጋላጮች ነን፡፡

ከኢንተርኔት ቅርብነትና በየትምህርት ቤቱ ሳይቀር የሚገኝና አስፈላጊ ጉዳይ ከመሆኑ ሌላም በየቦታውና በየሰፈሩ እንደ አሸን ከፈሉት ቪዲዮ ቤቶችም ሌላው ወሲብ ፊልም በቀላሉ እንዲገኝ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሌላ ቀርቶ አዟሪዎች እዚሁ አዲስ አበባ «ያም አለን» እያሉ «በኢትዮጵያውያን የተሠራ» ሳይቀር ልቅ ወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳይ ፊልም እየሸጡ መሆኑ በጋዜጦች ሳይቀር የተፃፈ «የአደባባይ ምስጢር» ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ «ፖርኖግራፊ» የሚባለው ቃል በእንግሊዝኛው ያለው ቃል የሚያጠቃልለኑወን ትርጉም ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ፖርኖግራፊ ቀላል የሚባል በእንግሊዝኛው «soft core pornography» እንዲሁም ጠንካራ ይዘት ያለው «hard core pornography» ተብሎ ይከፈላል። የመጀመሪያው ዓይነት የወሲብ ሁኔታዎችን የሚገልጹ እና እርቃን ፎቶግራፎችን የሚያወጡ መጽሔቶችን መመልከትን የሚጨምር ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት በግልጽ ወሲባዊ ግንኙነቶች የሚታዩበት ነው። በሁለተኛው ዓይነት ፖርኖግራፊ ሰዎች እጅግ አደገኛ የወሲብ ባህርያትን እንዲያዳብሩ የሚነሳሱና ተፅዕኖ የሚፈጥሩ የአስገድዶ መድፈርና ከእንስሳት ጋር ወሲብ መፈፀም የመሳሰለው የሚታይባቸው ናቸው።

ላውሪ ሄል የተባለች አንዲት ሴት ባሏ የፖርኖግራፊና የወሲብ ፊልሞች ሱሰኛ መሆኑ በቤተሰባቸው ላይ ያስከተለውን አስከፊ ውጤት በተመለከተ ስትናገረው እንደተሰቸው ሚሲዮናውያን ከሆኑ ቤተሰቦች የተወለደው ባለቤቷ ጃክ ፖርኖግራፊ የመመልከት ሱሱ የጀመረው ኮሌጅ ተማሪ ሳለ ብዙም ጠንካራ የማይባሉ ወሲብ ነክ ጽሑፎችን የሚያወጡ መጽሔቶችን በመመልከት ነበር። ቀጥሎ ለአዋቂዎች ብቻ የሚፈቀዱ ጠንከር ያሉ የወሲብ ፊልሞችን ወደ መመልከቱ ተሸጋገረ። በዚህም አላበቃ ራቁት ወደሚደነስባቸዙወ ቤቶች መሄድ ጀመረ። ከዚያም በእነዚህ የፖርኖግራፊ ውጤቶች የሚመለከታቸውን ነገሮች በተግባር ያይ ዘንድ በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ ሴቶችን መቅጠር ተያያዘ። በእነኝህ ሁሉ ሒደቶች ውስጥ ባለቤቱንና ልጆቹም በአጠቃላይም ቤቱን እርግፍ አድርጎ ትቶና ረስቶ ነበር። በቤቱ የሚገኝበት ጊዜ ከሚነሱ ውጪ የሚያሳያቸው ፍቅርና እንክብካቤም አልነበር፣ ሁኔታው ሁሉ አካሉ እንጂ ስሜቱ ከቤተሰቡ አባላት ጋር እንዳልሆነ የሚያሳይ ነበር።

ይህ ሁሉ ለምን ሆነ ለሚለው ምክንያት ስትፈልግ ነው እንግዲህ ላውሪ ባለቤቷ የተዘፈቀበትን አደገኛ ሁኔታ ማወቅ የቻለችው። ችግሩ እስዋ ስትነቃ በሺዎች የሚቆጠሩ ዶላሮች ዕጣ ውስጥ ተዘፍቀው ነበር። ለኤች.አይ.ቪ ተጋልጣ ሊሆን እንደሚችልም ስጋት አላት። በኋላ ላይ ለባለቤቷ በፃፈችው ደብዳቤ «ፖርኖግራፊ ይህንን ሁሉ እንዲያደርግብህ ለምን ፈቀድክ? ወሲብ ፊልምና

መሰል ነገሮች ሁሉ ከልጆችህ እንዴት በለጡብህ? እኔንስ ለምን ተውከኝ? እኔ ላንተ በቂ አልነበርኩም?» የሚል መልዕክት ያለው ነበር፡፡
እንደ አሜሪካ ያለው አገርና በአጠቃላይም የሰለጠነው ዓለም ፖርኖግራፊ የተስፋፋበት እንደ ላውሪ ያሉ ታሪኮች በየቀኑ የሚደገሙበት ነው፡፡ እንደ ድሮው የአዋቂ ወሲብ ፊልሞችን ለመመልከት ወደ ፊልም ቤት ማምራትና ራቁት ዳንስ ቤቶች መሄድ ላይጠበቅባቸው ይችላል፡፡ በየሱቁ የሚገኝ ጉዳይ ከመሆኑ ሌላ ገንዘባቸውን ለማውጣት እስከፈቀዱ ድረስ ቤታቸው፣ ቢሯቸው እና ትምህርት ቤቶቻቸው ድረስ በልዩ የቴሌቪዥን ቻናሎችና በኢንተርኔት የሚመጣላቸው ሆኗል፡፡
ባለፉት ዓመታት የፖርኖግራፊ ድረገፆች ቁጥር ከ30ሺ ዛሬ ወዳለበት 300 ሺ ደርሷል፡፡ ኢንተርኔት ፖርኖግራፊን በቀላሉ የሚገኝ ነገር ከማኑደረጉ ውጪ በፊት የማይደፈር የሚመስለውን እጅግ ጠንካራ የሚባል ዓይነ ይዘት ለማንኛውም ሕዝብ ይፋ ሆኖ እንዲገኝ አስችሎታል፡፡ ዛሬ ፖርኖግራፊ በአሜሪካ ገበያ ብቻ በየዓመቱ ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ገቢ የሚያስገኝ ትልቅ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ይህም ከሌላው ፊልም ዘርፍ ቀርቶ ከማናቸውም ኢንዱስትሪ ጋር የማይወዳደር ትርፋማነት ነው፡፡
ፖርኖግራፊ ተመልካችነት አደገኛ ባህሪ ከማጎልበትና በተለይም በሴቶች ላይ አስገድዶ መድፈርና መሰል ጥቃቶችን ከመሰንዘር ጋር ያለውን ቁርኝት በተመለከተ ጥናት ያደረጉ የአሜሪካ የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ አጥንኚዎች እንዲሁም የብሪቲሽ ተመራማሪዎች ቡድን መደምደሚያ ላይ ያልደረሱበት ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም በአሜሪካ የፖርኖግራፊን ጉዳይ በሚመለከት የተቋቋመው ኮሚኝ እነኝህ ክስተቶች ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳላቸው ይገልፃል፡፡
የፖርኖግራፊ መስፋፋት በጥቅሉ በማኅበረሰብ ውስጥ ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶችን ዕውቅና በመስጠት ቤተሰብ ላይ አደጋ የሚጋርጥ መሆኑን በዚህም ሳቢያ ችላ የማይባል ጉዳይ መሆኑን ነው ባለሙያዎቹ የሚስማሙበት፡፡ ፖርኖግራፊ ስለወሲብ አደገኛ ትክክል ያልሆነ መልዕክት የሚያስተላልፍ ሲሆን ይህም መልዕክት በሴቶችና በወንዶች መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖር

የሚያደርግ ነው። ከዚህም በላይ እያንዳንዱን ሰው በወሲብ ሱስ በዚህም ሳቢያ ለወሲብ ጥቃት የሚያጋልጥ ነው።

ፖርኖግራፊ ስለወሲብ ያለውን ግንዛቤና አመለካከት በመቀየር ወሲብ የተፈጥሯዊ ፍቅር የጋብቻና ለአንድ ሰው የመሰጠት ሁኔታን በማጥፋት ወሲብን ራስ ወዳድነትና ግል ጉዳይ ብቻ እንዲሁን ያደርገዋል። በአሜሪካ በተደረገ አንድ ጥናት ለምሳሌ ከተካተቱ መላሾች ፖርኖግራፊን ለምን እንደሚመለከቱ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ «ማስተርቤት ለማድረግ/ ራሴን ለማርካት፣ የወሲብ ስሜቴን (ወይንም የሌሎችን ስሜት) ለማነሳሳት» ያሉት በርካታ ቁጥር ያላቸው ናቸው። ይህ ከራስ ስሜት መንጭቶ ፖርኖግራፊን ማለት ባልና ሚስት ወይንም ሁለት ተጓዳኞች በጋብቻ አልያም በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ከሚያደርጉት ቁርኝትና ውህደት ጋር በእጅጉ የሚፃረር ነው። በዚህና በሌላ መልኩም ፖርኖግራፊ ታማኝ አለመሆንን ብዙ ፍቅረኞች መያዝን በአጠቃላይ አመንዝራነትን ያስፋፋል።

ሌላው ፖርኖግራፊ የሚያስተላልፈው አደገኛና የተሳሳተ መልዕክት ክቡር የሆነው የሰዎች ሰውነት እንደ ዕቃ እንዲታይና የተፈጠረበት ቀዳሚ ዓላማም ሌሎች ሰዎችን ማስደሰት ነው የሚለው ነው። ሌላው ደግሞ ወንዶች ወንድነታቸው የማፈተነው በሴቶች ላይ በሚፈጽሙት ወሲባዊ ድርጊት ብቻ እንደሆነ ተደርጎ እንዲታይ ማድረጉ ነው። ወንዶች በእንዲህ ዓይነቱ የፖርኖግራፊ ሁኔታ የሚሳተፉ «ፍጹም» የሴቶችን ምስል በመያዝ የተጓዳኞቻቸው ሰውነት እንዲህ ባልሆነ እንዲሉና በትዳር አጋሮቻቸው እንዳይረኩ የማድረግ አዝማሚያም አለው። ሰዎች ከተፈጥሯዊው ሁኔታ ውጪ እንዲያስቡና «ያፈነገጡ» እንዲሆኑም የደርጋል። በሀገራችን በሕግ የተከለከለው ግብረሰዶማዊነት የመስፋፋት ሁኔታም ይህንኑ የሚያሳዩ ፊልሞች የመበራከታቸው ውጤት ሊሆን ይችላል።

በተለይ በወሲብ ግንኙነቶች ሕፃናት እንዲካተቱ ተደርጎ የሚዘጋጅ ፖርኖግራፊ በኢንተርኔት እየስፋፉ ከመጡ የፖርኖግራፊ ዓይነቶች መካከል እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ እንግዲህ የአሜሪካ ሁለም ግዛቶች በሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶችንም ይሁን ሕፃናን ተጠቅሞ እንዲህ ዓይነት

ቪዲዮ ምስሎችንና ፊልሞችን መሥራትን በሕግ የሚከለክል መሆኑ እንዳለ ሆኖ የሚፈፀም ወንጀል መሆኑ ልብ ዓይነቱን ድርጊት መፈፀም አይደለም ሕፃናት ፊት እርቃን መሆንም ሆነ ወሰብ መፈፀም ሳይቀር በሕግ የሚያስቀጣ ነው፡፡
በእርግጥ በሃገራችን በሕፃናትና ታዳጊዎች ላይ የሚፈፀሙ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች (በአብዛኛው) በፍርድ ሒደትም ይሆን በፖሊስ መጃዎች የምንሰማቸው ወንጀሎች በአብዛኛው ሕፃናትና ታዳጊዎች ላይ የሚፈፀሙ ናቸው) ከበስተጀርባቸው ያለው ጉዳይ ምንድነው? የሚለው መጠናትና መታወቅ ያለበት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በበኩሌ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ለማነሳሳት የወሲብ ፊልሞች ሚና ቀላል እንደማይሆን አስባለሁ፡፡

********************

# ማይክሮቢሳይድስ /Microbicides/ አዲስ የኤች.አይ.ቪ. መከላከያ ንጥረ ነገር ለአፍሪካ መቼ?

ማይክሮቢሳይድስ (Microbesides) የወቅቱ እጅግ ተስፋ የተጣለበት ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ሊከላከል የሚችል ንጥረ ነገር (ቅባት፣ ጄል፣ ክኒን፣ ክሬም) ነገር ነው። በፊት የምናውቃቸው መታቀብ መወሰን እና ኮንዶም ለሁሉም የሚበጁና ሁሉንም ሊያቅፉ የሚችሉ ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል የሚበጁ አማራጮች ሆነው አልተገኙም። የሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች በኤድስ ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶችና አቀንቃኞች የመገናኛ ብዙሃኑና በሴቶች ዙሪያ የሚሠሩ የተለያዙየ ድርጅቶች ሁሉ ትኩረት በማይክሮቢሣይድስ ላይ ሆኗል።

በአንድ ወቅት «ከገዳዩና ከቀሣፊው ኤድስ ተጠንቀቁ» ሌላ ጊዜ «ታቀቡ፣ ታማኝ ሁኑ፣ ኮንዶም ተጠቀሙ» ከዚያ ደግሞ «ተመርመሩ ተመርመሩ የባህሪ ለውጥ አምጡ» ቀጠለና «ለሕይወታችሁ ፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት ደረሰላችሁ» አሁን ደግሞ ማይክሮቢሣይድስ ይኸው እዚያ ማዶ ደርሷል መጣ መጣ እየተባለ ነው። ቀጥሎስ?... «ቀጥሎስ? ከሚሉን ከዚሁ ጋር ተቀራራቢ የሆነውን ክትባት በቃ ይኸው ለምን አይሉም» የሚሉ የሞያው ባለቤትና ባለቤት ያልሆኑ ሰዎች ምሬት የሰማል። /ይደብቁናል አለ ቀልደኛው/እኛም የሚሰጡንን ያሉንን አድርጉ የተባልነውን ሁሉ ብንጠራጠርም ከዚህ ሲዘል ደግሞ መጮህ ብንችልም ከማድረግ አናቋርጥም። ለማንኛውም ስለዚህ ሣይንሳዊ ግኝት ወቅቱ ሆኗልና ግራ ቀኙን እናውጋ።

ማይክሮቢሣይድስ ተመራማሪዎቹ እንደሚሉት በአንድ ድንጋይ ሁለት እና ከዚያም በላይ ወፎች ... እንደማለት ነው። ማይክሮቢሳይድስ ከግንኙነት በፊት ሴቷ ብልቷ/ውስጡን/ በመቀባት ኤች.አይ.ቪንና እርግዝናን እንድትከላከል የሚያስችላት ቅባት ነገር ነው። ከዚህም ሌላ እንደ ጨብጥና ክርክረ ያሉ የአባላዘር በሽታዎችን ሊከላከል ይችላል።

በአብይነት እንደተገለፀው ማይክሮቢሳይድስ ጄል /ዝልግል ቅባት ነክ ነገር/ የአንዳ ዓይነት ምርትና ግኝት እንጅ በተለያየ መልኩ ቢያንስ በአምስት የምርምርና የጥናት ጣቢያዎች ሙከራ እየተደረገባቸው ያሉ የተለያየ ዓይነት /form/ ማይክሮቢሣይድስ አሉ።

ከጄል (ቅባት) ውጭ ማይክሮቢሣይድስ ዓይነት /Form/ ሌላ በእንግሊዝኛ /Suppository/ የሚባል ሌላ የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት አለ፡፡ ትናንሽ ክኒን ዓይነት ነገር ሆኖ ሴቷ ብልት ውስጥ ከገባ በኋላ በራሱ ጊዜ የሰውነት ሙቀት ሲያገኝ የሚሟሟ የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት ነው፡፡

ሦስተኛው ደግሞ /Cream/ ነው ወፈር ያለ ቅባት ነክ ነገር ሆኖ ለእጅ መጥረጊያ እንደሚዘጋጁ ስስ የታሸጉ ርጥበት ያለባቸው ሶፍት ነገር ልንወስደው እንችላለን፡፡ መጠናቸው በጣም ትንሽ ሆኖ ሴቶች ከግንኙነት በፊት ብልት ውስጥ እንደማጣበቅ ዓይነት ነገር አድርገው ይተውታል ራሱ ይቀልጣል፡፡

ተመራማሪዎቹ በእነዚህና በሌላም መልክ አንዳንዶቹን ኤች.አይ.ቪን ብቻ እንዲከላከሉ ግለሎቹን ደግሞ እርግዝናን ጨምረው እንዲከላከሉ በማስቻል መልኩ ምርምራቸውን ለማጠናቀቅ እየጣሩ ነው /ጥረት የነሱ ቃል ነው/

በ16ኛው ፖለም አቀፍ የግአድስ ጉባዔ ሦስት ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል የንማረዱ መንገዶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጎ አንዴ ጥናት አንዴ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥበት ሠንብቷል /በዚያው ሰሞን/ አንዱ የወንዶች ግርዛት ሌለው የሴቶች ኮንዶም ማስተኛውና ዋነኛው ደግሞ ማይክሮቢሣይድስ ነው፡፡ በተለይ ማይክሮሲሣይድስ የሴቶችን መብትም ፍላጎትም ከማሟላቷ አንፃር ቶሎ ‹‹በጉዳዩ ለተጎዱ ይድረስልን›› የሚሉ ተመራማሪዎች ባለፀጎች የተለያዩ ድርጅት ኃላፊዎች ደፋ ቀና ሲሉ ነበር /ከልባቸው ያድርግልን…/

በዓለማችን ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ 39 ሚሊዮን ሰዎች ውስጥ 19.2 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴቶች ናቸው፡፡ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ዕድሜአቸው ከ15 እስከ 24 ከሚሆኑ ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ ወጣቶች ውስጥ 74 በመቶ ሴቶች ናቸው፡፡ በደቡብ አፍሪካ ከአራት ዕድሜአቸው እስከ 22 ካሉ ሴቶች ውስጥ አንዷ ለኤች.አይ.ቪ ትጋለጣለች፡፡ በህንድ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች 22 በመቶ የሚሆኑት ባለትዳርና በአንድ ተወስነው የሚኖሩ ሴቶች ናቸው፡፡ በደቡብ አፍሪካ ከአራት ዕድሜአቸው እስከ 22 ካሉ ሴቶች ውስጥ አንዷ ለኤች.አይ.ቪ ትጋለጣለች፡፡ በህንድ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች 22 በመቶ የሚሆኑት ባለትዳርና በአንድ ተወስነው የሚኖሩ ሴቶች ናቸው፡፡ በሀገራችን ከጠቅላላው

ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች 57 በመቶ ሴቶች ሲሆኑ፣ 128,000 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ነፍሰጡር ሴቶች ናቸው፡፡

ሴቶች ከማኅበራዊ ከባህልና ከኢኮኖሚ ከተፈጥሮ ጋር በተያያዘ ከወንዶች የበለጠ ለችግሩ የተጋለጠ ናቸው፡፡ ከባህል/ልምድ ጋር በተያያዘ በቀላሉ ግርዛትን ጠለፋን ማንሳት ይቻላል፡፡ በኢኮኖሚ በአብዛኛው የወንዶች ጥገኛ እንዲሆኑ ስለተደረገ፣ የትምህርትና የሥራ ዕድል ስለተነፈጋቸው፣ በቤታቸውም ይሁን ከዚያም አልፎ በራሳቸው እንዳይወስኑ ሆነዋል፡፡ በተፈጥሮ የሴቶች ብልት ቫይረሱን በቀላሉ እንዲወስዱ ያደርጋቸዋል፡፡ ኮንዶም ያለ ወንዶች ፍቃድ የማይታሰብባቸው ጥምረቶች በርካታ ናቸው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ለምሣሌ ለሴተኛ አዳሪዎች በገንዘብ ኃይል ይደለላሉ፡፡ ከዚህና ከሌሎች በርካታ ምክንያቶች የተነሣ ማይክሮቢሣይድስ በተለይ ሴቶችን የሚገላግል የሚታደግ መፍትሔ እንደሆነ በብዙዎች ታምኖበታል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ቢያንስ በአምስት የምርምር ጣቢያዎች ማይክሮቢሣይድስ ላይ በተጨባጭ ፈቃደኛ ሰዎችን አግኝተው ሙከራና ቀጣይ ጥናቶችን እያደረጉ ነው፡ ፡ ሙከራው የሚደረገው በዚችው በአህጉራችን አፍሪካ ነው /አፍሪካን ለሙከራ ብቻ አይምረጧት እንጅ/ ሙከራው ነፍሰጡር ያልሆኑና ለወሲብ የደረሱ ለጋ ወጣቶችን /Sexually active/ ሣይጨምር ፈቃደኛ በሆኑ ሌሎች ሰዎች ላይ ቀጥሏል፡፡

የማይክሮቢሣይድስ ጥናት ምርምርና ሙከራ የሚደረገው በደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ዩጋንዳ፣ ኬኒያ፣ ታንዛኒያ፣ ዝምባብዌ፣ ዛምቢያ፣ ማላዊና ህንድ ውስጥ ሲሆን፣ በተለይ በደቡብ አፍሪካ ሰፋ ያሉና በርከት ያሉ ምርምሮች እየተካሄዱ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ጥናቶችና ምርምሮች የገንዘብ ዕርዳታ የሚያደርጉት በአብዛኛው የአሜሪካ ድርጅቶችና ባለፀጎች ናቸው፡፡ ለምሣሌ የዓለማችን ቁጥር አንድ ባለፀጋው የቢልጌትስና ባለቤታቸው ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን በደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ዩጋንዳና ህንድ ያሉትን ጥናቶች ስፖንሰር /የገንዘብ እገዛ/ በማድረግ ጥናቱ ይካሄዳል፡፡ ሌሎችም ፖፕሌሽን ከውንስል /population council/ ዩ.ኤስ.ኤድ /USAID/ የእንግሊዝ የሕክምና ምርምር ካውንስል /Uk medical Research council/ ፋሚሊ ሄልዝ

ኢንተርናሽናል /Family Healthy International-FHI/ እንዲሁም የተለያዩ ሀገራት በጎ አድራጊ ድርጅቶች ለጥናቱ የገንዘብ ዕርዳታ ያደርጋሉ፡፡ በአብይነት ግን አሜሪካ ሰፊውን እገዛ ለማይክሮቢሣይድስ ጥናት እያደገች ሲሆን፣ ቀሪውን ቢልጌትስ፣ ካናዳ፣ እንግሊዝ፣ የአውሮፓ ኅብረት አየርላንድ ኔዘርላንድስና ሌሎች ሀገራትም ተሳትፈውበታል፡፡

እያንዳንዱ ጥናት እየተደረገበት ያለ ማዕከል ደግሞ አንድና ከዚያ በላይ የማይክሮቢሳይድስ ዓይነቶችን ጥቅም ላይ ያውላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በሐሳብ ደረጃ /ideally/ ወይም ማይክሮቢሣይድስ እንዲሆን የሚፈለገው የጎን ጠንቅ የሌለው ወይም በእጅጉ አነስተኛ፣ በመካከል ደረጃው አስተማማኝ፣ ዋጋው እርካሽና በዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ በቀላሉ ሊገዛ የሚችል፣ አጠቃቀሙ በጣም ቀላል የሆነ ምርትን ማውጣት ነው /ኮንዶምን ገለል በይ የሚል ይመስላል/ ኮንዶምን የሚተካ የተሻለና የማይታይ /invisible condom/ ለአጠቃቀም የማይረብሽ መከላቀያ ነው ማይክሮቢሣይድስ፡፡

ይህ እያወራንበት ያለነው ሴቷ ከግንኙነት በፊት ቅባቱን /ጄሉን/ ብልቷን በመቀባት ኤች.አይ.ቪ ኤድስንና እርግዝናን እንዲሁም አንዳንድ የአባላዘር በሽታዎችን መከላከል የማያስችል የምርምር ውጤት ማይክሮበሣይድስ በስድስቱ በተለይ በአምስቱ የምርምር ጣቢያዎች መቼ ጥናቱ ተጠናቆ ይወጣል? መቼስ የአፍሪካ ሴቶች ሕይወትን ለመታደግ ይደርሳል? ማይክሮቢሣይድስ በምን መንገድ ነው ቫይረሱን የሚከላከለው? በምን ያህል ደረጃ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ ይከላከላል የሚሉ ጥያቄዎች መነሣታቸው አይቀርም፡፡

በቶሮንቶ ካናዳ 16ኛው ዓለም አቀፍ የኤድስ ጉባኤ ዶ/ር ጊታ ራምጂ /Gita Ramjee/ የተባሉ ከደቡብ አፍሪካ የማይክሮቢሣይድስ ምርምር ጣቢያ የተገኙ እመቤት አንድ ሰፊ ጥናትና የተለያዩ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ሰጥተዋል፡፡ የሳቸውንና የሌሎችን የጥናት ምላሽ ሳምንት እንደገና እናወጋበታለን፡፡

# **ማይክሮቢሳይድ** /Microbidcides/
# **አዲሱ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያ ንጥረ ነገር ለአፍሪካ መቼ?**

ክፍል ፪

...በተለያየ መልክ /form/ ለማቅረብ እየታሰበና ጥናቱ እየተገባደደ ሥላለው ኤች.አይ.ቪንና አንዳንድ የአባላዘር በሽታዎችን እንዲሁም እርግዝናን ስለሚከላከለው ማይክሮቢሣይድስ ዛሬ ልንመልሳቸው ቀጠሮ አስረን የተውናቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ለአፍሪካ መቼ ሊደርስ ይችላል? መድሃኒቱ ቫይረሱን በምን መንገድና ምን የሀል ደረጃ ይከላከላል? የሚሉና ሌሎችንም ጥያቄዎች አንስተን እንቀጥል፡፡

ማይክሮቢሣይድስን በአብዛኛው ለማቅረብ እየተኮረ ያለው በጄፀል (በዝልግል ቅባት) መልክ ነው፡፡ ቅባቱን ከወሲባዊ ግንኙነት በፊት ሴቷ ብልቷን /ውስጡን/ ትቀባዋለች፡፡ ኤች.አይ.ቪን እንዲሁም ሌሎች የአባላከር በሽታዎችን ይከላከልላታል፡፡ አንዳንድ የጥናት ጣቢያዎች ደግሞ እርግዝናን እንዳይከላከል አድርገው ለማቅረብ እንደሚሞክሩ በየመግለጫዎቻቸውና ጥናቶቻቸው ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ማይክሮቢሣይድስን በክሬም /cream/ በፊልም /film/ በሳፖዚተሪ /suppository/ እንዲሁም በሌሎች መልክ ለማቅረብ ተመራማሪዎቹ እየሞከሩ ነው፡፡ ክሮም ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ጄለ ትንሽ ተመሳሳይ ሆኖ ወፈር ያለ ቅባት ነክ ነገር ነው፡፡ ይህ ክሬም ሴቷ ብልት ውስጥ ካስገባችው በኋላ በራሱ ጊዜ የሚቀልጥ ነው፡፡ ፊልም /film/ ደግሞ ስስ ርጥበት ያለበት የእጅ መጥረጊያ ሶፍት ዓይነት ነገር ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በቀላሉ በሰውነት ሙቀት የማቀልጥ ነው፡፡ በመጨረሻ የተጠቀሰው ሳፖዚተሪ /suppository/ ደግሞ ክኒን ወይም እንክብል ሆኖ ከግንኙነት በፊት ብልት ውስጥ ከመቀመጡ መሟሟት የሚጀምር የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት ነው፡፡

ማይክሮቢሣይድስን በተለያየ መልክ ማቅረብ ያስፈለገው ሴቶች ከሚኖሩበት አካባቢና ከአኗኗራቸው አንፃር የተለያየ የሰውነት መዋቅር ስላላቸው የሚስማማቸውን መርጠው እንዲጠቀሙ ነው፡፡ ይህ ከሌሎች የእርግዝና መከላከያዎች ጋር ተመሳሳይ አቀራረብ ነው፡፡ በርካታ የሚባሉ የወሊድ

መከላከያ ዓይነቶችን እናውቃለን፡፡ በርካታ የሆኑበት ምክንያት ለአንዷ የሚስማማ ለሌላዋ ያለመስማማት አጋጣሚ ስለሚበረክት ነው፡፡

ማይክሮቢሣይድ በተለይ ወሲባዊ ግንኙነት ላይ የመደራደር /አልፈልግም፣ አላደርግም፣ ዝግጁ አፀይደለሁም ወይም ኮንዶም እንጠቀም ወዘተ የማለት/ አቅምም፣ መብትም፣ ልምድም፣ ባህልም ለሌላቸው የአፍሪካ ሴቶች ሁነኛ አማራጭ፣ ክሱን ያልሆነ ኮንዶም /invisible condom/ እንደሆነ ይታመናል፡፡

አንዳንዴ ይባስ ተብሎ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ እንዳለበት የሚጠራጠር ወይም የሚያቅ ለንድ ሚስቱም ጋር ይሁን ሌላ ሰው ጋር የሚተኛበት፣ ወሲብ የሚፈጽምበት አጋጣሚ አለ፡፡ ያኔ ሚስት ብትጠራጠርም ወይም በቃ ራሷን መጠበቅ ብትፈልግም መከላከያ አማራጭ አይኖራትም፡፡ ማይክሮቢሣይድስ ታዲያ ገላግሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ግንኙነት ካሰበችበት ሰዓት በፊት ቀድማ ጄሉን ወይም ቅባቱን ብልቷን /ውስጡራ/ ትቀባለች የፈራችውን ሁሉ ትከላከልበታለች፡፡

ማይክሮቢሣይድስ ኤች.አይ.ቪን በየትኛውም ደረጃ ቫይረሱ ወደ ሴቷ ብልት ከገባበት ቅፅበት ጀምሮ እስከየትኛውም ደረጃና ጥግ ድረስ በማሳደድ ይከላከለዋል ወይም ያጠቃዋል፡፡ ለምሳሌ MIV-150 እና ካራጋርድ /caraguard/ የተሰኙት የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት በሦስተ መንገድ ቫይረሱን ይከላከላሉ፡፡ ካራጋርድ ቫይረሱ ወደ ህዋስ እንዳይገባ ሲከላከል ኤም.አይ.ቪ 150 ደግሞ /MIV-150/ ከህዋስ /cell/ ውጭ ያገኘውን ቫይረስ አቅሙን ይሰልበዋል፡፡

በአጋጣሚ እንኳን ወደ ህዋስ የመጠጋት ወይም የመግባት ዕድል ቢኖርም ቫይረሱ እንዳይራባና ባለበት ደረጃ ፀንቶ እንኳን እንዳይቆም ያሽመደምደዋል፡፡ የሌሎቹም ማይክሮቢሣይድስ ዓይነቶችም ሥራቸው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው፡፡ C31G አሸርሴል /Ushercell/ በሚል የተሰየመው የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት ደግሞ ሥራው የቫይረሱን የላይኛውን ሽፋን /outer covering/ በመገንጠል ክንፍ የሌለው አሞራ ያስመስለዋል፣ ወዲያውም ቫይረሱ ቫይረስ መሆኑ ይቀራል፡፡

ሌላኛው ዓይነት የማይክሮቢሣይድስ ዓይነት ደግሞ በብልት አካባቢ የሚገኙ ህዋሣትን በተፈጥሮ ያላቸውን /raising PH level/ አቅም ከፍ ያደርጋል፡፡

ቫይረሱ መጠጊያየ ብሎ ወደሚተማመንበት ህዋስ እንዳይገባ አካባቢው ላይ ነውጥ በመፍጠር፣ ምቾት በመንሣት መመለሻ በሌለው መንገድ ቀብሩ እዛው እንዲሆን ያደርጋል። የእንግሊዝኛ ሣይንሳዊ ትንታኔውን ወደ አማርኛ ማምጣትና ማስረዳት አቅሜ አነሰ እንጅ አጠቃላይ የማይክሬቢሣይድስ ኤች.አይ.ቪን የመከላከል ሥርዓት /mechanism/ ይኸው ነው።

ይህ አዲስ መከላከያ ለታዳጊ ሀገራት መቼ ይደርሣል? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ አላስቀምጥ። በመጀመሪያ በማይክሮቢሣይድስ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ከደርዘራ በላይ ድርጅቶች አሉ። ቶሎ ይደርሣሉ የሚባሉት ግን አምስት ናቸው።

- በዩ.ኤስ.ኤድና በጌትስ ፋውንዴሽን ስፖንሰር የተደረገው አንዱ የጥናት ቡድን ውጤቱ Dec.2009 ሌላኛው ደግሞ Dec 2007 ይደርሳል ተብሏል።
- በዩ.ኤስ.ኤድ ብቻ የሚታገዘው የጥናት ቡድን ደግሞ አንዱ may 2007 ሁለተኛው Sep 2009
- በዲኤፍ አይዲ /DFID/ የገንዘብ ዕርዳታ የሚደረግለት የጥናት ቡድን ውጤት Dec 2009
- ኤን.አይ.ኤች /NIH/ የተሰኘ ድርጅት ስፖንሰር ያደገው የጥናት ቡድን ደግሞ Apr 2009 አደርሳለሁ ይላል (ሁሉም እ.ኤ.አ. ነው)

እነዚህ የጥናት ማዕከሎች በአሁኑ ሰዓት መድሃኒቶቻቸውን (ማይክሮቢሣይድስን) ፈቃደኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ሙከራ እያካሄዱ ናቸው። በተለይ እጅግ ያስፈልጋቸዋል ለሚባሉት ለታዳጊ ሀገራት ሕዝቦች ደግሞ ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት ባለው ግዜ በየመንደራቸው ጥግ ይደርሣቸዋል ተብሎ ይገመታል። ይህን መረጃ ያቀረቡት የአንዱ ታላቅ የጥናት ማዕከል ቡድን አባል ዶ/ር ጅታ ራምጅ /Dr. Gita Ramjee-from HIV prevention research unit Durban-South Africa/ ናቸው።

ማይክሮቢሣይድስ ቫይረሱን የመከላከል አቅሙ ከ40 – 60 በመቶ ድረስ ነው። ይህ በቁሙ ሲታይ ምናልባት አጥጋቢ የሚባል ላይሆን ይችላል። ሆኖም ከ100 ሰዎች ውስጥ 60 ሰዎችን ማትረፍ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች ሕይወት የሚታደግና ቀላል የማይባል ገንዘብ የሚያተርፍ ነው።

«የማይክሮቢሣይድስ አገልግሎት ላይ መዋል» አሉ አውሮፓ ኅብረት ውስጥ የሚሠሩ አንድ ባለሞያ /Human and social Development for European commission's director general of development Dr. Lieve Fransen/ ደ/ር ሌቭ ፍራንሰን «በታዳጊ ሀገራት ብቻ በዓመት ቢያንስ የሁለት ሚሊዮን ሰዎችን ሕይወት የሚታደግና ለጤና እንክብካቤ የሚወጣ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማትረፍ የሚያስችል መከላከያ ነው»

ጽሑፌን የሚጠናቅቀው ባለፀጋው አሜሪካዊ ቢልጌትስና ሌሎች ታላላቅ ሰዎች ስለ ማይክሮቢሣይድስ የተናገሩትን እንዳለ በማስቀመጥ ነው።

*«በፍጥነት የማይፈፀመውን ሁሉ የመፈፀም አንዳች ተአምራዊ ጥበብ ቢኖረኝ የመጀመሪያው ሥራዬ ማይክሮቢሣይድስን ዛሬውኑ ለሕዝበ ማድረስ ነበር»*

ቢልጌትስ አሜሪካዊ ቁጥር አንድ ቱጃር

*«የኤድስን ግብአተ መሬት ለማየት በክትባት በማይክሮቢሣይድስና በሌሎች የመከላከያ መንገዶች ላይ ጥናቶችን ጠንክረን መቀጠል አለብን»*

ቢል ክሊንተን የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት

*«የፆታ እኩልነት አለመኖር የቫይረሱን ሥርጭት አባብሷል። ሥርጭቱን ለመቀነስ ማይክሮቢሳይድስ ትርጉም ያለው አማራጭ ሆኖ ምናልባት በቅርብ የምናገኘው መፍትሔ ሊሆን ይችላል»*

ስቴፈን ሉውስ የተ.መ.ድ የአፍሪካ
የኤድስ ጉዳይ ልዩ መልዕክተኛ

*«የአፍሪካ ሴቶች በከፋ ሁኔታ ለኤች.አይ.ቪ የተጋለጡ ናቸው። አሁን የአደጋውን ገፅታ ለመለወጥ የሚያስችል ጥሩ አማራጭ ወደ እጃቸው ውስጥ ሊገባ ነው»*

ግራሻ ማቼል በሞዛምቢክ ኤፍ.ሲ.ዲ
የተሰኘ ድርጅት ፕሬዚዳንት

# መድረሻችን የት ይሆን?

ይህ አሁን የምናወጋችሁ ታሪክ የአንዲት ኢትዮጵያዊት እናት ታሪክ ነው። ታሪኳን ለአደባባይ ይፋ ብታወጣም ስሟ እንዲገለጽ አትፈልግምና እኛም ፍላጐቷን አክብረናል። በርዕሰ መዲናችን በአዲስ አበባ የተክለሃይማኖት አካባቢ ነዋሪ ናት። ዛሬ ሕይወቷ በተወሰነ መልኩ እየተስተካከለላት እንደሚገኝ ብታወሳንም በኤች.አይ.ቪ ሳቢያ ኑሮዋ ወዳልፈለገችው አቅጣጫ ተቀይሯል። በዚህም በእጅጉ ታዝናለች። ኤች.አይ.ቪ በደሟ ውስጥ እንዳለ ካወቀች ከረምረም ብላለች። የአራት ልጆች እናት ናት። እናቲቱ ከራሷ ባሻገር በወሊድ ወቅት ቫይረሱን ወደ ልጇ አሻግራለች። በዚሁ ሳቢያም የስምንት ዓመት ሴት ልጇ በደሟ ውስጥ ቫይረሱ ተገኝቷል። ግን ገና አላወቀችውም። ቫይረሱ በዚህ ጨቅላ ሕፃን ደም ውስጥ ሊኖርም ላይኖም ይችላል። «ይሄን እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው» ትላለች እናቲቱ። ከአራቱ ልጆቿ ሁለቱ ግን ከቫይረሱ ነፃ መሆናቸውን በምርመራ አረጋግጠዋል። ይህቺ ሴት ባለቤቷም ከቫይረሱ ጋር ነው የሚኖረው።

*****

እናቲቱ ቫይረሱ በእሷ ደም ውስጥ ከመገኘቱ ይልቅ ሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት በተለይም ልጆቿ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ መሆናቸውን ማሰብ በእጅጉ ያሳዝናታል። የዚህችን እናትና የቤተሰቧን ሕይወት ለዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን እንደመነሻ ተጠቅመንበት እንጂ አሁን በዚህ ዘመን በተመሳሳይ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩና ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው በርካታ የቤተሰብ አባላትን ማግኘት ከባድ አይሆንም። ምናልባት ቀጣዮቹ የቁጥር መረጃዎች የዘመኑን እውነታ በግልጽ ያሳያሉ ብዬ አምናለሁ።

*****

ከዓለማችን ሕዝብ ውስጥ 40 ሚሊዮን የሚጠጉት ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ጋር አብረው ይኖራሉ። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ታድያ ከ2 ሚሊዮን በላይ የሚገመቱት ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው። እኒህ ሕፃናት ቫይረሱን ያገኙት ጥንቃቄ የጎደለው ወሲባዊ ግንኙነት በመፈፀማቸው ነው? በፍፁም! አብዛኛዎቹ በርካቶቹ ቫይረሱን ከወላጆቻቸው ነው የወረሱት።

በUNAIDS የ2006 ግምታዊ መረጃ በዓለማችን ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ 40 ሚሊዮን ገደማ ሰዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወይም ከ24 ሚሊዮን በላይ የማገመቱት የሚኖሩት ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሃገራት ነው። ሃገራችን ኢትዮጵያ ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችን ይዛ ከእነዚህ ምድብ ውስጥ ተካትታለች።

*****

የኤች.አይ.ቪ ሥርጭትን ለመግታት በኤድስ ሳቢያ የሚከሰት ሞትን ለመቀነስ ሁሉም በየፊናው ትግሉን ቀጥሏል። ግና ዛሬም ቢሆን በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ በየደቂቃው በየሰኮንዱ በርካቶች በቫይረሱ ይያዛሉ። ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት በ2006 ብቻ በዓለማችን ከ4 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በቫይረሱ ተይዘዋል።

*****

የኤች.አይ.ቪ ሥርጭትን በመግታት ረገድ ሁሉም ሃገር፣ ሁሉም ሕዝብ የየራሱን እቅድ ይነድፋል፣ በዕቅዱም መሠረት ይሠራል። ግና ከመሥራት አቅማችንም በላይ የቫይረሱ አቅም የሚበረታ ይመስላል። በኤድስ ሳቢያ የሚከሰት ሞትን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። ግና ዛሬም በርካታ ሚሊዮኖች በኤድስ ሕይወታቸውን ያጣሉ። ባለፈው የፈረንጆች ዓመት በ2006 ብቻ ይህች ዓለማችን በኤድስ ሳቢያ 3 ማሊዮን ገደማ የሚጠጉ ዜጎቿን በሞት ተነጥቃለች። ከእነዚህ ሰዎች መካከል 380 ሺሕ የሚሆኑ ሕፃናት ናቸው፣ ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት።

*****

ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት በ2006 ብቻ 3 ሚሊዮን የማጠጉ የዓለማችን ሰዎች በኤድስ ሳቢያ ሕይወታቸውን አጥተዋል ብለናል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ አብላጫውን ድርሻ የሚወስዱት አፍሪካውያን ናቸው። በ2006 በኤድስ ሕይወታቸውን ካጡ የዓለማችን ዜጎች ውስጥ ከ2 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት አፍሪካውያን ናቸው። እናም ከዚህ ቁጥር ውስጥ ሃገራችን ኢትዮጵያ ቀላል የማይባለውን ድርሻ ትወስዳለች። በ2006 በኤድስ ሕይወታቸውን ያጡት ኢትዮጵያውያን 89 ሺሕ ገደማ ይገመታሉ። ይህን ቁጥር ወደ ቀን ብንመነዝረው ባለፈው ዓመት በሃገራችን ኢትዮጵያ ከ240 በላይ ሰው በቀን ሕይወቱን ያጣ ነበር ማለት ይቻላል።

*****

በሃገራችን ኢትዮጵያ ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት በ2006 89 ሺሕ ገደማ ሰው በኤድስ ለሕልፈተ ሕይወት ተዳርጓል ስንል ከዚህ ዙቀጥር ውስጥ ጨቅላ ሕፃናትም ድርሻ እንዳላቸው ማሰብ ሃዘንን የሚያጭር ነው። ባለፈው ዓመት በኤድስ ሕይወታቸውን ካጡት 89 ሺሕ ገደማ ኢትዮጵያውያን ውስጥ ከ10 ሺሕ በላይ የሚሆኑት ሕፃናት ናቸው። ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በታች የሆነ ከ10 ሺሕ በላይ ሕፃናት ቦርቀው ያልጠገቡበትን ምድር በኤድስ ሳቢያ ተሰናብተዋል።

*****

እኒህን ከላይ የገለጽናቸውን የቁጥር መረጃዎች ያለምክንያት አላቀረብናቸውም፡ ፡ የዓለማችን፣ የአህጉራችን የአፍሪካ ብሎም የሃገራችን ኢትዮጵያ ቁጥር አንድ የጤና ችግር መሆኑን ለማሳየት ነ። የቁጥር መረጃዎችን ማስነበባችን። እንዲህ ያሉ ትክክለኛ መረጃዎችን ከመስማታችን ቀድመን አለዚያም የቅርብ ሰዎቻችንን፣ ወዳጆቻችንን በኤድስ ከመነጠቃችን ቀድመን ስለችግሩ ስፋት በጥልቀት አናስብ ይሆናል። ግን ኤድስ በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ በየደቂቃና ሰኮንዱ የበርካታ ሚሊዮኖችን ሕይወት እየነጠቀ ይገኛልና ቆም ብለን ልናስብ፣ ችግሮቻችንን ልንመረምር ራሳችንን ልናውቅ፣ ልንጠነቀቅ ግድ ይለናል። አንድ አባባል አለ፣ ሱሪ ሰጥቶ አትቀመጥበት ማለት አይቻልም። እንዲያ እንዳይባል ሁሉ የወሲብ አካላት ለተሰጡት የሰው ልጅ ወሲብ አትፈጽም ብሎ መከራከር ከተፈጥሮ ሕግ ጋር እንደመጣላት ይቆጠራል የሚሉ ወገኖች አሉ። እኛም ታድያ ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽሞ አታድርጉ ብለን ልንሟገት አልተነሳንም። ግና አማራጮችን እንድንመረምር ልናበረታታ እንሞክር እንደሆነ እንጂ።

*****

እንዲያው በደፈናው ኤች.አይ.ቪ መጥቷልና ወሲባዊ ግንኙነት አታድርጉ ብሎ መደምደም ባለመቻሉ ነው ሌሎች የመከላከያ አማራጮች መምጣታቸው። ሁሉም ሰው የተለያየ ዓይነት የወሲባዊ ግንኙነት ልምድና ሕይወት አለው። ወሲባዊ ግንኙነት በጭራሽ ያልጀመሩ የመኖራቸውን ያህል ወሲባዊ ሕይወትን የሚኖሩትም የዛኑ ያህል በርካታ ናቸው። ገና በፍቅረኝነት ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ የመኖራቸውን ያህል ተዋደው የተጋቡ፣ ተጋብተው በትዳር ሕይወት ውሰጥ የሚኖሩም የትየለሌ ናቸው። እናም ታዲያ ለኒህ ሁሉ አንድ ዓይነት

ምክር አይመከር ይሆናል። ለዚህም ነው የ‹‹መ›› ሕጎች በሚል ርዕስ የተለያዩ ኤች.አይ.ቪን የመከላከያ መንገዶች መጠቀሳቸው። መታቀብ፣ መወሰን፣ ኮንዶም መጠቀም። ቸር እንሰንብት።

# የጡት ካንሰር የዘነጋነው ችግር

አኒ ማክላፍሊን ትባላለች፣ ስኮትላንዳዊት ናት። የጡት ካንሰር እንዳለባት ካወቀች ዓመታት ተቆጥረዋል። አኒ በሽታው እንዳለባት ስታውቅ በከባድ ድንጋጤ ውስጥ ተውጣ ነበር። በዚሁ ሳቢያ ስታዝን እያዘነችም ስታነባ ለረዥም ጊዜ ቆይታለች። ሕይወቷ ያበቃ፣ ያከተመ ያህል እየተሰማት በእጅጉ አንብታለች። የኋላ ኋላ ግን መረጋጋት ጀመረች። መረጋጋት ብቻም አይደለም። ካንሰር ያለባቸውን ሌሎች ሰዎች ማፅናናትም ጀምራለች።

ከዓመታት በፊት ነው። የጭንቅላት እጢ ላለበት ሰው እንዲህ አለች። «ምሕረቱን ታገኝ ዘንድ እመኝልሃለሁ። እኔ የጡት ካንሰር እንዳለብኝ ካወቅኩኝ በኋላ የተለያዩ ቀዶ ሕክምናዎችን አድርጌያለሁ። ካንሰር እንዳለብህ ማወቅና፣ አውቀህም መረጋጋት መቻል ቀላል ነገር አይደለም። የነገ ሕይወትህ፣ ተስፋህ ብን ብሎ የጠፋ ያህል ነው የሚሰማህ። አንድ ነገር ልምከርህ። እያንዳንዷን ቀን እንደ አመጣጧ ተቀበል። ቀኖችህ አንድም ጥሩ አንድም መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ። ግን ነገሮችን በቀናነት ተመልከታቸው። እንዲህ የሚባል ነገር አለ። «ጐዶሎ ብርጭቆ ብታይ ይህ ብርጭቆ ግማሽ ድረስ ጐዶሎ ነው ከማለት ይልቅ ግማሽ ድረስ ሞልቷል ብለህ ተቀበል። እናም ከእያንዳንዷ ቀን ውስጥ መልካምና ጣፋጭ ነገርን ፈልግ። መልካሙ ሁሉ ይግጠምህ። አኒ ማክላፍሊን ከጡት ካንሰር ጋር የምኖር እህትህ።›› 

***

ስለጡት ካንሰር ስናወጋ «ለመሆኑ በሽታው ከምን ይመጣል?›› ብለን መጠየቃችን ተገቢ ነው። ምላሹ ግን አንድና አንድ ብቻ አይሆንም። ለጡት ካንሰር በአጠቃላይም ለማንኛውም ዓይነት የካንሰር ችግር መነሻ ምክንያቶቹ የተለያዩ እንጂ አንድ ዓይነት ብቻ አይሆኑም፡ ለምሳሌ ለሳንባ ወይም ለአፍ ውስጥ ካንሰር ሲጋራ እንደ አንድ ምክንያትነት ሊጠቀስ ቢችልም የሳንባ ካንሰር ሲጋራ ከማጨስ ብቻ ይመላጥ ማለት አይደለም። ከፍተኛ የፀሐይ ብርሃን ተፅዕኖ ለቆዳ ካንሰር ያጋልጣል ስንልም የኖቀዳ ካንሰር መንስአው ከፍተኛ የፀሐይ ብርሃን ብቻ ነው ማለትም አይደለም። የጡት ካንሰርም መንስአ ተመሳሳይ ባህርይ ነው ያለው። ለጡት ካንሰር መከሰት ምክንያት የሚሆኑ

በርካታ ነገሮች ይኖራሉ። አንዳንዶቹን ልንከላከላቸው ወይም ልንተዋቸው፣ ልንርቃቸው፣ ልንሸሻቸው የማንችላቸው ናቸው። ለምሳሌ የወር አበባን ከ12ኛ ዓመት ዕድሜያቸው በፊት ማየት የጀመሩ ታዳጊዎች የኋላ ኋላ ለጡት ካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው። በአንፃሩም የወር አበባ ማየታቸውን በጣም ዘግይተው ያቆሙ ወይም በጣም ዘግይተው፣ ከ55ኛ ዓመት ዕድሜያቸው በኋላ የወር አበባቸው የቆመላቸው ሴቶች ለጡት ካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው። ይህ ሲባል ግን ገና በአፍላ የልጅነት ዕድሜያቸው፣ ከ12ሃ ዓመት ዕድሜያቸው በፊት የወር አበባ የተከሰተባቸው ወይም ከ55ኛ ዓመት ድማያቸው በኋላ ዘግይቶ የወር አበባቸው የቆመላቸው ሴቶች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ለካንሰት ይጋለጣሉ ብሎ መደምደም ይቻላል ማለት አይደለም። ለካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው ተባለ እንጂ።
ለጡት ካንሰር የሚያጋልጡ ሌሎች ጉዳዮችን መጥቀስ ይቻላል። እዚህ ጋር የዘር ጉዳይ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል። አንዳንዴ የጡት ካንሰር በሥጋ ዘመዶች ወይም በቤተሰቦች መካከል ሊተላለፍ ይችላል። ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዱ ወይም አንዷ የጡት ካንሰር ያለባት/ያለበት ወይም የነበረበት/ የነበረባት ቢሆን ከቤተሰቡ አባላት ሌላው/ሌላዋ በካንሰር የመጠቃት አጋጣሚው/ዋ ሰፊ ነው፡ ዝምድናው የቅርብ ሲሆን፣ እናት፣ እህት ወይም ሴት ልጅ በካንሰር ተጠቅታ ነበር ማለት ሌላዋ የቤተሰቡ አባል በጡት ካንሰር የመያዝ አጋጣሚዋ በሁለት እጥፍ ይጨምራል ማለት ነው።
ሌላም ጉዳይ ለጡት ካንሰር መንስአነት ሊጠቀስ ይችላል። የX-Ray (የራጅ) ምርመራ። በልጅነት ወይም በወጣትነት ዕድሜያቸው ለአንድ በሽታ ደረታቸውን ራጅ የተነሱ (የራጅ ምርመራ ያደረጉ) ሲቶች በኋለኛው ዕድሜያቸው ለጡት ካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው። በነገራችን ላይ እነዚህ ልንከላከላቸው የማንችላቸው ዓይነት የጡት ካንሰር መንስኤዎች ናቸው፡
፡

***

ሌሎች የጡት ካንሰር መንስኤዎች አሉ። እነዚህኞቹን ግን ልንከላከላቸው እንችላለን ነው የሚሉት ባለሙያዎቹ። ከወሊድ ጋር በተያያዘው መንስአ እንጀምር። በሕይወታቸው ጭራሽ ልጅ ያልወለዱ ሴቶች ወይም በጣም

ዘግይተው ከ30ኛ ዓመት ዕድሜያቸው በኋላ የወለዱ ሴቶች ለጡት ካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው፡፡ ከ3 ሳምንታት በፊት የወጣ አዲስ ጥናት ይህንን ሒሳብ ደግፎታል፡፡ የሚያጠቡ ሴቶች ለጡት ካንሰር የመጎለጥ አጋጣሚያቸው ትንሽ ነው፡፡
ሌላም የጡት ካንሰር መንስኤን ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህንንም ልንከላከለው እንችላለን፡፡ በአፍ የሚወሰዱ የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶች ለጡት ካንሰር የማጋለጥ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው ይላሉ ባለሙያዎቹ፡፡ ይህ ሲባል ግን በአፍ የሚወሰዱ ሁሉም የእርግዝና መከላከያ ኪኒኖች ለካንሰር ያጋልጣሉ ማለት አይደለም፡፡ ባለሙያዎችም በእርግጥ የትኞቹ የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶች ለጡት ካንሰር ያጋልጣሉ ለሚለው ቁርጥ ያለ ምላሽ አልሰጡም፡፡ ነገር ግን እንደ ሴቶቹ ተፈጥሯዊ ባህርይ አንዳንድ በአፍ የሚወሰዱ ወይም የሚዋጡ የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶች ለጡት ካንሰር የማጋለጥ ዕድልን ይፈጥራሉ ነው ያሉት ባለሙያዎቹ፡፡

****

ዶ/ር ዋልተር ዊሌት ይባላሉ በሐርቫርድ የሕዝብ ጤና ትምህርት ቤት የሥነ ምግብ ምርምር ባለሙያ ናቸው፡፡ «ካንሰር ድንገት በአንድ ለሊት የሚመጣ ሕመም አይደለም፡፡ አኗኗራችን፣ አመጋገባችን የሚፈጥረው የረዥም ጊዜ ውጤት ነው» ይላሉ፡፡ የምንመገባቸው ምግቦች የሰውነት አቋማችንን ከማስተካከልና ከማሳደጋቸው ባሻገር፣ ጤንነታችንንም ከመቆጣጠር በተጨማሪ ለአንዳንድ ላልተፈለጉ የጎንዮሽ የጤና ጠንቆች የመዳረግ አጋጣሚያችንን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ከእነዚህም የጤና ችግሮች መካከል አንዱም ካንሰር ሊሆን ይችላል፡፡
የጥናት ውጤቱን ይፋ ያደጉት ወይም ጥናቱን በጥመረት ያካሄዱት ዓለም አቀፍ የካንሰር ጥናት ፈንድና የአሜሪካን የካንሰር ጥናት ተቋም ናቸው፡፡ እንደ ድርጅቶቹ ባለሙያዎች ገለፃ ከሆነ በእርግጥም የምግብ ምርጫዎቻችን ካንሰርን በሰውነታችን ውስጥ ለማዳበር ታላቅ ተፅዕኖን ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ የዓለም ጤና ድርጅትን ጨምሮ የተለያዩ የጤና ተቋማት ባለሙያዎች እንደሚመክሩት ፍራፍሬዎችን፣ የአትክልት ምግቦችንና ጥራጥሬዎችን

አዘውትሮ መመገብና ስብ ነክ ምግቦችን፣ ስጋና የወተት ምርቶችን መቀነስ ካንሰርን ጨምሮ የልብ ሕመምንና የስኳር በሽታን ይከላከላል።
ይህ በቢቢሲ ድረ-ገፅ ከ3 ሳምንታት በፊት ይፋ የገሀነው ይህ ጥናት አንድ አስገራሚ ጉዳይንም አውስቶ ነበር። ከቁመታቸው ረዘም ዘለግ ያሉ ሰዎች፣ በካንሰር ሕመም የመጠቃት አጋጣሜያቸው ከፍ ያለ ነው። አጫጭር ሰዎች ግን ለካንሰር የመጋለጥ አጋጣሚያቸው ጠባብ ነው። እንዴት የሚለውን ጥያቄ ግን ጥናቱ በዝርዝር መልስ አልሰጠበትም።
በነገራችን ላይ የሀገራችን የሕክምና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እንደሚገልጹት ለጡት ካንሰር ሕክምና ከሚመጡ ኢትዮጵያውያነ መካከል ሰባ አምስት ከመቶዎቹ ሕመማቸው ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ነው ወደ ሐኪም ዘንድ የሚደርሱት። ስለዚህም በጡታችን ላይ የተለያዩ ሕመሞች ሲሰሙን ወደ ሕክምና ባለሙያ መሄድ ችግሩ ሳይስፋፋ ተገቢውን ሕክምና ለማግኘት ያስችለናል ይላሉ ባለሙያዎች። ቸር እንሰንብት።

**********************

# «ባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው ብቻ የአእምሮ ጤንነታቸው ይጨምራል»

ፍቅር እውር ነው። ትዳር ግን ለፍቅር ብርሃንን ይለግሳል።

*ጆርጅ ሊችንበርግ*

ፍቅር ጊዜያዊ ሕመም ነው - በትዳር የሚታከም።

*አምብሮስ ቢርስ*

****

የተለያዩ ፀሐፍት፣ የተለያዩ ፈላስፎች ስለትዳር የተለያዩ ነገሮችን ብለዋል። ሁላችንም ስለትዳር ብንጠየቅ የምንለው አናጣ ይሆናል። ዛሬ እኔ በዚህ መጣጥፌ ስለትዳር የግል አቋማን ልነግራችሁ አልተነሳሁም። ይልቁንም በትዳር ዙሪያ የተሠሩ የጥናት ሥራዎችን ላስነብባችሁ እንጂ። እኔ ይህን መጣጥፍ ለመፃፍ ስነሳሳ ያነበብኳቸው የባህር ማዶ ጥናቶች ስለትዳርና ስለባለትዳሮች የተለያዩ አስገራሚ ውጤቶችን ይዘው አግኝቼያቸዋለሁ። እናም ከአግራሞቴ ትካፈሉ ዘንድ እነሆ ተርጉሜ አቅርቤያቸዋለሁ።

አዲስ ጥናት ከአውስትራሊያ እንደሚጠቁመው ባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው ብቻ የአእምሮ ጤንነታቸው ይጨምራል። ይህ የጥናት ውጤት እ.ኤ.አ 1972 ዓ.ም.፣ ከተደረገ ጥናት ጋር ፈጽሞ የሚቃረን ነው። በዛ ዘመን በ1972 ዓ.ም. ጄሊ በርናርድ የተባለች አንዲት የሥነ ማኅበረሰብ አጥኚ እንደገለፀችው በትዳር ሕይወት ሴቶች በውጥረት እና በጭንቀት የተሞሉ ሲሆኑ ወንዶቹ ግን ከሴቶቹ በተሻለ መልኩ ፍፁም ጤንነትን ከትዳራቸው ያተርፋሉ። ይሄ ለየት ያለ የጥናት ውጤት ነው።

የቅርብ ጊዜ አዲስ ጥናት ከአውስትራሊያ እንደሚጠቁመው ከሆነ ግን ሴት ወንድ ሳይባል ሁለቱም የትዳር ጥንዶች በጋብቻ በመተሳሰራቸው ብቻ ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ ጤንነትን ያተርፋሉ። የዚህ ጥናት ባወቤት የሆኑት ሳይኮሎጂስት ዴቪድ ዴቫስ እንዳሉት ከሆነ «በእኔ ጥናትና በቀደመው ጥናት መካከል ልዩነትን እንዲፈጥር ያደረገው ጭንቀትና ውጥረት ለሚሉት ቃላት የሰጠናቸው ፍቺ ይመስለኛል።» በእርግጥም በ10,000 ወንዶችና ሴቶች ላይ የተደረገው ጥናተ እንዳመለከተው ከሆነ ከወንዶች ይልቅ ሴት ባለትዳሮች ጥቂት በጣም ጥቂት

የሆነ የአእምሮ ውጥረት ይታይባቸዋል። ያ ግን በእርግጥ ጭንቀት የሚባለው ደረጃ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ ማየት ያሻል። ምንአልባትም ካለባት ኃላፊነት የተነሳ የሚመጣ ውጥረት ይሆናል። የተመራማሪዎቹ ቃል ነው።

ይህን የጥናት ውጤት የሰሙ ይሥነ ልቦና ባለሙያዎች በአንድ ነገር እየተከራከሩ ነው። በእርግጥ ሴቶችም ወንዶችም በትዳር በመተሳሰራቸው ብቻ ሙሉ የአእምሮ ጤንነት ይኖራቸዋል። የሚለው መደምደሚያ ለሁልጊዜም የሚሠራ ይሆን? ወይስ የቀደመው ጥናት እንዳመለከተው በትዳራቸው አትራፊ የሚሆኑት ወንዶች እንጂ ሴቶች አይደሉም ይሆን? የክርክር ጫፍ ነው።

ይህ ጥናት በትዳር ሕይወት የአእምሮ ጤንነት የሚያገኙት ሴቶችም ወንዶችም ናቸው ይላል። ከ30 ዓመታት ቀድሞ የተደረገ ጥናት በትዳር አትራፊ የሚሆኑት ወንዶች ብቻ ናቸው፣ ሴቶቹ ግን በትዳር ሕይወታቸው ጭንቀትና ውጥረትን ነው የሚያተርፉት ይል ነበር። ሌላ የጥናት ዘገባን ደግሞ ላስነብባችሁ። ሪክ ሳንቶረም የተባሉ ፀሐፊ «The Necessity of marriage» በሚል ርዕስ ካሰፈሩት መጣጥፍ ያገኘሁት ነው።

### ትዳር ለሴቶች

እስከዛሬ ትዳር ለንሰቶች ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ ይመዝናል ሲባል ነበር የምንሰማው። ግን እውነታው ከዚህ ተቃራኒ ነው። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ያገቡ ሴቶች ካላገቡት ሴቶች ይልቅ የጤንነታቸው ሁኔታ በ30 በመቶ ከፍ ያለ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ያገቡ ሴቶች (ወንዶችንም ጨምሮ) ካላገቡት ሴቶች በተሻለ ለረዥም ጊዜ በሚዘልቅ ሕመም አይሰቃዩም፤ ወይም በጤና ሕመም የመያዛቸው አጋጣሚ ጠባብ ነው። ያገቡ ሴቶች በገቢ ደረጃም የተሻለ ጠቀሜታን ያገኛሉ ይላል የጥናት ውጤቱ። በትዳር ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በ50 በመቶ ከፍ ያለ ነው። ያገቡ ወንዶች ገቢ ደግሞ በ25 በመቶ ከፍ ይላል ከወትሮው።

የቤት ውስጥ ጥቃትንና ሌሎች ጥቃቶችንም በመቀነስ ረገድ ጋብቻ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ያገቡ ሴቶች ለተለያዩ ጥቃቶች የመጋለጣቸው አጋጣሚ ካላገቡት ወይም ትዳራቸውን ከፈቱት ሴቶች ያነሰ ነው። ካላገቡ አንድ ሺሕ ሴቶች መካከል ከ11 በላይ የሚሆኑት የተለያዩ ጥቃቶች የሚደርስባቸው ሲሆን፣

ከባለትዳር አንድ ሺሕ ሴቶች መካከል ግን ሁለቱ ብቻ ናቸው ለጥቃት የሚጋለጡት።

**ትዳር ለወንዶች**

በእርግጥ ትዳር ለወንዶች እጅግ በጣም እንደሚጠቅም ነው ጥናቶች የሚጠቁሙት። ለወንጀል ከመጋለጥና ለእስር ከመዳረግ እንጀምር። ያላገቡ (ትዳር ያልፈፀሙ) ወንዶች በተለያዩ ወንጀሎች ሳቢያ ለእስር የመዳረግ አጋጣሚያቸው ካገቡት ወንዶች ጋር ሲነፃፀር በስድስት እጥፍ ይጨምራል። ባለትዳር ወንዶች በአብዛኛው ጊዜያቸውን ከልጆቻቸው ጋር ስለሚያሳልፉ፤ በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ስለሚሳተፉ፣ ዘመድ ጥየቃን ስለሚያዘወትሩ ለወንጀል ለሚያጋልጡ ሁኔታዎች ጊዜ የላቸውም።

በገቢ ረገድም ያገቡት ወንደች ካላገቡት ወንዶች በተሻለ በ25 በመቶ ከፍ ያለ ገቢ ይኖራቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከትዳር ውጪ ከወለዱ ወይም ተፋትተው ለየብቻ ልጆቻቸውን ከሚያሳድጉ ነጠላ ወላጆች (Single - Parnets) ይልቅ በትዳር ተጣምረው ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት ወላጆች ለድህነት የመጋለጥ አጋጣሚያቸው በአምስት እጥፍ የቀነሰ ነው። የሞት አደጋን በመቀነስ ረገድም ቢሆን ትዳር ጠቀሜታው ሰፊ ነው። በትዳር ዓለም በደስታ ከሚኖሩት ይልቅ በፍቺ የተለያዩ ወላጆች እራሳቸውን የማጥፋት አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው እናስ ትዳር አይጠቅምም ይላሉ?

# ባልና ሚስት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንም ሊጋሩ ይችላሉ

***በኖቲንግሐም ሳይንቲስቶች***

ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ። ይሄ ኢትዮጵያዊ ተረት ነው። ቢቢሲ ያስደመጠው ዜና ይሄንኑ አባባል በሳይንስ የሚያረጋግጥ ይመስላል። የሃገራችን ብሂል ባልና ሚስት ከአንድ በህር ይቀዳሉ ሲል የባህሪይ ተመሳስሎ ይኖራቸዋል ለማለት ነው። የቢቢሲ ሳይንሳዊ ዘገባ ደግሞ ምን የባህሪይ ተመሳስሎ ብቻ፣ ባልና ሚስት በሽታንም ከአንድ ባህር ይቀዳሉ ይላል። ግኙቱ የኖቲንግሐም ዩኒቨርስቲ ተመሪማሪዎች ነው። ባልና ሚስት (የፍቅር ጥንዶች) በአንድ ዓይነት በሽታ ሊጠቁ ይችላሉ ይላል። ታዲያ ባልና ሚስቱ የሚጠቁበት ተመሳሳይ በሽታ በሁለቱም ላይ የሚከሰተው ተላላፊ (Infections) ስለሆነ ብቻ አይደለም። በጥናቱ ውጤት መሠረት ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፉ የማይችሉ በሽታዎችን ባልና ሚስቱ ግን ተጋርተውት ይገኛሉ። ይህ የሚሆነው ደግሞ ባልና ሚስቱ በተመሳሳይ አካባቢ ተመሳሳይ የሆነ ምግቦችን ጨምሮ ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን እየተጋሩ በመኖራቸው ነው።

አጥኚዎቹን በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዲያካሂዱ የገፋፋቸው አንድ ጉዳይ በመኖሩ ነው። ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆነ ባልና ሚስቶች (የትዳር ጥንዶች) ወደ ደም ግፊት ምርመራ ክሊኒኮች ያቀናሉ። ታዲያ ለምርመራ በጋራ ከሚሄዱት ጥንዶች ብዙዎቹ ባልና ሚስቶች በተመሳሳይ የደም ግፊት ተጠቅተው ይገኛሉ። ይህን መነሻ በማድረግ አጥኚዎቹ ሰፊ የገሀነ ጥናት ለማካሄድ ወሰኑ። እነሆም አሁን የደረሱበት ውጤት ላይ ደረሱ። የትዳር ጥንዶች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን እንኳን ሊጋሩ ይችላሉ የሚል።

ዕድሜያቸው ከ30-74 በሆኑ 8,000 ያህል የትዳር ጥንዶች ላይ የተደረገ ጥናት ነው - ይሄ ጥናት። እንደ ጥናት ውጤቱ ገለፃ ከሆነ በለቤትዎ በአስም አልያም በደም ግፊት በሽታ የተጠቁ ከሆነ እርስዎም ላይ በሽታው የመገኘቱ አጋጣሚ በእጅጉ የሰፋ ነው። ከትዳር ጥንዶች (ከባል ወይም ከሚስት አንዳቸው በአስም፣ ወይም በደም ግፊት አለዚያም በጨጓራ ቁስለት የሚሰቃዩ ከሆነ ሌላኛቸውም

በተመሳሳይ በበሽታው የመያዝ ዕድላቸው 70 በመቶ የሰፋ ነው። ሳልና ሚስት ከአንድ ባህር ከተቀዱ አይቀር እንደዚህ በደንብ ነው እንጂ። ቸር እንሰንብት።

************************

## አለማወቅ የጥፋት ሰበብ ሲሆን

መደበኛው እለታዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጠናቀቁን የሚገልፀው የትምህርት ቤት ደውል ከተደወለ ጥቂት ደቂቃዎች አልፈዋል። ይህ የመጨረሻ ደውል በየዕለቱ ተደጋግሞ የሚመጣ ቢሆንም የሎተሪ ዕድል ያህል ሁልጊዜም ቢሆን ለተማሪዎች አዲስ እና አስደሳች ነው። ከደውሉ ትንፋሽ መቋረጥ እኩል ተማሪዎች ደብተራቸውን ሸክፈው ግቢውን ጥለው እብስ ይላሉ። ዛሬም ተማሪዎቹ ግቢውን ለቀው ለመውጣት ጊዜ አልፈጀባቸውም። የ8 ዓመቷ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ግን እንደአቻዎቿ እሮጣ እና ጥድፊያ ወደ ቤቷ ለመሄድ የሚያስችል አቅም አልነበራት።

አለፎ አለፎ የሚያገረሽባት ሕመም ዛሬም ያችኑ ያልጠነከረች ጉልበቷን አድቅቆና ከትምህርት ጓደቺ ነጥሎ ብቻዋን አስቀርቷታል። እሷ ግን ተላምዳዋለች። የመጣው ሁሉ በሽታ አልጋ ላይ የሚያውላት ይህች የ8 ዓመት ታዳጊ ይኸው ሳያንሳት ሳንባዋ በበሽታ በመጐዳቱ በተደረገላት ምርመራ ከቫይረሱ ጋር እንደምትኖር ተረጋግጧል። መድሃኒት የምትውጥበትን ምክንያት እንኳን ሳታውቅ በቀን ሁለት ጊዜ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት መዋጥ በልጅነት የተጋፈጠችው እጣዋ ሆኗል።

ስማ እና አካባቢዋ እንዲጠቀስ ያልፈለገችው ወላጅ እናቱ ግን ልጇ 10 ዓመት ዕድሜዋ ላይ ስትደርስ ነው እውነቱን ልትነግራት የወሰነችው። እሺ እንደምትለው ይህችን የመጀመሪያ ልጇን ስትወልድ ባይረሱ ጋር መኖሯን አላወቀችም ነበር። እንደ ልጇ ሁሉ ዘወትር በበሽታ ስትጠቃና ሁለተኛ ልጇ ሲሞት ግን በሐኪም ምክር ተመርምራ ነው ውጤቷን ያወቀችው ያን ጊዜ ለእሷ ፈታኝ የነበረው ነገሩን ለባለቤቷ የመግለፁ ጉዳይ ነበር ይሁን እንጂ ከጤና ጣቢያዎችና በእናቶች የድጋፍ ቡድን በተደረገላት ድጋፍ እና ምክር የፈራቸውን እውነታ ልትጋፈጠው ተገድዳለች ከብዙ ክርክር እና ጭቅጭቅ በኋላ የትዳር አጋርዋም ሐሳቡዋን ተቀብሎ ተመረመረ።

ዛሬ ሦስተኛ ልጇን ብተወልድም ከጤና ባለሙያዎች ባገኘችው የምክር እና ክትትል ድጋፍ ከቫይረሱ ነፃ ሊሆን ችሏል። ይሄ ለእሷ በሴት ልጅ የተሰበረው ልቧን የጠገነና አቻ የማታገኝለት ገፀ-በረከቷ ነው። የዚህች ባለታሪካችን ሁኔታ በሷ ብቻ ተወስኖ የቀረ አይደለም ይልቅም እጅግ በርካታ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች ታሪክ እንጂ የቅድመ ወሊድ የጤና ምርመራና ክትትል ማድረጓ ልጇን ባይረሱ ሊታደግ ችሏል። ሆኖም ግን የአብዛኞቹ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች ወደ ጤና ጣቢያዎች ለመመለስ ድፍረቱን ማጣታቸው ለሞት እና የቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ ሥርጭት ከፍ ማለት ምክንያት መሆኑን ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ላይ ያወጣው ጥናታዊ መረጃ እንደሚያመለክተው በአገራችን በ1996 ዓ.ም. 70ሺ የነበረውና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች ቁጥር በአሁኑ ወቅት ከ75ሺ በላይ ሆኗል። ካቫይረሱ ጋር የሚኖሩና ዕድሜአቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች አሃዝ ከ14 ሺሕ በላይ ደርሷል። በመጪዎቹ ዓመታት ቁጥሩ እንደሚጨምር ነው መረጃው የሚጠቁመው።

ዕድሜአቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑት እና ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩት ታዳጊዎች መካከል 90 ከመቶ የሚሆኑት ቫይረሱን የሚወርሱት ከእናቶቻቸው ነው። ከቫይረሱ ጋር የምትኖር እናት ቫይረሱን የማስተላለፍ አጋጣሚ 37 ከመቶ ነው። 7 ከመቶ በእርግዝና፣ 15 ከመቶ በወሊድ እንዲሁም 15 ከመቶ ጡት በማጥባት ወቅት ነው። ስለዚህም ከቫይረሱ ጋር የምትኖር እናት ወደ ጤና ጣቢያዎች በመሔድ ተገቢውን የጤና የምክር የክትትልና ድጋፍ ካገኘች ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ የመውለድ ዕድሏ ከፍተኛ ነው።

ከዚህ አንፃርም የነፍሰ ጡር እናቶች የቅድመ ወሊድ ምርመራና ክትትል ማጠናከር ቀዳሚውን ድርሻ ሊይዝ እንደሚገባ ነው ባለሙያው የሚናገሩት። አቶ አበበ ሽብሩ በነፍሰጡር እናቶች ክትትልና ድጋፍ ለአራት ዓመታት በሠራው ኢንትራ ሔልዝ ኢንተርናሽናል ካፓሲቲ ፕሮጀክት የፊልድ ኦፕሬሽነ ማናጀር ናቸው። በድርጅታቸው በሠሩበት ዓመታት ነፍሰጡር እናቶች የቅድመ ወሊድ ምርመራ እና ክትትል የቫይረሱን ሥርጭት ለመቀነስ እና የእናቶችን ሞት

በመቀነስ ጤናማ ሕይወት እንዲመሩ ለማስቻል እጅግ የማይናቅ ድርሻ እንዳለው መገንዘባቸውን ይገልጻሉ፡፡

ስለሆነም አገልግሎቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ነው የሚያሳስቡት፡፡ ይሁን እንጂ ይላሉ ባለሙያው የነፍሰ ጡር እናቶች የኤች.አይ.ቪ ምርመሪ የመጠናከሩን ያህል ተከታታይ የጤና ምርመራና ክትትል የማድረጋቸው ሁኔታ ግን እጅግ አናሳ ነው፡፡ ነፍሰ ጡር እናች ከቫይረሱ ጋር መኖራቸውን ካወቁ በኋላ ለምርመራና ክትትል ተመልሰው አይመጡም፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን በምክንያትነት ያነሳሉ፡፡

አድልዎና መገለል፣ ሴቶች የባሎቻቸው የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆን፣ የእናቶችን ፍላጎት ያሟላ ድጋፍና እንክብካቤ ያለመኖር፣ በገጠሩ አካባቢ የጤና ጣቢያዎች የቦታ ርቀት ሲሆን፣ አካባቢ የጤና ጣቢያዎች የቦታ ርቀት ሲሆን፣ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ እናቶች ለማንና እንዴት ልናገር የሚለው እጅግ ፈታኝ ጥያቄ ነው፡፡ የቅርባቸው የሆኑት የትዳር አጋሮቻቸው ቢሆኑም የመደብደብ፣ መባረርና የትዳር መፍረስ ፍራቻ ስለሚያስጨንቃቸው መናገሩን አይደፍሩም፡፡ አቶ አበበ እንደሚያስገነዝቡትም የሚሰጣቸው ምክር መረጃ ከመሰጠት ባሻገር ውጤትን የሚያስጨብጥ ክሕሎት ሊሆን ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ የጤና ባለሙያዎችን የምክር አገልግሎት ግንዛቤ ማሳደግ የግድ ነው፡፡

የእነዚህን ካቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ነፍሰጡር እናቶች ችግ ለመፍታት ከሚንቀሳቀሱት መንግሥታዊ ካልሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶች አንዱ ደግሞ ኢንትራ ሄልዝ ኢንተርናሽናል ካፓሲቲ ፕሮጀክት ነው ድርጅቱ በዩኤስ አይዲ በኩል በፔፕፋር በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በሀገሪቱ ባሉ ክልሎች ባቋቋማቸው 248 የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

በመግቢያችን ላይ የጠቀስናት ከቫይረሱ ጋር የምትኖር እናት ድርጅቱ ባቋቋመው የእናቶች ድጋፍ ፕሮግራም ተጠቃሚ ነች፡፡ በድርጅቱ የፊልድ ኦፐሬሽን ማናጀር የሆኑት አቶ አበበ ሽብሩ የእናቶች ድጋፍና ክትትል ፕሮግራም ችግሩን ከመፍታት አንፃር ጉልህ ድርሻ ስላለው ሊስፋፋ ይገባል፡፡

ቡድኑ ተመሳሳይ የሆኑትንና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶችን ያካተተ ነው፡፡ በመሆኑ እናቶች ችግሩን በግልጽ በመወያየት ሊመካከሩበት እና ልምዳቸውን ሊጋሩበት ይቻላል ከዚህም ባሻገር በኑሮአቸው እንዲደጋገፉ ዕድል ይፈጥራል፡፡
ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ እናቶች ወደ ጤና ጣቢያዎች ተመልሶ ያለመምጣት ጉዳይ በሴቷ ብቻ ሳይሆን በወንዶችም ተፅዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ ትኩረቱ ከእናቶችም የዘለለ ሊሆን ይገባል የችግሩ አካል ናቸውና ወንዶችንም ያሳተፈ ፕሮግራም መዘርጋት የግድ ነው፡፡
ከቫይረሱ ጋር የምትኖር ነፍሰ ጡር እናት ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ መውለድ እና ጤናማ ሕይወት መምራት መቻሏ ከቤተሰብ ባለፈ ማኅበረሰብን ብሎም ትውልድን የመታደግ ሥራ ነውና ሁሉንም ያካተተ የጥምረት ሥራ መሥራት የግድ ነው ስለዚህም ኡንትራ ሄልዝ ከዩኤስአይዲ ጋር በመተባበር እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚሊዮኖችን ሕይወት የመታደግ ነውና ሊበረታታ ይገባል፡፡ ዛሬ የምናከብረው ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን ከቫይረሱ ጋር በተያያዘ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የምናደርገው የጋራ ጥረት የምናጠናክርበት ሊሆን ይገባል፡፡

************************